የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 34
ADDIS ABABA–4th July, 2002

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የገቢ ግብር አዋጅ ............................ ገጽ ፩ሺ፰፻፷፯

CONTENTS

Proclamation No. 286/2002
Income Tax Proclamation................................ page 1867

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬
## የገቢ ግብር አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአገሪቱ ውስጥ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ግንኙነቶችንና ተቋሞችን ለማሳደግና ለማስፋፋት አዲስ ምዕራፍ የከፈተ በመሆኑ፤

በነዚህም ሁኔታዎች መፈጠር ምክንያት አሁን በሥራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር ሥርዓት በመለወጥና በማስተካከል በነፃ ገበያ ሥርዓት ውስጥ ስለተለያዩ የገቢ ምንጮች ከሚሠራባቸው የገንዘብ ነክ ጉዳይ መርሆዎች ጋር እንዲዋሐድ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የግብር ሥርዓቱን ዘመናዊ በማድረግና የግብር መሠረቱን በማስፋት ቁጠባንና ኢንቬስትመንትን ማበረታታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የሚያግዝ መሆኑ ስለታመነበት፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ምዕራፍ ፩
መሠረታዊ ድንጋጌዎች
ክፍል ፩
ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ
በዚህ አዋጅ ውስጥ፣ የተለየ ትርጉም በግልፅ ካልተሰጣቸው በስተቀር፣ በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት በተተረጐሙበት ሕግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፤

## *PROCLAMATION NO. 286/2002*
## *INCOME TAX PROCLAMATION*

WHEREAS, the Declaration on Economic Policy of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia inaugurates a new era in social and economic relations and institutions in this country;

WHEREAS, in consequence of these developments, the existing system of Income Tax needs to be changed and adjusted to the basic principles of fiscal treatment in a free market economy;

WHEREAS, it is believed that modernizing the tax system and broadening the tax base promotes economic growth by encouraging saving and investment;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

CHAPTER I
*Substantive Provisions*
*Section 1*
*General*

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Income Tax Proclamation NO.286/2002"

2. *Definitions*
In this Proclamation, the meanings of terms defined in other laws of Ethiopia apply unless a different meaning is expressly provided herein. For the purposes of this Proclamation the following terms shall have the meanings given to them hereunder:

ያንዱ ዋጋ 5.00
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፩· "ሰው" ማለት ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት ወይም ማኅበር ሲሆን፣ ሌላን ሰው በመወከል ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ሥራ የሚያካሂድ የንግድ ወኪልን ይጨምራል፤

፪· "ድርጅት" ማለት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ወይም ከኩባንያ ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን፣ በውጭ ሀገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ፀንቶ በሚሠራበት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ሕግ የተመሠረተ ወይም ዕውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል፤

፫· "የሰዎች ኅብረት" ማለት ግለሰቦች አባል የሆኑበት ማኅበር ወይም ግለሰብ ያልሆኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ አባላትን የሚጨምር ማኅበር ሲሆን፣ ለ"ድርጅት" በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ማኅበራትን አይጨምርም፤

፬· "ግንኙነት ያላቸው ሰዎች" ማለት፤

(i) የተፈጥሮ ሰው እና

ሀ) የዚህ የተፈጥሮ ሰው ማናቸውም ዘመድ፣ ወይም

ለ) ዘመዱ ተጠቃሚ የሚሆንበት ወይም ሊሆንበት የሚችል የባለአደራ ተቋም፣ ወይም

(ii) ባለአደራ ተቋም እና የዚሁ ባለአደራ ተቋም ተጠቃሚ የሆነ ወይም ሊሆን የሚችል ሰው፣

(iii) የሽርክና ማኅበር፣ የጋራ ልማት ማኅበር፣ የሕግ የሰውነት መብት ያላገኘ ድርጅት ወይም የግል ኩባንያ፣ እና

ሀ) የእነዚህ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው፣

ለ) እንደሁኔታው የሽርክና ማህበር፣ የጋራ ልማት ማህበር ወይም በሕግ የሰውነት መብት ያላገኘ ድርጅት ወይም የግል ኩባንያ አባል የሆነና ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በሚል በተተረጐመው የሚሸፈን ሌላ ሰው፣

(iv) ዝግ ከሆነ ኮርፖሬሽን በስተቀር በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት እና፣

ሀ) በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጠው ድርጅት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወይም ይህ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች፣

(i) በአንድ ኩባንያ ውስጥ ያለውን ድምፅ የመስጠት መብት፣

(ii) የአንድን ኩባንያ ካፒታል ወይም ትርፍ የመከፋፈል መብት በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች መካከል ባለ አገናኝ ኩባንያ፣ የሽርክና ማኅበር ወይም ባለአደራ ተቋም አማካኝነት፣

፲ ፐርሰንት (አሥር በመቶ) እና ከዚያ በላይ የያዙ በሚሆንበት ጊዜ፣

ለ) በተራ ፊደል (ሀ) በመጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ወይም ይህ ሰው እና በዚህ ትርጉም መሠረት ከዚህ ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሰው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ኩባንያ ውስጥ፣

(i) በኩባንያው ውስጥ ያለውን ድምፅ የመስጠት መብት፣

1) "Person" shall mean any individual, body, or association of persons (including a business representative residing and doing business in Ethiopia on behalf of the principal).

2) "Body" shall mean any company, registered partnership, entity formed under foreign law resembling a company or registered partnership, or any public enterprise or public financial agency that carries out business activities including body of persons corporate or unincorporated whether created or recognized under a law in force in Ethiopia or elsewhere and any foreign body's business agent doing business in Ethiopia on behalf of the principal.

3) "Association of persons" shall mean an association of individuals or an association that includes one or more members who are not individuals, but not including any association falling within the definition of "body".

4) "Related person" means:

(i) a natural person and,
  (a) any relative of that natural person; or
  (b) a trust in respect of which such relative is or may be a beneficiary; or

(ii) a trust and a person who is or may be a beneficiary in respect of that trust; or

(iii) a partnership, joint venture, or unincorporated association,or body or private company; and
  (a) any member thereof; or
  (b) any other person where that person and a member of such partnership, joint venture, or unincorporated association or body, or private company as the case may be, are related persons in terms of this definition; or

(iv) an incorporated company, other than a closed
  (a) a person, other than an incorporated company, where that person or that person and a person a person related to the first mentioned person in terms of this definition controls 10 percent or more of;
    (i) the right to vote in the first mentioned company; or
    (ii) the rights to distributions capital or profits of the first-mentioned company, either directly or through one or more interposed companies, partnerships, or trusts; or
  (b) any other incorporated company in which the first mentioned person referred to in (a) or that person and a person related to that first mentioned person in terms of this definition controls 10 percent or more of:
    (i) the right to vote in the first mentioned company, or

(ii) በመጀመሪያ የተጠቀሰውን ኩባንያ ካፒታል ወይም ም ትርፍ የመከፋፈል መብት፣ በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ኩባንያዎች መካከል ባለ አገናኝ ኩባንያ፣ የሽርክና ማኅበር ወይም ባለአደራ ተቋም አማካኝነት ፲ ት ፐርሰንት (አሥር በመቶ) እና ከዚያ በላይ የያዘ ሲ በሚሆንበት ጊዜ፣

ሐ) ማንኛውም ሰው፣ ይህ ሰው እና በተራ ፊደል (ሀ) የተመለከተው ሰው ወይም በተራ ፊደል (ለ) የተመለከተው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት በዚህ ትርጉም መሠረት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ሆነው የተቆጠሩ በሚሆንበት ጊዜ፣ ወይም

መ) ማናቸውም ሰው፣ በዚህ ትርጉም መሠረት በተራ ፊደል (ሐ) ከተመለከተው ሰው ጋር ግንኙነት ያለው ሆኖ የተቆጠረ በሚሆንበት ጊዜ፣

፭. "ዝምድና" ማለት፤
(i) ግለሰብ እና የትዳር ጓደኛ፣
(ii) በቀጥታ ወደላይ ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ዘመዶች፣ ወንድም፣ እህት፣ አጐት፣ አክስት፣ የአክስት ወይም የአጐት ልጅ፣ የእንጀራ አባት፣ የእንጀራ እናት፣ የእንጀራ ልጅ፣ ወይም የግለሰቡ ወይም የትዳር ጓደኛው የጉዲፈቻ ልጅ፣ እና የጉዲፈቻ ልጅን በተመለከተ የጉዲፈቻ አሳዳጊዎች፣ ወይም
(iii) በንዑስ አንቀጽ II የተመለከተው ማንኛውም ሰው የትዳር ጓደኛ እና ለዚህ ትርጉም አፈፃፀም ማንኛውም የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አሳዳጊው ጋር የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና እንዳለው፣ ይቆጠራል።

፮. "የንግድ ሥራ" ወይም "ንግድ" ማለት በማናቸውም ሰው አማካኝነት ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም የጣልቃ ገብ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም፣ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንደ ንግድ ሥራ ዕውቅና የተሰጠው ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ ነው፤

፯. "ግብር ከፋይ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው ነው፤

፰. "ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው" ማለት ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው፤

፱. "በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት" ማለት አንድ ሰው የንግድ ሥራውን በሙሉ ወይም በከፊል የሚያከናውንበት ቋሚ የንግድ ሥራ ቦታ ነው። የሚከተሉት በተለይ በቋሚነት የሚሠራ የንግድ ድርጅት በመባል ይታወቃሉ።

ሀ) የንግድ ሥራው የአስተዳደር ማዕከል፣ ቅርንጫፍ፣ ፋብሪካ፣ የቴክኒክ ሥራዎች የሚከናወኑበት ሥፍራ፣ ለዚህ አዋጅ አግባብነት እስካለው ድረስ ማናቸውም ሌላ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም ላይ በሚውሉበት ሁኔታ የሚዘጋጁበት ሥፍራ ሕንፃ የሚገነባበት ቦታ ወይም የግንባታ ወይም የመገጣጠም ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ፤

ለ) አንድ ሰው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የለውም የሚባለው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ስቻ የሚያከናውን ከሆነ ነው፤
(i) ድርጅቱን የራሱ የሆኑትን ዕቃዎችና ሸቀጦች ለማከማቸት ወይም በናሙናነት ለማሳየት ብቻ የሚጠቀምበት ሲሆን፣
(ii) የራሱ የሆነውን የዕቃ ወይመ ሸቀጥ ክምችት የሚይዘው በመጋዘን ለማስቀመጥ ወይም በናሙናነት ለማሳየት ብቻ ሲሆን፣
(iii) የራሱ የሆነውን የዕቃ ወይም የሸቀጥ ክምችት የያዘው በሌላ ሰው በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ከሆነ፣
(iv) የተወሰነ ሥፍራ ያለውን የንግድ ሥራ ቦታውን የሚጠቀምበት ለንግድ ሥራው የሚውሉ ዕቃዎችን ወይም ሸቀጦችን ለመግዣ ወይም መረጃዎችን ለማሰባሰቢያ ብቻ የሆነ እንደሆነ፣

(ii) the rights to distributions of capital or profits of the first-mentioned company, either directly or through one or more interposed companies, partnerships, or trusts; or

(c) any person where that person and the person referred to in (a) or the other incorporated company referred to in (b) are related persons in terms of this definition; or

(d) any person related to the person referred to in (c) in terms of this definition; or

"Relative" in relation to a natural person; means:
(i) the spouse of the rpeson; or
(ii) an ancestor, lineal descendant, brother, sister, uncle, aunt, nephew, niece, stepfather, stepmother, stepchild, or adopted child of that person or of the spouse, and in the case of an adopted child the adoptive parent; or
(iii) the spouse of any person referred to in paragraph (ii) and for the purposes of this definition, any adopted child is treated as related to her adoptive parent within the first degree of consanguinity.

6) "Business" or "Trade" shall mean any industrial, commercial, professionl or vocational activity or any other activity recognized as trade by the Commercial Code of Ethiopia and carried on by any person for profit.

7) "Taxpayer" shall mean any person subject to tax under this Proclamation.

8) "Withholding Agent" shall mean any person with a tax collection obligation under this proclamation.

9) "Permanent Establishment" shall mean a fixed place of business through which the business of a person is wholly or partly carried on. The following shall, in particular, be considered to be a permanent establishment:

(a) an administrative, branch, factory, workshop, mine, quarry or any other place for the exploitation of natural resources, and a building site or place where construction and/or assembly works are carried out.

(b) A person shall be considered not to have a permanent establishment if that person:
(i) uses facilities solely for the purpose of storage or display of goods or merchandise belonging to that person;
(ii) maintains a stock of goods or merchandise belonging to that person solely for the purpose of storage or display;
(iii) maintains stock of goods or merchandise belonging to that person solely for the purpose of processing by another person;
(iv) maintains a fixed place of business solelly for the purpose of purchasing goods or merchandise or a collecting information for that person's business;

(v) የተወሰነ ሥፍራ ያለውን የንግድ ሥራ ቦታውን የሚጠቀምበት ለንግድ ሥራው የሚጠቅሙ ዝግጅቶችን ወይም ለዚሁ ሥራው ብቻ የሚያግዙ ተግባሮችን ለማከናወን ከሆነ፣ ነው።

ሐ) ከዚህ በላይ በተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተነገረው ቢኖርም፣ ወኪል፣ ከዚህ በታች በፊደል (ሠ) የተመለከተው ተፈፃሚ የሚሆንበትን ራሱን ችሎ የሚሠራን ወኪል ሳይጨምር፣ አንድን ሰው ወክሎ የሚሠራ ከሆነ ወይም በወከለው ሰው ስም ውል የመፈፀም ሥልጣን ያለውና ይህንን ሥልጣኑን አዘውትሮ የሚጠቀምበት ከሆነ፣ ወካዩ ወኪሉ እርሱን ወክሎ የሥራ እንቅስቃሴውን በሚያከናውንበት ቦታ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት እንዳለው ይቆጠራል። ሆኖም ወኪሉ ሥራውን የሚያከናውንበት የተወሰነ ሥፍራ ያለው ቢሆንም በቋሚነት እንደሚሠራ ድርጅት በማያስቆጥሩት ከዚህ በላይ በፊደል (ለ) በተዘረዘሩት የሥራ እንቅስቃሴዎች የተወሰነ ከሆነ፣ በተወሰነ ሥፍራ ያለው የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ በቋሚነት የሚሠራ የንግድ ድርጅት አያሰኘውም፤

መ) ማንኛውም ሰው በደላላ፣ በጠቅላላ የኮሚሽን ወኪል ወይም ራሱን ችሎ በሚሠራ በማናቸውም ሌላ ወኪል አማካኝነት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴን በማከናወኑ ብቻ እንደዚህ ያሉት ወኪሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴውን የሚያከናውኑት መደበኛ የንግድ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ካልሆነ በስተቀር በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት እንዳለው አይቆጠርም፤

ሠ) አንድ ኩባንያ ሌላውን ኩባንያ በመቆጣጠሩ ወይም በሌላ ኩባንያ ቁጥጥር ሥር የሚሠራ በመሆኑ ምክንያት ብቻ አንዱ የሌላው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት እንደሆነ ተደርጐ አይወሰድም።

፲. "ገቢ" ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን፣ በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ ይጨምራል፤

፲፩. "ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ማለት በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡት ደንቦች መሠረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሣቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን ነው፤

፲፪. "ተቀጣሪ" ማለት የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት በውል የሚቀጠርን ሰው ሳይጨምር በቀጣሪው ቁጥጥር እና በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ነው፣

ሀ) "ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ" ማለት መደበኛ የሙያ ሥልጠና ያልወሰደ፣ ልዩ ሙያ በሚጠይቁ ማሽኖችና መሣሪያዎች የማይጠቀም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ከ፴ ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የተቀጠረ ግለሰብ ነው፤

ለ) "የተወሰነ አገልግሎት ለመስጠት በውል የሚቀጠር ሰው" ማለት ሥራውን በራሱ የመምራትና የመቆጣጠር በቂ ሥልጣን በሚሰጠው ውል መሠረት ሥራውን የሚያከናውን ግለሰብ ነው።

፲፫. "የግብር ባለሥልጣን" ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የየክልሉ የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው።

(v) maintains a fixed place of business solely for the purpose of carrying on, for that person's business, any other activity of a preparatory or auxiliary character.

(c) Notwithstanding the provisions of sub-Articles (a) and (b) above, where an agent, other than an agent of an independent status to whom letter (e) below applies, acts on behalf of a person and has, and habitually exercises, an authority to conclude contracts in the name of that person and has, and habitually exercises, an authority to conclude contracts in the name of that person, that person shall be treated as if it has a permanent establishment in respect of any activities which the agent undertakes for the person at the place at which those activities are carried on, unless the activities of such agent are limited to those mentioned in letter (b) above which, if exercised through a fixed place of business, would not make that fixed place of business a permanent establishment.

(d) A person shall not be treated as if it has a permanent establishment where it merely carries on its business activities through a broker, general commission agent or any other agent of an independent status, provided that such agents are acting in the ordinary course of their business.

(e) The fact that a company controls or is controlled by another company shall not of itself constitute either company a permanent establishment of the other.

10) "Income" shall mean every sort of economic benefit including nonrecurring gains in cash or in kind, from whatever source derived and in whatever form paid credited or received.

11) "Taxable Income" shall mean the amount of income subject to tax after deduction of all expenses and other deductible items allowed under this Proclamation and Regulations issued there under;

12) "Employee" shall mean any individual, other than a contractor, engaged (whether on a permanent or temporary basis) to perform services under the direction and control of the employer;

(a) "Unskilled Employee" shall mena an employee who has not received vocational training, does not use machinery or equipment requiring special skill, and who is engaged by an employer for a period aggregating not more than 30 days during a calendar year;

(b) "Contractor" shall mean an individual who is engaged to perform services under an agreement by which the individual retains substantial authority to direct and control the manner in which the services are to be performed.

13) "Tax Authority" shall mean the Federal Inland Revenue Head Office or any of its branch offices estblished in any part of Ethiopia and the tax authorities of the Regional States.

፲፬· "ሚኒስትር" እና "ሚኒስትር" ማለት የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትርና የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ናቸው

፲፭· "የበጀት ዓመት" ማለት የኢትዮጵያ መንግሥት የበጀት ዓመት ነው፤

፲፮· "የደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋይ" "የደረጃ 'ለ' ግብር ከፋይ" እና "የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋይ" በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የተሰጣቸውን ትርጉም ይዖዛሉ።

፫· የተፈፃሚነት ወሰን

፩· ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ባገኙት ገቢ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪· በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በተመለከተ አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ ባገኙት ገቢ ላይ ብቻ ይሆናል።

፬· ግብር የመክፈል ግዴታ

ማንኛውም በዚህ ሕግ የሚሸፈን ገቢ ያገኘ ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

፭· ነዋሪ

፩· ማንኛውም ግለሰብ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፣

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ ያለው፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያዘወትረው ማረፊያ ቦታ ያለው እና/ወይም

ሐ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው እና ከኢትዮጵያ ውጭ በኰንሱላር፣ በዲፕሎማቲክ ወይም በተመሳሳይ ሥራ ተመድቦ የሚሠራ ሲሆን፣

ነው።

፪· በአሥራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ሳያቋርጥ ወይም በመመላለስ ከ፩፻፹፫ ቀናት በላይ የኖረ ግለሰብ ለዚያው የታክስ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ እንደሆነ ይቆጠራል።

፫· ድርጅት በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው፤

ሀ) ዋና ጽ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሆነ፤

ለ) ለውጥ የሚያስከትል ውሣኔ ለመስጠት የሚችል የአመራር አካል በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ከሆነ እና/ወይም

ሐ) እንደአግባብነቱ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም በየክልሉ የንግድ ቢሮዎች የንግድ መዝገብ ላይ የተመዘገበ ከሆነ፤

፬· "ነዋሪ የሆነ ሰው" በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ንብረት የሆነውን በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ይጨምራል።

፮· የገቢ ምንጭ

በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በእነዚህ ሳይወሰን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል፤

ሀ) ከቅጥር የሚገኝ ገቢ፤

ለ) ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፣

ሐ) የማዝናናት ሥራ የሚሠራ፣ ሙዚቀኛ ወይም ስፖርተኛ በግል ካከናወነው ሥራ የሚያገኘው ገቢ፣

መ) ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነ ሰው በቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት አማካኝነት ከሚያከናውነው የንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ፣

ሠ) በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት ተንቀሳቃሽ ንብረት የሚገኝ ገቢ፣

ረ) ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እና ከተቀፅላዎቻቸው የተገኘ ገቢ፣ ከቁም ከብት፣ ከግብርና እና ከደን የሚገኝ ገቢ፣ ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች አላባ እና ማናቸውም ሌላ መብት የሚገኝ ገቢ፣ እነዚህ ንብረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ እስከሆነ ድረስ፣

ሰ) በፊደል (ሠ) የተመለከቱትን ንብረቶች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፣

14) "Minister" shall mean the Minister of Finance and Economic Development and "Ministry" shall mean the Ministry of Finance and Economic Development.

15) "Fiscal Year" shall mean the budgetary year of the Ethiopian Government.

16) "Category A taxpayer", "Category B taxpayer", and "Category C taxpayer" shall have the respective meanings given to them in a regulation to be issued hereunder.

3. Scope of Application

1) This Proclamation shall apply to residents of Ethiopia with respect to their worldwide income.

2) The Proclamation shall apply to non-residents of Ethiopia with respect to their Ethiopian source income.

4. Obligation to pay Income Tax

Every person having income as defined herein shall pay income tax in accordance with this Proclamation

5. Residence

1) An individual shall be resident in Ethiopia, if he:

(a) has a domicile within Ethiopia;

(b) has an habitual abode in Ethiopia; and/or

(c) is a citizen of Ethiopia and a consular, diplomatic or similar official of Ethiopia posted abroad.

2) An individual, who stays in Ethiopia for more than 183 days in a period of twelve (12) calendar months, either continuously or intermittently, shall be resident for the entire tax period.

3) A body shall be resident in Ethiopia, if it:

(a) has its principal office in Ethiopia;

(b) has its place of effective mangement in Ethiopia; and/or

(c) is registered in the trade register of the Ministry of Trade and Industry or Trade bureaux of the Regional Governments as appropriate.

4) "Resident person" includes a permanent establishment of a non-resident person in Ethiopia.

6. *Source of Income*

Income taxable under this proclamation ahall include, but not limited to:

(a) income from employment;

(b) income from business activities;

(c) income derived by an entertainer, musician, or sports person from his personal activities;

(d) income from enterpreneurial activities carried on by a non-resident through a permanent establishment in Ethiopia;

(e) income from movable property attributable to a permanent establishment in Ethiopia;

(f) income from immovable property and appurtenances thereto, income from livestock and inventory in agriculture and forestry, and income from usufruct and other rights deriving from immovable property is uch property is situated in Ethiopia;

(g) income from the alienation of property referred to in (e);

ሸ) ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ የሆነ ኩባንያ የሚያከፋፍለው የአክሲዮን ድርሻ፣

ቀ) ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ የሆነ የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር የሚያከፋፍለው የትርፍ ድርሻ፣

በ) በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት ወይም በከተማ መስተዳድሮች ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ባይሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት የተከፈለ ወለድ፣

ተ) የራስ በሆነ ነገር ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የተሰጠ ፈቃድ ክፍያ (በሊዝ መብት መጠቀምን ጨምሮ) እና በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ በሆነ ሰው ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ባይሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት የተከፈለ የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

፯· በውጭ አገር የተከፈለን ግብር ስለማካካስ

፩· በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ሰው በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ምንጩ ከኢትዮጵያ ውጪ የሆነ ገቢ ያገኘ እንደሆነ፣ በዚህ ገቢ ላይ በውጭ አገር መከፈል በሚገባው ግብር መጠን ነዋሪው በኢትዮጵያ ውስጥ መክፈል ከሚገባው ግብር ላይ ይቀነስለታል። በውጭ አገር የተከፈለው ግብር እንደግብር ውሣኔ ማስታወቂያ፣ ከተከፋይ ሂሳብ ግብር ተቀናሽ መደረጉን በሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ወይም በግብር ባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ባለው ሌላ ተገቢ ማስረጃ መረጋገጥ አለበት።

፪· ሆኖም ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀነሰው ግብር በኢትዮጵያ ውስጥ መከፈል ካለበት ግብር ሊበልጥ አይችልም።

፫· በሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር መክፈል ያለበትን ግብር ከፋይ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረገው ማናቸውም ተቀናሽ ግብር፣ ይህ ቅናሽ ባይኖር ኖሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊከፈል የሚገባው ግብር መጠን የሚወሰን ሆኖ፣ ስሌቱ የሚከናወነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ የተመለከተው (ኪሣራን ማሸጋገር) ከእያንዳንዱ አገር የተገኘውን ትርፍ እና ኪሣራ በተናጠል እንደሚመለከት ተደርጐ ነው።

፬· በዚህ አንቀጽ የተፈቀደው ተቀናሽ ግብር፣ ገቢ ወይም ትርፍ የተገኘበትን እያንዳንዱን አገር በሚመለከት በተናጠል መሰላት ይኖርበታል።

፰· የግብር ዓይነቶች

ይህ አዋጅ በሚከተለው ዓይነት በተመደቡ አራት ሠንጠረዦች ግብር እንዲከፈል ይደነግጋል፤

፩· ሠንጠረዥ 'ሀ'፣ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣

፪· ሠንጠረዥ 'ለ'፣ ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

፫· ሠንጠረዥ 'ሐ'፣ የክልል መንግሥታት በሚያወጡት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ ሥር የተመደበ ካልሆነ በስተቀር በአንቀጽ ፪(፮) ከተገለፁት የንግድ ሥራዎች የሚገኝ ገቢ፣

፬· ሠንጠረዥ "መ"፣ ሌሎች ገቢዎች የሚከተሉትን ጨምሮ፣

ሀ) የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

ለ) ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚሰጥ አገልግሎት የሚገኝ ገቢ፣

ሐ) በዕድል ሙከራ ውድድር አሸናፊነት የሚገኝ ገቢ፣

መ) ከአክሲዮን ድርሻ፣

ሠ) ቋሚ ባልሆነ ሁኔታ ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ፣

ረ) በወለድ ገቢ፣

ሰ) ከንግድ ሥራ ጋር ካልተያያዘ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም፣

፱· በውጭ ምንዛሪ የሚደረግ ግብይት

በውጭ ምንዛሪ በሚደረግ ግብይት የተገኘ ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሣራ ለግብር አከፋፈል ሲባል ግብይቱ በተከናወነበት የግብር ዓመት ውስጥ እንደተገኘ ጥቅም ወይም እንደ ደረሰ ኪሣራ ሆኖ መገለጽ አለበት።

(h) dividends distributed by a resident company;

(i) profit shares paid by a resident registered partnership;

(j) interest paid by the national, a regional or local Government or a resident of Ethiopia, or paid by a non-resident through a permanent establishment that he maintains in Ethiopia;

(k) license fees (including lease payments, and royalties paid by a resident or paid by a non-resident through a permanent establishment that he maintains in Ethiopia.

7. Foreign Tax Credit

1) If during the tax period a resident derives foreign source income, the Income Tax payable by that resident in respect of that income shall be reduced by the amount of foreign tax payable on such income. The amount of foreign tax payable shall be substantiated by appropriate evidence such as a tax assessment, a withholding certificate or any other similar document accepted by the Tax Authority.

2) However, the reduction of the Income Tax provided by Sub-Article (1) shall not ex ceed the tax payable in Ethiopia that would otherwise be payable on the foreign source income.

3) In the case of a taxpayer subject to Income Tax on Schedule C income, any reduction of tax prescribed by Sub-Article (1) shall be limited to the tax that would otherwise be payable in Ethiopia computed as if Article 28 (loss carry forward) of this Proclamation applied separately to each foreign country in respect of profit and losses derived from sources therein.

4) The reduction of tax prescribed by this Article shall be calculated separately in respect of each foreign country from which income or profit is derived.

8. Schedules of Income

This Proclamation provides for the taxation of income in accordance with four schedules, as follows:

1) Schedule 'A,' income from employment;
2) Schedule 'B,' income from rental of buildings;
3) Schedule 'C,' income from business as defined in Article 2(6), but not including activities covered by the Rural Land Use Fee and Agricultural Activities Income Tax Proclamations issued by regional states;
4) Schedule 'D', other income including income from:
   (a) royalties;
   (b) income paid for services rendered outside of Ethiopia;
   (c) income from games of chance;
   (d) dividends;
   (e) income from casual rental of property;
   (f) interest income;
   (g) specified non-business capital gains.

9. Foreign Exchange Transactions

All net gains and losses arising from any transactions in foreign exchanges shall be brought to account for tax purposes as additions to taxable income or deductible losses in the year in which they are realized.

## ክፍል ፪
## የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ
## ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣

፲· ግብር የሚከፈልበት ገቢ

፩· ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ ከዚህ በታች በአንቀጽ ፲፩ በተመለከተው ሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላል። በመቀጠር የሚገኝ የመጀመሪያው ብር ፩፻፶ (አንድ መቶ አምሳ ብር) የገቢ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ውስጥ አይካተትም፣

፪· ማንኛውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ግብሩን መቀነስ፣ የተቀነሰውን ግብር በየወሩ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። ከዚህ በላይ ለተነገረው አፈፃፀም የነሐሴ ወርና የጳጉሜ ገቢ በአንድነት ተጠቃሎ እንደ አንድ ወር ገቢ ይቆጠራል።

፲፩· የግብር ማስከፈያ መጣኔ

ሠንጠረዥ "ሀ"

| ከመቀጠር የሚገኝ የወር ደመወዝ | | የሚከፈለው ግብር በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከብር | እስከ ብር | |
| 0 | 150 | ከግብር ነፃ |
| 151 | 650 | 10 |
| 651 | 1400 | 15 |
| 1401 | 2350 | 20 |
| 2351 | 3550 | 25 |
| 3551 | 5000 | 30 |
| ከ5000 | በላይ | 35 |

፲፪· ከመቀጠር የሚገኝን ገቢ ስለመወሰን

፩· ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣ ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ሲሆን፣ ከቀድሞ ቅጥር የተገኘን ገቢ እና ወደፊት ለመቀጠር አስቀድሞ የሚደረግ ክፍያን ይጨምራል።

፪· ግብር የሚከፈልባቸው በዓይነት የሚሰጡ ጥቅሞች እና እነዚህ ጥቅሞች የሚሰሉበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፫· በደመወዝ መልክ የተገኘ ጥቅም መ/ቤቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለመገኘት የሚደረገውን እና ሌሎች ተመሳሳይ ወጪዎችን (በማኅበራዊ ተግባሮች፣ እንግዳን ለማስተናገድ የወጡትን ወጪዎች ወ·ዘ·ተ) አይጨምርም።

፲፫· ከግብር ነፃ ስለማድረግ

የሚከተሉት ገቢዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚከፈል ግብር ነፃ ይሆናሉ፤

ሀ) በማንኛውም የአሥራ ሁለት (፲፪) ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪ ከአንድ (፩) ወር ለበለጠ ጊዜ ያላገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ የሚያገኘው ገቢ፣

ለ) በቀጣሪዎች የሚዋጣ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ፲፭ ፐርሰንት ያልበለጠ የጡረታ መዋጮ፣ ፕሮቪደንት ፈንድ እና ማናቸውም ዓይነት የጡረታ ጥቅም፣

ሐ) ተመሳሳይ ሁኔታ ለኢትዮጵያውያን ተፈፅሞ ሲገኝ፣

## SECTION II
## Schedule 'A' Income /Employment Income

10. Taxable Income

1) Every person deriving income from employment is liable to pay tax on that income at the rate specified in Schedule A, set out in Article 11. The first Birr 150 (one hundred fifty Birr) of employment income is excluded from taxable income.

2) Employers have an obligation to withold the tax from each payment to an employee, and to pay to the Tax Authority the amount withheld during each calendar month. In applying the preceding, income attributable to the months of Nehassie and Pagumen shall be aggregated and treated as the income of one month.

11. Tax Rate

Schedule A

| Employment income (per month) | | Income Tax payable |
|---|---|---|
| Over Birr | to Birr | |
| 0 | 150 | exempt threshold |
| 151 | 650 | 10 |
| 651 | 1400 | 15 |
| 1401 | 2350 | 20 |
| 2351 | 3550 | 25 |
| 3551 | 5000 | 30 |
| Over 5000 | | 35 |

12. Determination of Employment Income

1) Employment income shall include any payments or gains in cash or in kind received from employment by an individual, including income from former employment or otherwise or from prospective employment.

2) The type of taxable fringe benefits and the manner of their assessment shall be determined by Regulations to be issued by the Council of Ministers.

3) Income received in the form of wages does not include representation and other similar expenditures (on social functions, guest accommodations, etc.)

13. Exemptions

The following categories of income shall be exempt from payment of income tax hereunder:

(a) income from employment received by casual employees who are not regularly employed provided that they do not work for more than one (1) month for the same employer in any twelve (12) months period;

(b) pension contribution, provident fund and all forms of retirement benefits contributed by employers in an amount that does not exceed 15% (fifteen percent) of the monthly salary of the employee;

(c) subject to reciprocity, income from employment, received for services rendered in the exercise of their duties by:

(i) የዲፕሎማቲክና የቆንሲላዎች ወኪሎች፣ እና
(ii) በማንኛውም ኤምባሲ፣ ሌጋሲዮን፣ ቆንስላዎች ወይም የውጭ አገር መንግሥት ውስጥ ተቀጥረው የዚያን ሀገር ጉዳይ የሚፈፅሙና የዲፕሎማቲክ ይለፍ ፈቃድ የያዙ ወይም በዓለም ዐቀፍ አሠራር ወይም ልማድ መሠረት አብዛኛውን ጊዜ ከግብር ነፃ የሆኑ ሰዎች፣ ተቀጥረው በሚሰጡዋቸው አገልግሎቶች ምክንያት የሚያገኙዋቸው ገቢዎች፣

መ) በተለይ ከገቢ ነፃ እንዲሆን፣
(i) በዚህ አዋጅ በተለይ ካልተሻሻለ ወይም ካልተሰረዘ በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች፣
(ii) በዓለም ዐቀፍ ስምምነቶች፣ ወይም
(iii) በሚኒስትሩ በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ገቢ፣

ሠ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለኤኮኖሚ፣ ለማኅበራዊ ወይም ለአስተዳደር ምክንያቶች በዚህ አዋጅ ገቢ ተብሎ ዕውቅና የተሰጠውን ማናቸውንም ገቢ በደንብ ነፃ ሊያደርግ ይችላል።

ረ) ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጋር በተያያዘ ለአንድ ሰው የሚፈፀም ካሣ ወይም ስጦታ፦
፩· በተቀባዩ ሰው ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት፣
፪· በሌላ ሰው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ።

## ክፍል ፫
## የሠንጠረዥ "ለ" ገቢ
## ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

፲፬· ግብር የሚከፈልበት ገቢ

በማናቸውም ሁኔታ ከተከራየ ቤት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይከፈላል።

፲፭· የግብር ማስከፈያ ልክ

ከተከራዩ ቤቶች በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር የሚወሰነው የሚመደበውና የሚከፈለው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው፦

ሀ) በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጣቸው ድርጅቶች ገቢ ላይ ሲሆን ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ፴ ፐርሰንት ሠላሳ በመቶ ፣
ለ) በግለሰቦች ገቢ ላይ ሲሆን ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ፣

ሠንጠረዥ "ለ"

| ግብር የሚከፈልበት የዓመት የኪራይ ገቢ | | የሚከፈለው የገቢ ግብር በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከብር | እስከ ብር | |
| 0 | 1,800 | ከግብር ነፃ |
| 1,801 | 7,800 | 10 |
| 7,801 | 16,800 | 15 |
| 16,801 | 28,200 | 20 |
| 28,201 | 42,600 | 25 |
| 42,601 | 60,000 | 30 |
| ከ60,000 | በላይ | 35 |

፲፮· ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ስለመወሰን

፩· በቤት ኪራይ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር የሚታሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፤
ሀ) ቤቱ ወይም ግቢው ከነዕቃው የተከራየ እንደሆነ፣ የዕቃው ወይም የመሣሪያው ኪራይ ከጠቅላላው ገቢ ጋር ይደመራል፣



(i) diplomatic and consular representatives, and
(ii) other persons employed in any Embassy, Legation, Consulate or Mission of a foreign state performing state affairs, who are national of that state and bearers of diplomatic passports or who are in accordance with international usage or custom normally and usually exempted from the payment of income tax.

(d) income specifically exempted from income tax by:
(i) any law in Ethiopia, unless specifically amended or deleted by this Proclamation;
(ii) international treaty; or
(iii) an agreement made or approved by the Minister.

(e) the Council of Ministers may by regulations exempt any income recognized as such by this Proclamation for economic, administrative or social reasons.

(f) payments made to a person as compensation or a gratitude in relation to:
(i) personal injuries suffered by that person;
(ii) the death of another person.

## Section III
## Schedule 'B' Income/Income From Rental of Buildings

14. Taxable Income

Income tax shall be imposed on the income from rental of buildings.

15. Tax Rate

The tax payable on rented houses shall be charged, levied and collected at the following rates:
(a) on income of bodies thirty percent (30%) of taxable income,
(b) on income of persons according to the Schedule B (hereunder)

Schedule 'B'

| Taxable Income from Rental (per year) | | Income Tax payable |
|---|---|---|
| Over Birr | to Birr | |
| 0 | 1800 | exempt threshold |
| 1,801 | 7,801 | 10 |
| 7,801 | 16,800 | 15 |
| 16,801 | 28,200 | 20 |
| 28,201 | 42,600 | 25 |
| 42,601 | 60,000 | 30 |
| Over 60,000 | | 35 |

16. *Determination of Income*

1) Income from rental of building shall be computed as follows:
(a) if the tax payer leased furnished quarters the amounts received attributable to the lease of furniture and equipment shall be included in income.

ለ) ተከራይቶ በማከራየት የሚገኘው ገቢ የቤቱ ባለቤት ለሆነው አከራይ ከሚከፈለው የኪራይ ዋጋ የበለጠ ከሆነ ተከራይተው የሚያከራዩ ግብር ከፋዮች ግብሩን የሚከፍሉት በሚያገኙት የገቢ ልዩነት ላይ ነው።

ሐ) ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሠላበት ጊዜ የሚከተሉት ከጠቅላላ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋሉ፤

(i) ከገቢ ግብር በስተቀር ከተከራየው ቤት ጋር በተያያዘ የተከፈለ የመሬት ግብር እና የሕንፃ ታክስ፤

(ii) መዝገብ ለማይዙ ግብር ከፋዮች ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃና ለመሣሪያ ማደሻ፣ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ (ዲፕሪሲየሽን) የሚሆን ከቤት፣ ከቤት ዕቃና ከመሣሪያ ከሚገኘው ጠቅላላ የኪራይ ገቢ አንድ አምስተኛው፣

(iii) መዝገብ ለሚይዙ ግብር ከፋዮች፣ ግብር ከፋዩ ወጪዎቹን በማስረጃ ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው የኪራዩን ገቢ ለማግኘት፣ ለኪራዩ ንግድ ሥራ ዋስትና ለመስጠት፣ እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ። ተቀናሽ የሚደረጉት ወጪዎች በእነዚህ ሳይወሰኑ ለመሬት ሊዝ (ኪራይ) ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃና ለመሣሪያ ማደሻ፣ መጠገኛና ለእርጅና መተኪያ (ዲፕሪ ስየሽን)፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት እንዲሁም የባንክ ወለድ፣ የኢንሹራንስ አረቦን፣ የሚሆነው ወጪ በሚይዙት መዝገብ መሠረት ተቀናሽ ይደረጋሉ፣

፪. ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት፣ ተከራዩ ግብሩን ባይከፍል ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል።

፫. ለኪራይ የሚሠሩ ቤቶች ተሠርተው እንዳለቁ ወይም ቤቱ እንደተከራየ፣ ከሁለቱ በሚቀድመው ጊዜ የቤቱ ባለቤትና የሕንፃው ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም ቤቱ የተከራየ መሆኑን፣ ከቤቱ ኪራይ በሚገኘው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ያለበትን ሰው (ሰዎች) ስም፣ አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቤቱ ለሚገኝበት ቀበሌ መስተዳድር ማስታወቅ አለባቸው። የቀበሌው መስተዳድርም በራሱ ክትትል ወይም ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት የሚያገኘውን መረጃ ለሚመለከተው የግብር አስገቢ ባለሥልጣን የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

## ክፍል ፬
## የሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ
## የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር

፲፯. በሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ ላይ የሚጣለው ግብር ወሰን

ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ የገቢ ግብር እየተጣለ ይሰበሰባል።

፲፰. ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ተቀባይነት ያገኘውን የሂሳብ አያያዝ መርህ በመከተል የሚዘጋጀውን የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ ወይም የገቢ መግለጫ እና ይህንን አዋጅ እና የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ በእያንዳንዱ የግብር ዘመን ይወሰናል።

፲፱. የግብር መጣኔ

፩. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች ግብር ከሚከፈልበት ገቢያቸው ላይ (፴ ፐርሰንት) ሠላሳ በመቶ ግብር ይከፍላሉ።

፪. በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሌሎች ግብር ከፋዮች በሚያገኙት ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ላይ፣ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር ይከፍላሉ።

(b) sub-lessors shall pay the tax on the difference between income from sub-leasing and the rent paid to the lessor, provided that the amount received from the sub-lessor is greater than the amount payable to the lessor.

(c) the following amounts shall be deducted from income in computing taxable income:

(i) taxes paid with respect to the land and buildings being leased; except income taxes; and

(ii) for taxpayers not maintaining books of account, one fifth (1/5) of the gross income received as rent for buildings furniture and equipment as an allowance for repairs, maintenance and depreciation of such buildings, furniture and equipment;

(iii) for taxpayers maintaining books of account, the expenses incurred in earning, securing, and maintaining rental income, to the extent that the expenses can be proven by the taxpayer and subject to the limitations specified by this Proclamation; deductible expenses include (but are not limited to) the cost of lease (rent) of land, repairs, maintenance, and depreciation of buildings, furniture and equipment in accordance with Article 23 of this Proclamation as well as interest on bank loans, insurance premiums.

2) The owner of a building who allows a lessee to sub-lease is liable for the payment of the tax for which the sub-lessor is liable, in the event the sub-lessor fails to pay.

3) At the earlier of the time construction of a rental building is completed or when the building is rented, the owner and the builder are required to notify the administration of the kebele in which the building is situated about such completion and the name, address, and tax identification number of the person (or persons) subject to tax on income from rental of the building. The kebele administration has the obligation to communicate this information or information obtained by the administrations own initiative to the appropriate tax authority.

## Section IV
## *Schedule 'C' Income/Business Income Tax*

17. *Scope of Schedule 'C' Income*

Income Tax shall be imposed on the taxable business income realized from entrepreneurial activity.

18. *Taxable Business Income*

Taxable business income shall be determined per tax period on the basis of the profit and loss account or income statement, which shall be drawn in compliance with the Generally Accepted Accounting Standards, subject to the provisions of this Proclamation and the directives issued by the Tax Authority.

19. *Tax Rate*

1) Taxable buisness income of bodies is taxable at the rate of 30%.

2) Taxable business income of other taxpayers shall be taxed in accordance with the following Schedule C.

ሠንጠረዥ "ሐ"

| ግብር የሚከፈልበት የዓመቱ የንግድ ሥራ ገቢ | | የሚከፈለው የገቢ ግብር በመቶኛ |
|---|---|---|
| ከብር | እስከ ብር | |
| 0 | 1,800 | ከግብር ነፃ |
| 1,801 | 7,800 | 10 |
| 7,801 | 16,800 | 15 |
| 16,801 | 28,200 | 20 |
| 28,201 | 42,600 | 25 |
| 42,601 | 60,000 | 30 |
| ከ60,000 | በላይ | 35 |

፳· ተቀናሽ ወጪዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ ግብር የሚከፈልበትን ከንግድ ሥራ የሚገኝ ገቢ በሚመለከት በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ሥራው ገቢ ለማግኘት፣ ለንግድ ሥራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ።

፳፩· ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች

፩· የሚከተሉት ወጪዎች ተቀናሽ አይደረጉም፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ መሠረት የእርጅና ቅናሽ የሚደረግለትን የንግድ ሥራውን ሀብት ለማግኘት፣ ለማሻሻል፣ ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረገ ወጪ፣

ለ) የኩባንያውን አክሲዮን ወይም ለተመዘገበ የሽርክና ማኅበር መሠረት የሆነውን ካፒታል ማሳደግ፣

ሐ) ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ፲፭ ፐርሰንት (አሥራ አምስት በመቶ) በላይ የሚደረግ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፣

መ) ባለአክሲዮኖች እንዲያውቁት የተደረገ የአክሲዮን ድርሻ እና የተከፈለ የትርፍ ድርሻ፣

ሠ) በብሔራዊ ባንክና በንግድ ባንኮች መካከል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ መጣኔ ፪ ፐርሰት (ሁለት በመቶ) በላይ የሆነ የወለድ ወጪ፣

ረ) የመድን ዋስትና ሽፋን ያለው ጉዳት፣

ሰ) በጥፋት ምክንያት የተከፈለ የጉዳት ካሣ እና መቀጫ፤

ሸ) በዚህ አዋጅ ከተፈቀደው ውጪ አዲስ መጠባበቂያ ሂሳብ ማቋቋም ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የመጠባበቂያውን መጠን ማሳደግ ወይም ለተለየ ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስቀመጥ፣

ቀ) በሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ ላይ የተከፈለ ግብር፣ ወይም ተመላሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣

በ) የንግድ ድርጅቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለመገኘት የሚደረግ ወጪ፣ ከሠራተኛው ደመወዝ ከ፲ ፐርሰንት የሚበልጥ ከሆነ ፣

ተ) የግል ፍጆታ ወጪዎች፣

ቸ) በዚህ አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚወጣ ደንብ ከተደረገ ገደብ በላይ የተደረገ ወጪ፤

ነ) የመዝናኛ ወጪዎች፣

ኘ) ስጦታ ወይም ዕርዳታ፣

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ኘ) የተመለከተው ቢኖርም፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝብ ጥቅም የሚውል ዕርዳታ ወይም ስጦታ ተቀናሽ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።

፫· ባለአክሲዮኖች ለኩባንያው የሰጡት ብድር እና የቅድሚያ ክፍያ በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ በአማካኝ ከኩባንያው አክሲዮን ካፒታል ዋጋ አራት እጥፍ በላይ ከሆነ ለብድሩ እና ለቅድሚያ ክፍያው የሚከፈለው ወለድ ተቀናሽ አይደረግም። ከዚህ በላይ የተነገረው በባንክ እና በመድን ኩባንያዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።



Schedule 'C'

| Taxable Business Income (per year) | | Income Tax Payable |
|---|---|---|
| Over Birr | to Birr | |
| 0 | 1,800 | exempt threshold |
| 1,801 | 7,800 | 10 |
| 7,801 | 16,800 | 15 |
| 16,801 | 28,200 | 20 |
| 28,201 | 42,600 | 25 |
| 42,601 | 60,000 | 30 |
| Over 60,000 | | 35 |

20. *Deductible Expenses*

In the determination of business income subject to tax in Ethiopia, deductions shall be allowed for expenses incurred for the purpose of earning, securing, and maintaining that business income to the extent that the expenses can be proven by the taxpayer and subject to the limitations specified by this Proclamation.

21. *Non-Deductible Expenses*

1) The following expenses shall not be deductible:
   (a) the cost of the acquisition, improvement, renewal and reconstruction of business assets that are depreciated pursuant to Article 23 of this Proclamation;
   (b) an increase of the share of capital of a company or the basic capital of a registered partnership;
   (c) voluntary pension or provident fund contributions over and above 15% of the monthly salary of the employee.
   (d) declared dividends and paid-out profit shares;
   (e) interest in excess of the rate used between the National Bank of Ethiopia and the commercial banks increased by two (2) percentage points.
   (f) damages covered by insurance policy;
   (g) punitive damages and penalties;
   (h) the creation or increase of reserves, provisions and other special-purpose funds unless otherwise allowed by this Proclamation;
   (i) Income Tax paid on Schedule C income and recoverable Value-Added Tax;
   (j) representation expenses over and above 10% of the salary of the employee;
   (k) personal consumption expenses;
   (l) expenditures exceeding the limits set forth by this Proclamation or Regulations issued hereunder.
   (m) entertainment expenses;
   (n) donation or gift.
2) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) (n) of this Article, the Council of Ministers may by Regulations allow donations or gifts provided for public use to be deducted.
3) Interest paid to shareholders on loans and advances shall not be deductible to the extent that the loan or advances in respect of which the interest paid exceeds on average during the tax period four times the amount of the share capital. This sub-Article does not apply to banks and insurance companies.

፬· ከኩባንያ ውጭ ያሉ ሌሎች ድርጅቶችን በሚመለከት ከዚህ በላይ የአክሲዮን ካፒታል የሚለው ሐረግ መሠረታዊ ካፒታል በሚል የተተካ በሚሆንበት ጊዜ የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

፳፪· <u>በመጋዘን የሚገኝ የንግድ ዕቃ</u>

፩· ግብር ከፋዩ ያገኘው ገቢ በሚሠላበት ጊዜ በግብር ዘመኑ ውስጥ ለተሸጠ በመጋዘን ለሚገኝ የንግድ ዕቃ የተደረገው ወጪ ተቀናሽ ይደረጋል።

፪· በግብር ዓመት ውስጥ ለተሸጡ በመጋዘን የሚገኙ የንግድ ዕቃዎች የተደረገ ወጪ የሚሰላው በአማካኝ የወጪ ስሌት ዘዴ ማለትም በመጋዘን የሚገኘው የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ በአማካኝ ወጪ እንዲሠላ በሚያስችለው አጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ አያያዝ ስሌት መሠረት ነው።

፫· ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "በመጋዘን የሚገኝ የንግድ ዕቃ" ማለት በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ወይም የምርት አካል እንዲሆን የተደረገ የንግድ ሥራ ሀብት ወይም ለሽያጭ የተያዘ ማናቸውም ዕቃ ነው።

፳፫· <u>የእርጅና ቅናሽ</u>

፩· ግብር የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ ገቢ ለመወሰን የንግድ ሥራው ሀብት ባለቤት ለንግድ ሥራው ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ ማድረግ ይችላል።

፪· ሥነ ጥበብ፣ የጥንት ዕቃዎች፣ ከከበሩ ማዕድናት የተሠሩ ጌጣጌጦች እና ሌሎች ዋጋቸው የማይቀንስ እና ጊዜ የማያልፍባቸው የንግድ ሥራ ሀብቶችን በሚመለከት የእርጅና ቅናሽ አይፈቀድም።

፫· የሕንፃ ወይም የሌሎች ግንባታዎች ባለቤት ለመሆን፣ ሕንፃ ወይም ሌሎች ግንባታዎችን ለማሻሻል፣ ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረጉ ወጪዎች ለእያንዳንዱ በተናጠል በቀጥተኛ የእርጅና አቀናነስ ዘዴ መሠረት ፭ ፐርሰንት የእርጅና ቅናሽ ይደረጋል።

፬· ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው ሀብቶች ባለቤት ለመሆን ወይም እነዚህን ሀብቶች ለማሻሻል፣ ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረጉ ወጪዎች ለእያንዳንዱ በተናጠል በቀጥተኛ የእርጅና አቀናነስ ዘዴ መሠረት ፲ ፐርሰንት የእርጅና ቅናሽ ይደረጋል።

፭· ከዚህ በታች በሁለት ምድብ የተመለከቱ የንግድ ሥራ ሀብቶች በጥቅል የእርጅና አቀናነስ ሥርዓት መሠረት ቀጥሎ በተመለከተው መጣኔ የእርጅና ቅናሽ ይደረግላቸዋል፤

ሀ) ኮምፒውተሮች፣ የመረጃ ሥርዓቶች፣ የሶፍትዌር ውጤቶች እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያዎች ፳፭ ፐርሰንት

ለ) ሌሎች ማናቸውም የንግድ ሥራ ሀብቶች .... ፳ ፐርሰንት

፮· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፭) ለተመለከተው ለእያንዳንዱ ምድብ የተወሰነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በየምድቡ ለእርጅናው ቅናሽ መሠረት በሆነው ሂሳብ ላይ ተፈፃሚ ይደረጋል።

፯· የእርጅናው ቅናሽ መሠረት በታክስ ዘመን መጀመሪያ የመነሻ ሂሣብ ሚዛን ላይ የተመዘገበው የመዝገብ ዋጋ ሲሆን፣ በዚህ ሂሳብ ላይ፤

ሀ) በየምድቡ ያሉ ሀብቶች ባለቤት ለመሆን ወይም አዳዲስ ሀብቶችን ለመመሥረት ወይም እነዚህን ሀብቶች ለማሻሻል፣ ለማደስ፣ መልሶ ለመገንባት በታክስ ዘመኑ የተደረገ ወጪ ተጨምሮ፣

ለ) በታክስ ዘመኑ የተወገዱ ዕቃዎች የሽያጭ ዋጋ፣ በተፈጥሮ አደጋ ለወደሙ ወይም በሌላ ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ለውጥ ላጋጠማቸው ሀብቶች የተገኘ ካሣ ተቀንሶ፣ ይሆናል።

፰· የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ከዜሮ በታች ከሆነ፣ ከዜሮ በታች የሆነው መጠን ግብር ከሚከፈልበት ትርፍ ላይ ተደምሮ የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ዜሮ ይደረጋል።

፱· የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ከብር ፩ሺ የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ይህ መጠን በአንድ ጊዜ ከንግድ ሥራው ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።

፲· የንግድ ሥራው ሀብት እንደገና እንዲገመት ተደርጐ ተጨማሪ እሴት የተገኘ እንደሆነ፣ ተጨማሪው እሴት የእርጅና ቅናሽ መሠረት ሆኖ አይወሰድም።

፲፩· ግብር የሚከፈልበትን ከንግድ ሥራው ንብረት የተደረገ የጥገና እና የማሻሻያ ትክክለኛ ወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል። ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚቀነሰው ወጪ መጠን ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ንብረት የእርጅና ቅናሽ መሠረት ከሆነው ሂሣብ ፳ ፐርሰንት ሊበልጥ አይችልም። ከ፳ ፐርሰንት በላይ የሆነውን ትክክለኛ ወጪ የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ከፍ ለማድረግ ይውላል።

4) In the case of bodies other than companies, Sub-Article (3) above shall apply as if for the reference to share capital there were substituted a reference to basic capital.

22. *Trading Stock*

1) For the purposes of ascertaining the income of a person for a tax period from a business, there shall be deducted the cost of trading stock of the business disposed of by that person during that period.
2) The cost of trading stcok disposed of during a tax period is determined on the basis of the average-cost method, i.e. the generally accepted accounting principle under which trading stock valuation is based on an average cost of units on hand.
3) The term "trading stock' means any business asset that is either used in the production process and becomes part of the product, or that is hold for sale.

23. *Depreciation*

1) In the determination of taxable business income, the owner of the business assets may deduct depreciation for business assets.
2) Fine art, antiques, jewelry, trading stock and other business assets not subject to wear and tear and obsolescence shall not be depreciated.
3) The acquistion or construction cost, and the cost of improvement, renewal and reconstruction, of buildings and constructions shall be depreciated individually on a straight-line basis at five per cent (5%).
4) The acquisition or construction cost, and the cost of improvement, renewal and reconstruction, of intangible assets shall be depreciated individually on a straight-line basis at ten percent (10%).
5) The following two categories of business assets shall be depreciated according to a pooling system at the following rates:
   (a) Computers, information systems, software products and data storage equipment: twenty-five (25%).
   (b) All other business assets: twenty percent (20%).
6) In each category as referred to in Sub-Article (5), the rate of depreciation specified in that Sub-Article shall be applied to the depreciation base of the category.
7) The depreciation base shall be the book value of the category as recorded in the opening balance sheet of the tax period:
   (a) increased by the cost of assets acquired or created and the cost of improvement, renewal and reconstruction of assets in the category during the tax period.
   (b) decreased by the sales price of assets disposed of and the compensation received for the loss of assets due to natural calamities or other involuntary conversion during the tax period.
8) If the depreciation base is a negative amount, that amount shall be added to taxable profit and the depreciation base shall become zero.
9) If the depreciation base does not exceed Birr 1,000 the entire depreciation base shall be a deductible business expense.
10) If a revaluation of business assets takes place, no depreciation shall be allowed for the amount of the revaluation.
11) In determination of taxable business income a deduction is permitted in respect of each category of business assets for the maintenance and improvement expenses of business assets belonging to that category for the acutal amount of the expenses, but not in excess of twenty percent (20%) of the deprciation base of the category at the end of the year. Any actual expenses exceeding this twenty percent (20%) shall increase the depreciation base of that category.

፳፬ የንግድ ሥራ ንብረት ዝውውር

፩· በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ንብረት የተሸጠ፣ የተለወጠ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተላለፈ እንደሆነ፣ በእንዲህ ዓይነቱ ዝውውር የተገኘ ጥቅም ወይም ኪሣራ ከግምት ውስጥ የሚገባ ይሆናል።

፪· እንደገና የመደራጀት ሂደት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ኩባንያዎች የንግድ ሥራ ንብረት ከአንዱ ወደሌላው መተላለፍ ንብረቱ እንደተሸጠ አያስቆጥርም።

፫· እንደገና የመደራጀት ሂደት ተፈፃሚ የሆነበት/ የሆነ ባቸው ኩባንያ/ ኩባንያዎች የንግድ ሥራ ንብረት እሴት እንደገና የመደራጀቱ ሂደት ከመፈፀሙ በፊት ከነበረው የንብረቱ እሴት ጋር አንድ ይሆናል። በመሆኑም ቀሪው የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ እንደገና በመደራጀት ወደተፈ ጠረው ኩባንያ ይዘዋወራል።

፬· "እንደገና መደራጀት" ማለት፣

ሀ) ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ የሆነ የሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ኩባንያዎች መዋሀድ፣

ለ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነውን ኩባንያ ድምፅ የሚያስጥ አክሲዮን ዋጋ (፶ ፐርሰንት) ሃምሳ በመቶ ወይም የሌሎች ጠቅላላ አክሲዮኖችን ዋጋ ሃምሳ በመቶ እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ አባል የሆነ ድርጅት በሚያገኘው አክሲዮን ለውጥ ብቻ የተሸጠ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተላለፈ እንደሆነ፣

ሐ) እንደገና በሚደራጀው ኩባንያ ውስጥ አባል ለሆነ ኩባንያ በአክሲዮን ድርሻ ክፍያ ረገድ ልዩ መብት በማያስጥና የድምፅ ተሳትፎ ብቻ በሚያስገኝ አኳኋን፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ ከሆነ ኩባንያ ሀብት ውስጥ (፶ ፐርሰንት) ሃምሳ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ለሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የተሰጠ ወይም የተላለፈ እንደሆነ፣

መ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወደሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ ኩባንያዎች መከፋፈል፣

ሠ) አንድ የንግድ ሥራ ድርጅት የተቀፅላዎቹን ካፒታል፣ የድርጅቱን ካፒታል ለያዙ ሲያከፋፍል ነው።

የዚህ ዓይነቱ እንደገና መደራጀት ማለትም ውህደት፣ በሌላ መያዝ፣ መተላለፍ፣ መከፋፈል ወይም የተቀጽላዎች ካፒታል የዋናውን የንግድ ሥራ ኩባንያ ካፒታል ወደያዙ መሸጋገር ዋንኛ ዓላማ የታክስ ከለላ ለማግኘት ያለመሆኑን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማረጋገጥ አለበት።

፭· ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ ፩–፬ የተደነገገው በአንቀጽ ፳፫(፭) የተመለከተውን የንብረት ዝውውር በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆንም።

፮· ለኪሣራ ዕውቅናን ስለመስጠት የተነገረው በአንቀጽ ፪(፬) መሠረት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደ ረግን የንግድ ሥራ ንብረት ዝውውር አይመለከትም።

፳፭· የማይሰበሰብ ዕዳ

ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ግብር የሚከፈ ልበት የንግድ ሥራ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ የማይሰበሰቡ ዕዳዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ።

ሀ) ከማይሰበሰበው ዕዳ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ሂሳብ ቀደም ሲል በንግድ ሥራው ገቢነት ተይዞ ከሆነ፣ እና፣

ለ) ዕዳው ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ የተሠረዘ ከሆነ፣ እና

ሐ) ዕዳውን ለማስመለስ ተገቢው የሕግ እርምጃ ተወስዶ ገቢ ለማድረግ ያለመቻሉ የተረጋገጠ ከሆነ።

፳፮· ለፋይናንስ ድርጅቶች የተፈቀደ ልዩ መጠባበቂያ

ግብር የሚከፈልበት የፋይናንስ ድርጅቶች የንግድ ሥራ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጣ መመሪያ የተፈቀዱ ልዩ (የቴክኒክ) መጠባበቂያዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ። ሆኖም ግብር የሚከፈልበት የፋይናንስ ድርጅቶች የንግድ ሥራ ገቢ ከልዩ መጠባበቂያው ሂሳብ ወጪ በተደረገው መጠን ከፍ እንዲል ይደረጋል።

፳፯· ተቀናሽ የሚደረግ የካፒታል ተሳትፎ

፩· ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ያገኘውን ትርፍ የሌላን ኩባንያ ወይም የሽርክና ማኅበር ካፒታል ለማሳደግ ያዋለው ከሆነ ለዚህ ዓላማ የዋለው ትርፍ ግብር ከሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።

24. *Transfers of Business Assets*

1) *When assets used in a business are sold, exchanged, or otherwise transferred, gain or loss is recognized on the transfer.*
2) *Transfers of business assets among companies which are parties to a reorganization are not treated as a disposal of the property.*
3) *The value of business assets held by a company or companies which are parties to a reorganization is the same as the value of such assets immediately before the reorganization. Similarly, the balance value of any depreciation categories shall be carried over.*
4) *"reorganization" means:*
   - (a) *a merger of two or more resident companies;*
   - (b) *the acquisition or takeover of fifty percent (50%) or more of the voting shares and fifty percent (50%) or more of all other shares by value of a resident company solely in exchange for shares of a party to the reorganization;*
   - (c) *the acquisition of fifty percent (50%) or more of the assets of a resident company by another resident company solely in exchange for voting participations with no preferential rights as to dividends of a party to the reorganization;*
   - (d) *a division of a resident company into or more resident companies; or*
   - (e) *a spin-off*

   *The Tax Authority shall ensure that the merger, acquisition, takeover, division, or spin-off is not having tax avoidance as a principal objective.*
5) *The rules of Sub-Article (1) – (4) shall not apply to the transfer of assets described under Article 23(5).*
6) *Loss shall not be recognized on the transfer of a business asset to related person within the meaning of Article 2(4).*

25. *Bad Debts*

In the determination of taxable business income, a deduction shall be allowed for a bad debt if the following conditions are met:

(a) an amount corresponding to this debt was previously included in the income;

(b) the debt is written off in the books of the taxpayer; and

(c) any legal action to collect the debt has been taken but the debt is not recoverable.

26. *Special Reserves for Finance Institutions*

In the determination of taxable business income of finance institutions a deduction shall be allowed for special (technical) reserves in accordance with the directives issued by the National Bank of Ethiopia; the business income, however, shall be increased by amounts drawn from such reserves.

27. *Participation Deduction*

1) If a resident company or partnership reinvests the profit it earned to raise the capital of another company or partnership subject to the conditions in Sub-Article (2) and (3); such amount shall be deductible from its taxable income.

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) የተመለከተው ተቀናሽ አክሲዮንን በሚመለከት ተፈፃሚ የሚሆነው አክሲዮን የተገዛባት ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ እና በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን እና አክሲዮኑን የገዛው ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር በኩባንያው ውስጥ በቁጥር ወይም በዋጋ ቢያንስ ፳፭ ፐርሰንት የአክሲዮን ካፒታል የያዘ ወይም በዚሁ መቶኛ መጠን ድምፅ የመስጠት መብት ያለው ከሆነ ነው።

፫· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) የተመለከተው ተቀናሽ የትርፍ ድርሻን በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆነው የካፒታል መዋጮ የተደረገበት የሽርክና ማኅበር በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ እና በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሲሆን እና የካፒታሉን መዋጮ ያደረገው ኩባንያ ወይም የተመ ዘገበ የሽርክና ማኅበር፣ የሽርክና ማኅበሩ መሠረት ከሆነው ካፒታል ዋጋ ውስጥ ቢያንስ ፳፭ ፐርሰንት የያዘ እንደሆነ ነው።

፬· በዚህ አንቀጽ የተፈቀደው ማበረታቻ ተፈፃሚ የሚሆ ንበት ዝርዝር ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል።

፳፰· ኪሣራን ስለማሸጋገር

፩· በአንድ የግብር ዘመን ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወ ሰንበት ጊዜ በዚያው የግብር ዘመን ውስጥ የታየው ኪሣራ በሚቀጥሉት ሦስት (፫) የግብር ዘመናት ከተገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ የሚካካስ ይሆናል። ይህም የሚፈፀመው በመጀመሪያ ያጋጠ መውን ኪሣራ በኋላ ካጋጠመው ኪሣራ አስቀድሞ በማካካስ ነው።

፪· በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ የአንድ ኩባንያ የካፒታል ባለቤትነት ወይም ድምፅ የመስጠት መብት በዋጋ ወይም በቁጥር ከ፳፭ ፐርሰንት በላይ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተለወጠ እንደሆነ ኩባንያው በዚያው የግብር ዘመንም ሆነ ቀደም ባሉ የግብር ዓመታት የደረሰበትን ኪሣራ በሚመለከት የንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ተፈፃሚነት ያቋርጣል።

፫· ማናቸውም ሰው በንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ያጋጠመው ኪሣራ በማናቸውም ሁኔታ በሁለት የሦስት ዓመታት ጊዜ ከሚቆጠሩ ፮ ዓመታት በላይ ሊሸጋገርና ተቀናሽ ሊሆን አይችልም።

፳፱· የማስተላለፊያ ዋጋ

፩· በሁለት በተለያዩ ሰዎች መካከል ከሚደረገው የንግድ ወይም የፋይናንስ ግንኙነት፣ የተሳሰሩ ሰዎች የንግድ ወይም የፋይናንስ ግንኙነት የተለየ እንዲሆን የሚያ ደርግ ወይም የሚያስገድድ ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ፣ የግብሩ ባለሥልጣን ከተሳሰሩት ሰዎች መካከል የአንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑት ገቢ የዚህ ዓይነቱ ትስስር ባይኖር ኖሮ ሊያስገኝ የሚችለውን ትርፍ እንዲጨምር ሊወስን ይችላል። የግብሩ ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት የሚወስነው ከሚኒ ስትሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ይሆናል።

፪· ለዚህ አንቀጽ ትክክለኛ እና ውጤታማ አፈፃፀም እንዲያመች በተሳሰሩ ሰዎች መካከል የሚደረገው ግንኙነት በሁለት በተለያዩ ሰዎች መካከል ከሚደ ረገው ግንኙነት የተለየ እንዳይሆን የሚያስችል እንደአ ስፈላጊነቱ ሁኔታዎች የተካተቱበት፣ ስምምነት የግብሩ ባለሥልጣን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከሚያከ ናውኑ ሰዎች ጋር አስቀድሞ ሊያደርግ ይችላል።

፴· ከግብር ነፃ ስለማድረግ

፩· የሚከተሉት ገቢዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል ባቸው ከሚገባው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ነፃ ናቸው፤
  ሀ) አንድን ቴክኖሎጂ ለተወሰነ ሁኔታ እንዲስማማ በማድረግ ወይም አዲስ የፈጠራ ሀሳብ በማቅረብ እና ወጪን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሠራሮችን ሥራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት፣
  ለ) በማናቸውም መስክ የላቀ ተግባር ላከናወኑ ሰዎች የሚሰጥ ሽልማት፣
  ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ ፀንቶ በሚሠራበት ሕግ፣ በዓለም ዐቀፍ ስምምነት፣ ወይም ሚኒስትሩ በሚያደርገው ወይም በሚፈቅደው ስምምነት መሠረት በተለይ ግብር እንዳይከፈልበት የተደረገ ገቢ፤

፪· የሚከተሉት በሥራቸው አጋጣሚ የሚያገኙት ገቢ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ከሚከፈል ግብር ነፃ ይሆናል፡



2) The deduction mentioned in letter (a) of Sub-Article (1) shall apply to shares of resident companies that are subject to taxation under Scdedule C and in which the investing body has a shareholding of at least twenty-five percent (25%), by value or by number, in the share capital or the voting rights.

3) The deduction mentioned in letter (b) of Sub-Article (1) shall apply to basic capital of resident registered partnerships that are subject to taxation under Schedule C and in which the investing body holds at least twenty-five percent (25%) by value of basic capital.

4) The Council of Ministers shall by regulations determine the manner in which the incentive granted in this Article shall be applied.

28. *Loss Carry forward*

1) If the determination of taxable business income results in a loss in a tax period, that loss may be set off against taxable income in the next five (5) tax periods, earlier losses being set off before later losses.

2) If during a tax period the direct or indirect ownership of the share capital or the voting rights of a body changes more than twenty-five percent (25%), by value or by number, Sub-Article (1) shall cease to apply to losses incurred by that body in that tax period and previous tax periods.

3) A net operating loss may be carried forward and deducted only for two periods of three years.

29. *Transfer Pricing*

1) Where conditions are made or imposed between persons carrying on business in their commercial or financial relations which differ from those which would be made between independent persons, the Tax Authority may direct that the income of one or more of those related persons is to include profits which he or they would have made but for those conditions. The Tax Authority shall do so in accordance with the directives to be issued by the Minister.

2) In order to ensure the just and efficient application of this Article the Tax Authority may make agreements in advance with persons carrying on entrepreneurial activities, subject to conditions if necessary, that specified conditions between related persons do not differ from those which would be made between independent persons.

30. *Exemptions*

1) The following categories of income shall be exempt from payment of business income tax hereunder:
   (a) awards for adopted or suggested innovations and cost saving measures, and
   (b) public awards for outstanding performance tax any field.
   (c) income specifically exempted from income tax by the law in force in Ethiopia, by international treaty or by an agreement made or approved by the Minister.

2) The revenue obtained by:

ሀ) የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የመንግሥት መ/ቤቶች፣
ለ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ።

ክፍል ፭

የሠንጠረዥ "መ" ገቢ/ ሌሎች ገቢዎች

፴፩· የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ

፩· በማንኛውም የፈጠራ መብትን በማከራየት በተገኘ ገቢ ላይ አምስት በመቶ (አምስት በመቶ) ግብር ይከፈልበታል።

፪· ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠቀሰውን ግብር ቀንሶ በመያዝ ለግብር አስገቢው መ/ቤት የማስታወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት ።

፫· ከፋዩ ነዋሪነቱ በውጭ አገር ሆኖ ተቀባዩ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ እንደሆነ ፣ ተቀባዩ በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፈጠራ መብት በማከራየት ጥገኘው ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር ይከፍላል ።

፬· በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ታክስ ከዚህ እንቅስቃሴ የተገኘውን ገቢ በሚመለከት የመጨረሻ ይሆናል ።

፭· በዚህ አዋጅ ውስጥ "የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ" ማለት ተንቀሳቃሽ ፊልም እና ለሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት የሚውል የተንቀሳቃሽ ፊልም ወይም የድምፅ ክሮችን ፣ ማናቸውም በአንድ ሰው መብት ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድ ፣ የንግድ ምልክት ፣ ንድፍ ወይም ሞዴል ፣ ፕላን ፣ በሚስጥር የተያዘ ፎርሙላ ወይም የአመራረት ሂደት ፣ ወይም የማናቸውንም የኢንዱስትሪ ፣ የንግድ ወይም የሣይንስ መሣሪያ ወይም በኢንዱስትሪ ፣ በንግድ ወይም በሣይንስ ከተገኘ ልምድ የተሰባሰበ መረጃን መጠቀምን ወይም የመጠቀም መብትን ጨምሮ ማናቸውንም የሥነ–ጽሑፍ፣ የኪነጥበብ ወይም የሣይንስ ሥራ ልዩ መብትን መጠቀምን ወይም የመጠቀም መብትን ለጥቅም በማከራየት ምክንያት የሚገኝ ማናቸውም ክፍያ ነው ።

፴፪· የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት የሚገኝ ገቢ፣

፩· በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ሰዎች ከኢትዮጵያ ውጪ ለተሰጠ የቴክኒክ አገልግሎት የተፈፀመ ክፍያ ፲ ፐርሰንት (አሥር በመቶ) ብር ይከፈልበታል ። ይህንንም ግብር አገልግሎት የተፈፀመለት ከፋይ እየቀነሰ በማስቀረት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ገቢ ማድረግ አለበት።

፪· "የቴክኒክ አገልግሎት" ማለት ማናቸውም የባለሙያ ምክር ወይም የቴክኖሎጂ አገልግሎት ነው ።

፴፫· ከዕድል ሙከራ የሚገኝ ገቢ፣

፩· በዕድል ሙከራ ውድድር አሸናፊ በመሆን (ለምሳሌ ከሎተሪ ፣ ከቶምቦላ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች) ገቢ የሚያገኝ ማናቸውም ሰው ከብር ፩፻ በላይ በሆነው ገቢ ላይ ፲፭ ፐርሰንት (አሥራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፍላል።

፪· ከፋዩ በአንቀጽ ፷፯ በተመለከተው መሠረት ግብሩን ቀንሶ በማስቀረት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ።

፫· በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ከዚህ እንቅስቃሴ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ታክስ ይሆናል።

፴፬· የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ

፩· የአክሲዮን ማኅበር ካከፋፈለው የአክሲዮን ድርሻ ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከሚያከፋፍለው ትርፍ ገቢ የሚያገኝ ማናቸውም ሰው ባገኘው ገቢ ላይ ፲ ፐርሰንት (አሥር በመቶ) ግብር ይከፍላል።

፪· ከፋዩ ግብሩን ቀንሶ በማስቀረት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።

፫· በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ከዚህ እንቅስቃሴ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ታክስ ይሆናል።

፴፭· ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ከተመለከተው ግብር ከሚከፈልበት የንግድ እንቅስቃሴ ጋር በማይገናኝ አኳኋን ንብረት አልፎ አልፎ በማከራየት ገቢ ያገኘ ማናቸውም ሰው ፣ ባገኘው የዓመት ጠቅላላ ገቢ ላይ ፲፭ ፐርሰንት (አሥራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፍላል። በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር የመጨረሻ ይሆናል።



(a) the Federal, Regional and Local Governments of Ethiopia;
(b) the National Bank of Ethiopia.

from activities that are incidental to their operations shall be exempt from tax on Schedule C income.

*SECTION V*

*Scheduled Income/Other Income*

31. *Royalties*

1) Royalties shall be liable to tax at a flat rate of five percent (5%).
2) The withholding Agent who effects payment shall withhold the foregoing tax and account to the Tax Authority within the time limit set out in this Proclamation.
3) Where the payer resides abroad and the recipient is a resident, the recipient shall pay tax on the royalty income within the time limit set out in this Proclamation.
4) This tax is a final tax in lieu of a net income tax.
5) The term "roayalty" means a payment of any kind received as a consideration for the use of, or the right to use, any copyright of literary, artistic or scientific work, including cinematography films, and films or tapes for radio or television broadcasting, any patent, tradework, design or model, plan, secret formula or process, or for the use or for the right to use of any industrial, commercial or scientific equipment, or for information concerning industrial, commercial or scientific experience.

32. *Income from Rendering of Technical Services*

1) All payments made in consideration of any kind of technical services rendered outside Ethiopia to resident persons in any form shall be liable to tax at a flat rate of ten percent (10%) which shall be withheld and paid to the Tax Authority by the payer.
2) The term "technical service" means any kind of expert advise or technological service rendered.

33. *Income from Games of Chance*

1) Every person derving income from winning at games of chance (for example, lotteries, tombolas, and other similar activities) shall be subject to tax at the rate of fifteen percent (15%), except for winnings of less than 100 Birr.
2) The payer shall withhold or collect the tax and account to the Tax Authority in the manner provided in Article 67.
3) This tax is a final tax in lieu of income tax.

34. *Dividends*

1) Every person deriving income from dividends from a share company or withdrawals of profits from a private limited company shall be subject to tax at the rate of ten percent (10%).
2) The withholding Agent shall withhold or collect the tax and account to the Tax Authority.
3) This tax is a final tax in lieu of income tax.

35. *Income From Rental of Property*

Every person derving income from the casual rental of property (including any land, building, or moveable asset) not related to a business activity taxable under Article 17 shall pay tax on the annual gross income at the rate of fifteen percent (15%). This tax is a final tax in lieu of a net income tax.

፴፮· በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈል የወለድ ገቢ

፩· ማናቸውም ሰው ከተቀማጭ ገንዘብ በሚያገኘው ወለድ ላይ አምስት በመቶ (፭ ፐርሰንት) ግብር ይከፍላል ።

፪· ከፋዩ ግብሩን ቀንሶ በማስቀረት በአንቀጽ ፷፯ በተደነገገው መሠረት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ።

፫· በዚህ ዓይነት የተከፈለው ግብር ከወለድ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ የመጨረሻ ግብር ይሆናል ።

፴፯· የተወሰኑ የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም

፩· በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩ ንብረቶችን በስጦታ ወይም በሽያጭ በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ከዚህ በታች በተመለከተው የማስከፈያ ልክ ግብር የሚከፈልበት ይሆናል ።

ሀ) ለንግድ፣ ለፋብሪካ፣ ለቢሮ የተያዙ ሕንፃዎች ፲፭ ፐርሰንት (አሥራ አምስት በመቶ)፣

ለ) የኩባንያዎች አክሲዮን ፴ ፐርሰንት (ሠላሳ በመቶ)፣

፪· በግል መኖሪያነት የተያዘ ቤት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ግብር አይከፈልበትም ።

፫· በዚህ አንቀጽ ግብር ከተጣለባቸው ንብረቶች የተገኘውን ጥቅም ለማስላት የሚያስችለው ዘዴ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ።

፬· በአንቀጽ ፳፬(፬) በተመለከተው መሠረት በሚከናወን እንደገና የመደራጀት ሂደት በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ ኩባንያ ውስጥ የሚደረግ ማናቸውም የአክሲዮን መተላለፍ ፣ በዚሁ የመደራጀት ሂደት ተሳታፊ ለሆነ ለሌላ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆነ ኩባንያ የሚደረግ የአክሲዮን ልዋጭ ከሆነ አክሲዮን እንደተሸጠ አይቆጠርም ።

፭· በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በልዋጭ የተሰጠው አክሲዮን ዋጋ የመጀመሪያው አክሲዮን ዋጋ ይሆናል።

፮· ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እንደዚህ ያሉ ንብረቶችን በማስተላለፍ ሂደት የሚደርስ ኪሣራ ዕውቅና ተሰጥቶት ከተገኘ ጥቅም ጋር እንዲካካስ ይደረጋል ።

ሀ) በዚህ አንቀጽ መሠረት በተደረገ የካፒታል ንብረት መተላለፍ ያጋጠመ ኪሣራ በዚሁ አንቀጽ መሠረት በተደረገ የንብረት መተላለፍ በተገኘ ጥቅም ላይ እንጂ በማናቸውም ሌላ አኳኋን በተገኘ ገቢ ወይም ጥቅም ጋር እንዲካካስ አይደረግም ። ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ያልተካካሰ ኪሣራ ላልተወሰነ ጊዜ ወደፊት ሊሸጋገር ይችላል ።

ለ) በአንቀጽ ፪(፬) ግንኙነት ላላቸው ሰዎች በተሰጠው ትርጉም የሚሸፈኑ ድርጅቶች በመካከላቸው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚያጋጥማቸው ኪሣራ እንደሚካካስ ኪሣራ ተደርጐ አይወሰድም ።

፯· ማናቸውም በዚህ አንቀጽ ግብር የተጣለበትን የካፒታል ንብረት ዝውውር የመቀበል ወይም የመመዝገብ ወይም በማናቸውም መንገድ የማፅደቅ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ግብሩ መከፈሉን ሳያረጋግጥ ዝውውሩን አይቀበልም ፣ አይመዘግብም ፣ አያፀድቅም።

ምዕራፍ ፪

የአፈፃፀም ድንጋጌዎች

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፴፰· የግብር አስገቢ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር፤

፩· ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈጸም ኃላፊነት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ይሆናል ።

፪· በማንኛውም በሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ በግብር ከፋይ የቀረቡ ማንኛቸውንም መግለጫዎች ፣ ሠነዶችና የሂሣብ መዝገቦች ለማረጋገጥ፣

ሀ) ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸው ተቆጣጣሪዎችን ወደ ግብር ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ቦታ በመላክ ገቢና ወጭን የሚያሳዩ ሠነዶችን ፣ ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን ፣ ሌሎች ዕቃዎችን ወይም የሂሣብ መዛግብትንና ሠነዶችን ለማመሳከርና ለመመርመር ፣

36. *Interest Income on Deposits*

1) Every person deriving income from interest on deposits shall pay tax at the rate of five percent (5%).
2) The payer shall withhold the tax and account to the Tax Authority in the manner provided in Article 67.
3) This tax is a final tax in lieu of income tax.

37. *Gain on Transfer of Certain Investment Property*

1) Income Tax shall be payable on gains obtained from the transfer (sale or gift) of property described in this Article at the following rates:
   (a) building held for business, factory, office 15% (fifteen percent)
   (b) shares of companies 30% (thirty percent)
2) Gains obtained from the transfer of building held for residence shall be exempt.
3) The basis for computation of gains obtained from the transfer of properties described in this Article shall be determined by Regulations to be issued by the Council of Ministers.
4) Any exchange of shares in a resident company which is a party to a reorganization – as defined in Article 24(4) – in exchange for share in another resident company which is also a party is not a disposal of the shares.
5) The value of the shares given in exchange under Sub-Article (4) shall be equal to the value of the original shares.
6) Loss on the transfer of such property shall be recognized and be available to offset gain subject to the following limitations:
   (a) Loss on transfers under this Article may be used to offset gain on transfers under this Article, but may not be used to offset any other income or gain. Unused losses may be carried forward indefinitely.
   (b) No loss shall be recognized on transfer to associates within the meaning of Article 2(4).
7) Any person authorized by law to accept, register or in any way approve the transfer of capital assets shall not accept, register or approve the transfer before ascertainig that the payment of the tax has been duly effected in accordance with this Article.

CHAPTER II

*Procedural Provisions*

*Section 1*

*General Provisions*

38. *Powers And Duties of Tax Authority*

1) The implementation and enforcement of this Proclamation and of Regulations issued hereunder shall be the duty of the Tax Authority.
2) Notwithstanding anything to the contrary in any other law, the Tax Authority shall be empowered to investigate any statements, records and books of account submitted by any taxpayer at any time by:
   (a) sendiñg duly accredited inspectors to the place of business or practice of the tax payer to check same or any vouchers, stocks of other material items of the taxpayer;

ለ) ግብር ከፋዩን ወይም የሒሣብ መዝገቦችን እና ሠነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይም እነዚህኑ የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የግብር ከፋዩን ተቀጣሪ በአመቺ የግብር አስገቢ መሥሪያ ቤት የሥራ ሰዓቶች እና ጽ/ቤት ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሠነዶች እንዲያቀርብ ለማድረግ፤

ሐ) ማዘጋጃ ቤት ፣ ድርጅት ፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛውንም የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል መሥሪያ ቤት ፣ ጨምሮ ማናቸውም ሰው ስለግብር ከፋይ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም የመበደር ወይም የማበደር ግንኙነቶችን ዝርዝር እንዲገልጽ ለማድረግ ይችላል ።

፴፱· መረጃዎችን በሚስጥር ስለመጠበቅ

፩· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ፣ የባለሥልጣኑ ወኪል ሆነው የሚሠሩ ወይም ወኪል የነበሩ ወይም ተቀጣሪዎች ወይም ተቀጣሪ የነበሩ ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር በሥራቸው አጋጣሚ ያወቋቸቸውን አንድን ግብር ከፋይ የሚመለከቱ ሌሎች መረጃዎች ለማንም አሳልፈው ሳይሰጡ በሚስጥር መጠበቅ አለባቸው ። ከዚህ በላይ የተደነገገው ቢኖርም እንዲህ ያሉትን መረጃዎች ለሚከተሉት መግለጽ ይችላሉ፤

ሀ) ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ፣ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ተቀጣሪዎች ፣

ለ) የግብር ሕጉን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመውን ሰው ለፍርድ ለማቅረብ ፣ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት ፣

ሐ) የግብር ዕዳ ፣ መቀጫ ወይም ወለድ ወይም ማናቸውንም ሌላ የወንጀል ጉዳዮች በማየት ላይ ላለ ፍ/ቤት ፣

መ) ኢትዮጵያ ፈራሚ በሆነችበት ዓለም ዓቀፍ ስምምነት መሠረት ሲጠየቅ ለውጭ አገር የግብር ባለሥልጣናት።

፪· በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መረጃ በእጃቸው የገባ ሰዎች፣ መረጃው እንዲሰጣቸው ያደረገውን ምክንያት ማስፈፀም በሚያስችል አነስተኛ መጠን ካልሆነ በስተቀር እንዲህ ያለውን መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። በዚህ ክፍል ሚስጥርነታቸው እንዲጠበቅ የተደረጉ መረጃዎች የደረሷቸው ሌሎች ሰዎች እነዚህን መረጃዎች ለማንም ሌላ ሰው ተላልፈው እንዲሰጡ ማድረግ አይኖርባቸውም ። እነዚህን መረጃዎች የያዙ ሠነዶችን ወዲያውኑ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መመለስ አለባቸው ።

፫· አንድን ግብር ከፋይ የሚመለከቱ መረጃዎች ከዚህ ውጭ ለሆኑ ሌሎች ሰዎች እንዲሰጡ ማድረግ የሚቻለው የግብር ከፋዩ ስምምነት በጽሑፍ ሲገኝ ብቻ ይሆናል ።

፵· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች የሚመሩበት የሥነ–ምግባር ደንብ

፩· እያንዳንዱ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ፡–

ሀ) ታማኝ እና ትክክለኛ ፣ ግብር ከፋዩን በትህትናና በአክብሮት የሚቀበል ፣

ለ) ሕጎችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን የጉዳዩ ፍሬ ነገር በሚመራው መሠረት ሥራ ላይ ማዋል ፣ ለዘመዶቹ ወይም ለወዳጆቹ ልዩ አስተያየት ወይም አድልዎ ያለማድረግ ፣

ሐ) የራሱን እና የባለቤቱን የግብር ዕዳ በሚመለከት ውጤት ሊያስከትል በሚችል ውሣኔ ላይ ያለመሳተፍ ፣

መ) የሚታወቅ የቤተሰብ ዝምድና ወይም የንግድ ሥራ ጥቅም በተቀጣሪነቱ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ከሆነ ፣ እንዲህ ያለውን የዝምድና ግንኙነት ወይም ጥቅም ይፋ ማድረግ (አግባብ ባለው ሕግ በተወሰነው መሠረት) ፣

ሠ) በአንቀጽ ፴፱ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውንም የግብር ፣ የታክስ ወይም የቀረጥ መረጃ በሚስጥር መጠበቅ ፣

ረ) ማናቸውንም መደለያ አለመጠየቅ ፣ ያለመቀበል ወይም ማናቸውንም ግብርን ከመወሰን ወይም ከመሰብሰብ ተግባሩ ጋር የሚጋጩ ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ተግባሮችን ያለመፈጸም ፤

(b) requiring the taxpayer or any employee thereof who has access to or custody of any information, records or books of account to produce the same and to attend during normal office hours at any reasonably convenient tax office and answer any questions relating thereof;

(c) requiring any person including municipality, Body, Financial Institution Department or Agency of Federal or Regional Government to disclose particulars of any information or transactions, including any lending or borrowing which it may have relating to the taxpayer.

39. *Confidentiality of Tax Information*

1) The Tax Authority and all persons who are or have been its agents or employees shall maintain the secrecy of all information except such information as are required by the Commercial Code of Ethiopia to be published by trade gazette, on particular taxpayers received by them in an official capacity, and may disclose such information only to the following persons:

(a) employees of the Tax Authority, for the purpose of carrying out their official duties;

(b) law enforcement agencies, for the purpose of the prosecution of a person for tax violations;

(c) courts, in proceedings to establish a person's liability for tax, penalties, or interest, or in any criminal case;

(d) tax authorities of a foreign country, in accordance with an international treaty to which Ethiopia is a party.

2) Persons who receive informaion under Sub-Article (1) must maintain the secrecy of that informaion, except to the minimum extent necessary to achieve the object for which disclosure is permitted. Other persons who receive information the disclosure of which is regulated by this section may not further disclose the informaion and must return documents reflecting the informaion to the Tax Authority.

3) Information concerning a taxpayer may be disclosed to another person with the taxpayer's written consent.

40. *Code of Conduct for Tax Authority Employees*

1) Each employee of the Tax Authority shall:

(a) be honest and fair, treating each taxpayer with courtesy and respect;

(b) apply the law, regulations and rulings to each case on the basis the objective facts in that case, showing no partiality to members of his family or to friends;

(c) refrain from participating in any determination that will affect his or his spouse's tax liability;

(d) where either a known family relationship or a business interest might influence any determination he must, as an employee, make public (in the manner provided by regulations) such relationship or interest;

(e) Subject to Article 39 protect the confidentiality of any tax or duty information, and

(f) not solicit or accept any bribe or perform any other improper act relating to the duty to determine or collect any tax.

፪· ማንኛውም የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኛ ፣ የግብር ሂሣብ ባለሙያ ወይም አማካሪ ሆኖ ለማገልገል ወይም የግብር ማስታወቂያ ለማዘጋጀት ወይም በግብር ላይ ምክር ለመስጠት ለሌላ ሰው ተቀጥሮ መሥራት የለበትም።

፵፩· የሌሎች መሥሪያ ቤቶች ትብብር

፩· ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ባለሥልጣኖችና ወኪሎቻቸው በተጨማሪም ድርጅቶች ፣ የቀበሌ መስተዳድሮች ፣ ማኅበራት ሁሉ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው ።

፪· ሀ) በይግባኝ ቀጠሮ ላይ ካልሆነ ወይም በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተራዘመ የግብር መክፈያ ጊዜ ካልተሰጠ በስተቀር ፣ ግብር ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ የከፈለ ስለመሆኑ ወይም አዲስ ግብር ከፋይን በሚመለከት የተመዘገበ ስለመሆኑ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ ሰጭ ሚኒስቴር ፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የፌዴራል ወይም የክልል መሥሪያ ቤት አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ አይችልም ።

ለ) ግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ ያለበትን ግዴታ ስለመፈጸሙ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ሲሆን ስለዚሁ ያለውን ምክንያት በመዘርዘር በጽሑፍ ለጠያቂው ይሰጣል።

ሐ) የምስክር ወረቀት አልሰጥም በማለቱ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ በመሠረዙ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል ።

፵፪· የሚኒስትሩ ሥልጣን

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ ሚኒስትሩ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፤

ሀ) በተዋዋይ ሀገሮች በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ግብር የመክፈል ግዴታ ያለባቸው የንግድ ሥራዎች ተደራራቢ ግብር እንዳይከፈልባቸው ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ከሌሎች መንግሥታት ጋር መዋዋል ፣

ለ) ማንኛውም ግብር ከፋይ ከፍተኛ የተፈጥሮ ችግር ወይም ሌላ ከባድ አደጋ ወይም ጥፋት ሲደርስበት ወይም በቸልተኝነቱ ምክንያት ሳይሆን ከአቅሙ በላይ በሆኑ ምክንያቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ያለበትን ግብር የመክፈል ግዴታ ለመፈጸም የማያስችለው ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የደረሰበት ሆኖ ሲያገኘው ፣ እስከ ብር ፩፻ሺህ የሚደርሰውን የግብር ዕዳ የመሠረዝ ፣

ሐ) ከብር ፩፻ሺህ በላይ የሆነ የግብር ዕዳ ቀሪ ሊሆን የሚችለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል ።

መ) ለዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ ለሚወጣው ደንብ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል ።

፵፫· የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አስፈላጊ ስለመሆኑ

ሀ) ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት ። ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲይዝ አይፈቀድለትም ።

ለ) ማንኛውም ግብር ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት ክፍያ አይጠየቅም ።

ሐ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት የሚደረገው ምዝገባ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚወሰን የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ይከናወናል ።

፵፬· ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ለተሰጠው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠት

ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረግበት ማንኛውም ግብር ከፋይ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ፣ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ላለበት ሰው ማስመዝገብ አለበት ። ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው የሰበሰበውን ግብር አግባብ ላለው የግብር ባለሥልጣን ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ ግብሩ የተቀነሰባቸውን ግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር እንዲሁም ከእያንዳንዱ የተቀነሰውን ግብር መጠን የሚያሳይ ዝርዝር አብሮ ማቅረብ አለበት ።

2) No employee of the Tax Authority shall act as a tax accountant or consultant or accept employment from any person preparing tax declarations or giving tax advice.

41. *Co-operation of other Entities*

1) All Federal and Regional government authorities and their agencies, Bodies, Kebele Administrations and Associations shall have the duty to co-operate with the Tax Authority in the enforcement of this Proclamation.

2) (a) No Ministry, Municipality, Department or Office of Federal or Regional Government shall issue or renew any license to any taxpayer unless the applicant produces a certificate from the Tax Authority to the effect that tax due in respect of the preceding year or years, have been paid or where the taxpayer is seeking license for the first time that he has registered with the Tax Authority unless appeal is pending, or time for payment is extended by the Tax Authority.

(b) If the Tax Authority refuses to issue a certificate it shall, on demand by the applicant for the license, provide him or it with a written statement of its reasons therefore.

(c) Any applicant who is aggrieved by the reasons stated by the Tax Authority for refusing to issue a certificate or by the revocation of his or its license may appeal in writing to the Review Commmittee.

42. *Powers of the Minister*

In addition to any powers specifically vested in him in this Proclamation the Minister of Finance and Economic Development may:

(a) enter into agreement with other Government for the avoidance of double taxation on activities or transactions liable to tax in the territories of both parties;

(b) in his discretion, waive tax upto an amount of birr 100,000 in cases of grave hardship due to natural or supervening calamity or disaster, or in cases of exceptional personal hardship not attributable to negligence or any failure on the part of the taxpayer to discharge any duty under this Proclamation; and

(c) no amount of tax in excess of Birr 100,000 shall be waived except with the approval of the Council of Ministers.

(d) issue Directives for the better implementation of this Proclamation and Regulations issued there under.

43. *TIN Requirement*

(a) Every person having a tax obligation is required to obtain a tax payer identification number ("TIN"), but in no case may a person obtain more than one TIN.

(b) No taxpayer is to be charged a fee for obtaining a TIN.

(c) The registration process shall proceed according to the timetable to be prescribed by directives to be issued by the Tax Authority.

44. *Supplying TIN to the Tax Withholding Agent*

A person subject to tax withholding is required to supply the TIN to the withholding agent. When paying over the withheld tax, the withholding agent shall list the taxpayer's TIN number along with the amount of tax withheld with respect to that taxpayer.

፵፭· የንግድ ሥራ ፈቃድ

የንግድ ሥራ ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ የተሰጠው ወይም እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውምሰው በፈቃድሰጪው ባለሥልጣን ዘንድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ማስመዝገብ አለበት።

፩· የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ የሚሰጥ ወይም የሚያድስ ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት ወይም ተቋም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ላላቀረበ ሰው ወይም ድርጅት ፈቃድ አይሰጥም ወይም አያድስም።

፪· በንዑስ አንቀጽ (፩) የተነገረው ቢኖርም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፵፫ መሠረት እንዲደርሰው በተደረገው የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ ጠያቂው መመዝገብ ያለበት ቀን ያልደረሰ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑን ከተረዳ ግብር ከፋዩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያቀርብ አይጠይቀውም።

፵፮· መመሪያዎች

የገቢዎች ሚኒስትር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለማግኘት ግብር ከፋዮች የሚመዘገቡበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል። የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የገቢዎች ሚኒስትር የሚያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ በየምድቡ የሚገኙ ግብር ከፋዮች የሚመዘገቡበትን ቀን ለይቶ የሚያሳይ የምዝገባ ሠሌዳ ያዘጋጃል። ይህንንም የጊዜ ሠሌዳ አግባብ ላላቸው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣኖች ያሠራጫል።

፵፯· አድራሻ ስለመለወጥና የንግድ ሥራን ስለማቋረጥ

፩· የንግድ አድራሻውን የሚለውጥ ማንኛውም ግብር ከፋይ የተደረገውን ለውጥ በ፴ ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

፪· የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ማንኛውም ግብር ከፋይ የንግድ ሥራውን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት። የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በሚቋረጥበት ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ከፋዩ በዓመቱ መጨረሻ ማቅረብ ያለበትን የገቢ ማስታወቂያ እንቅስቃሴው ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ በ፷ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት። የንግድ ሥራውን እንቅስቃሴ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ ሊከፈል የሚገባው ግብር በዚህ አንቀጽ መሠረት ገቢውን ለማስታወቅ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ወይም ከዚያ በፊት መከፈል አለበት።

፫· ሀ) ከግብር ዘመኑ በፊት ወይም በግብር ዘመኑ ውስጥ ከተቋረጠው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ፣ ኢንቬስትመንት ከማናቸውም የገቢ ምንጭ ግብር ከፋዩ ገቢ ያገኘ፣ እና

ለ) የንግድ ሥራው እንቅስቃሴ፣ የኢንቬስትመንቱ ወይም ከማናቸውም ሌላ የገቢ ምንጩ ከመቋረጡ በፊት የተገኘው ገቢ፣

በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ ገቢው በተገኘ ጊዜ የንግድ ሥራው እንቅስቃሴ፣ ኢንቬስትመንቱ ወይም ማናቸውም ሌላ የገቢ ምንጭ እንዳልተቋረጠ ተቆጥሮ ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ይደረግበታል።

፵፰· መዝገብ የመያዝ ግዴታ

፩· ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በስተቀር በአንቀጽ ፪(፭) በተተረጐመው መሠረት በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ወይም በሙሉ ወይም በከፊል የሚከራዩ ሕንፃዎች ባለቤት የሆኑ፣ የሂሳብ መዝገብ እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አለባቸው።

፪· በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሂሳብ መዝገብና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ ያለበት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎች አሟልቶ መያዝ አለበት፤

ሀ) ቋሚ ንብረቶች የተገዙበትን ቀን፣ የተገዙበትን ዋጋ እና አሁን ያላቸውን የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ የቋሚ ንብረት መዝገብ ጨምሮ የንግድ ሥራውን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ ሰነድ፣

ለ) ከንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በየቀኑ የተገኘውን ገቢ እና የተደረገውን ወጪ በተለይ ከገቢና ወጪው ምክንያት ጋር በማያያዝ፣

ሐ) ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ የተገዙ እና የተሸጡ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚከተሉትን የሚያሳይ፣

45. *Business Licenses*

1) A person obtaining a license to carry on a business occupation is required to supply the TIN to the licensing authority. All public bodies and institutions issuing a business or occupational license shall not issue or renew such license unless the taxpayer has supplied the TIN.

2) Notwithstanding Sub-Article (1) the licensing authority may not require the taxpayer to supply a TIN if according to the registration schedule distributed as per Article 43 shows that the date for his registration is not yet due.

46. *Directives*

The Minister of Revenue is hereby empowered to issue directives to provide procedures for TIN registration of taxpayers. In accordance with those directives, the Tax Authority shall prepare a schedule of registration for a TIN, which shall inter alia contain specific dates for registration of a given class of taxpayers, and shall distribute copies of the timetable to all licensing authorities.

47. *Change of Address and Cessation of Business*

1) Any taxpayer who makes a change of address shall notify the Tax Authority of the change within thirty (30) days.

2) Any taxpayer who ceases a trade or business activity shall notify the Tax Authority within thirty (30) days that the activity has ceased. In the case of a cessation of activity, any declaration of income required by this Proclamaation to be filed at the end of a tax year, shall be filed no later than sixty (60) days after the activity has ceased. Any tax due for the period in which the cessation occurred shall be paid on or before the declaration due date determined under this provision.

3) Where:

(a) any income is derived by a person in a tax year from any business, activity, investment or other source that has ceased either before the commencement of the year or during the year, and

(b) if the income had been derived before the business, activity, investment or other source ceased it would have been chargeable to tax under this Proclamation,

this Proclamation shall apply to the income on the basis that the business, activity, investment or other source had not ceased at the time the income was derived.

48. *Record Keeping Requirement*

1) All persons who are engaged in a business or trade as defined in Article 2(5), or who own buildings held all or in part for rental, except for Category C taxpayers shall keep books and records.

2) A person who is required to keep books and records in accordance with Sub-Article (1) shall keep the following information:

(a) a record of the business assets and liabilities, including a register of fixed assets showing the date of acquisition the cost of acquisition, and the current book value of each asset;

(b) a record of all daily income and expenses related to the business activity and the matter to which they relate;

(c) a record of all purchases and sales of goods and services related to the business activitiy showing:

(i) የተሸጠውን ዕቃና የተሰጠውን አገልግሎት በመለየት፣

(ii) ዕቃውን የገዙ ወይም የሸጡ ወይም አገልግሎቱን የሰጡ ሰዎችን ስም፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለይቶ እንዲያውቃቸው በሚያስችል አኳኋን፣

(iii) የሻጩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ አስቀድሞ ቁጥር የተሰጣቸው ደረሰኞች በመጠቀም፣

መ) በመጋዘን የተከማቹ የንግድ ዕቃዎችን ዓይነት፣ ብዛት እና ለዕቃዎቹ የተደረገውን ወጪ እንዲሁም ዕቃዎቹ የተገመቱበትን ዘዴ ጨምሮ በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በእጅ ያሉትን ዕቃዎች የሚያሳይ የሰነድ መረጃ፣

ሠ) የሚፈለገውን ግብር ለመወሰን የሚያስችሉ ማናቸውም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች፣

፫· ግብር ከፋዩ በውጭ አገር ቋንቋ የተዘጋጁ የሂሳብ መዝገቦችና ሰነዶች ያሉት እንደሆነ እነዚህን መዝገቦችና ሰነዶች በራሱ ወጪ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሠራባቸው አግባብ ባላቸው የሥራ ቋንቋዎች አስተርጉሞ እንዲያቀርብ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል።

፬· ግብር ከፋዩ በንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩትን የሂሳብ መዝገቦችና ሰነዶች፣ የያዙት ሂሳብ አግባብነት ካለው የግብር ዘመን አንስቶ ለአሥር ዓመታት ማቆየት አለበት።

፵፱· <u>የማኅበር መመሥረቻ ደንብ ስለማቅረብ</u>

ኩባንያዎች፣ የሽርክና ማኅበሮች እና ሌሎች ለንግድ የተቋቋሙ ማኅበራት ሁሉ የተመሠረቱበትን የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ጽሑፍ ትክክል ግልባጭ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መስጠትና በተከታታይም በዚሁ ላይ የተደረገ ለውጥ ሲኖር ማስታወቅ አለባቸው ።

፶· <u>ኦዲተሮች</u>

፩· ማንኛውም ኦዲተር የደንበኛውን ዓመታዊ ሂሣብ መርምሮ የሰጠውን ሪፖርት በግብር አስገቢው ባለሥልጣን በፅሑፍ ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት ።

፪· ጥያቄው በቀረበበት ፅሑፍ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ማንኛውም ኦዲተር ሪፖርቱን ባያቀርብ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን የኦዲተሩ ፈቃድ እንዲሰረዝ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያስታውቃል ።

## ክፍል ሁለት
## ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሥርዓት

፶፩· <u>ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር ቀንሶ ገቢ ስለማድረግ</u>

፩· በዚህ አዋጅ በግልፅ ከግብር ነፃ እንዲሆን የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ክፍያ ላይ ተገቢውን ግብር ቀንሶ ማስቀረት አለበት ።

፪· ቀጣሪው በመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ በማድረግ ረገድ ያለበት ግዴታ ፣ ለሠራተኛው ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀናሽ መደረግ ካለባቸው ሌሎች ግዴታዎች ቅድሚያ ይኖረዋል ።

፫· ቀጣሪው ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ። በዚህ ዓይነት ተቀንሶ የቀረው ግብር ገቢ በሚደረግበት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያገኙትን ሠራተኞች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት ።

፬· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው መግለጫ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚወስነው ቅርፅና አኳኋን የሚቀርብ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ) የእያንዳንዱን ተቀጣሪ ስም ፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፣

ለ) እያንዳንዱ ተቀጣሪ ከመቀጠር ያገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን፣

ሐ) ከዚሁ ገቢ ላይ ተቀንሶ የቀረውን ግብር መጠን ፣

መ) ከግብር ነፃ የተደረገ ተቀጣሪው ያገኘው ገቢ መጠን፣

(i) the particular goods and services sold;

(ii) the name of the buyers and sellers or providers in such a manner that they can be identified by the Tax Authorities;

(iii) and using pre-numbered invoices containing the vendor's tax identification number;

d) a record of trading stock on hand at the end of the accounting period, including the type, quantity and cost of that stock as well as the method of valuation of that stock;

(e) any other document relevant for the determination of the tax liability.

3) If a taxpayer has certain books or records in a foreign language, the Tax Authorities may require that they be translated into one of the official languages of Ethiopia at the taxpayer's expense.

4) The books and records mentioned in Sub-Article (2) shall be kept by the taxpayer for a period of ten (10) years after the end of the tax period to which they relate.

49. *Submission of Memorandum of Association*

Companies, partnership and other business organizations shall submit to the Tax Authority a copy of their memorandum of association and statutes and shall notify the Tax Authority of any subsequent change therein.

50. *Public Auditors*

1) Any auditor, when requested by the Tax Authority in writing shall submit the audit report of his clients.

2) Where any auditor fails to submit the report within the time specified in the letter referred above, the Tax Authority shall notify the Licensing Authority to withdraw the license of the auditor.

## SECTION II
### *Withholding Procedures*

51. *Withholding of Tax on Employment Income*

1) An employer shall withhold tax from every payment to an employee, unless the payement is expressly made tax-exempt by this Proclamation.

2) The obligation of an employer to withhold tax has priority over all other obligations to withhold any other amounts from payments to an employee.

3) An employer shall pay the withheld tax to the Tax Authority within thirty (30) days of the end of each calendar month, and each payment shall be accompanied by a statement with respect to each employee who derives taxable income for the month.

4) The statement referred to in Sub-Article (3) shall be in the form and furnished in the manner prescribed by the Tax Authority, and shall contain the following information:

(a) the name, address, and TIN of each employee;

(b) the amount of taxable income derived by each employee from the employment;

(c) the amount of the tax withheld from that income, and

(d) the amount of any tax-exempt income derived by the employee.

፶፪· *ዕቃዎች ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ ስለሚከፈል የገቢ ግብር*

፩· ዕቃዎች ለንግድ ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ የንግድ ትርፍ ግብር ይከፈልባቸዋል ። በዚህ ዓይነት የሚሰበሰበው ግብር ፣ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ እንደቀረ ግብር ተቆጥሮ ግብር ከፋዩ በዓመቱ መጨረሻ መክፈል ከሚገባው የግብር መጠን ላይ እንዲታሰብለት ይደረጋል ።

፪· በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰበው የንግድ ትርፍ ግብር አስመጪው ለዕቃው በከፈለው ዋጋ የመድን አረቦን፣ እና የመጓጓዣ ወጪ (ሲ·አይ·ኤፍ) ላይ የሚታሰብ ፫ ፐርሰንት (ሦስት በመቶ) ይሆናል።

፫· ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ግብር፣ ግብር ከፋዩ ያስታወቀውን ገቢ መሠረት በማድረግ ከተወሰነው ግብር ያነሰ እንደሆነ፣ ግብር ከፋዩ ልዩነቱን እንዲከፍል ይደረጋል። ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ግብር በዓመቱ ሊከፈል ከሚገባው ግብር የበለጠ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሂሳቡን አጣርቶ በብልጫ የተከፈለውን ግብር በአንቀጽ ፸፮ በተገለጸው ጊዜ እና አኳኋን ለግብር ከፋዩ ይመልስ ለታል።

፬· በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰበሰበው ግብር፣ የግብር ከፋዩን ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመጠቀም መመዝገብ እና ሂሳቡን በዚሁ መሠረት መያዝ አለበት። ሆኖም ግብር ከፋዩ የመመዝገቢያው ጊዜ ባለመድረሱ ምክንያት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያልያዘ እንደሆነ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን አግኝቶ ግብሩን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ገቢ ለሚያደርገው ሰው እስከሚሰጥ ድረስ ምዝገባው የሚከናወነው በግብር ከፋዩ ስምና አድራሻ ብቻ ይሆናል።

፭· ሚኒስትሩ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ለንግድ የሚውሉ ዕቃዎች» የሚለውን ሐረግ ትርጉም በመመሪያ ይወስናል።

፶፫· *ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት*

፩· በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የመን ግሥት መ/ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሚኒ ስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት ከተወሰነ ማናቸውም ክፍያ ላይ ግብሩን ቀንሰው ማስቀረት አለባቸው።

፪· ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ ቀሪ የሚደረገው ግብር የጠቅላላ ተከፋይ ሂሳብ ፪ ፐርሰንት (ሁለት በመቶ) ይሆናል።

፫· ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት ሰው በወሩ ውስጥ ከተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው በወሩ የሰበሰበውን አጠቃላይ ሂሳብ ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ ክፍያ የተፈፀ መለትን የእያንዳንዱን ሰው ወይም ድርጅት ስም፣ መለያ ቁጥሩን፣ በወሩ ውስጥ ለተጠቀሰው ሰው የተከፈለውን ገንዘብ አጠቃላይ ድምር፣ ተቀናሽ ተደርጐ የቀረበውን ግብር እና በእያንዳንዱ ሰው ስም ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የተደረገውን ሂሳብ የሚያሳይ ዝርዝር ማቅረብ አለበት።

፬· ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ የተቀነሰው ግብር በዓመቱ መከፈል ከነበረበት ትክክለኛ ግብር ያነሰ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ግብር ከፋዩ ገቢውን በሚያስታውቅበት ጊዜ በልዩነት የሚፈለገውን ግብር ገቢ ማድረግ አለበት። ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ የተቀነሰው ግብር በዓመቱ መከፈል ከሚገባው በላይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን በብልጫ የተከፈለውን ግብር በአንቀጽ ፸፮ በተገለጸው ጊዜ እና አኳኋን ለግብር ከፋዩ ይመልስለታል።

52. *Collection of Tax On Imports*

1) A current payment of income tax shall be collected on Schedule C income at the time of import of goods for commercial use, and the collected amount treated as tax withheld that is creditable against the taxpayer's income tax liability for the year.

2) The amount collected on import of goods shall be three percent (3%) of the sum of cost, insurance, and freight ("CIF value").

3) If the amount of income tax collected on the import of goods results in underpayment of business income tax due for the year, as determined at the time of declaration of income tax, the taxpayer is required to pay the difference with the declaration. If the amount represents an overpayment of income tax due for the year, the Tax Authority shall after ensuring the accuracy of the books and records refund the taxpayer the amount overpaid within 3 months period.

4) The tax collected under this Article shall be recorded and accounted – for using the taxpayer's name, address, and TIN; provided, however that if a taxpayer is not required to obtain a TIN the records shall be kept using only the taxpayer's name and address until such time as the taxpayer supplies a TIN to the collecting agency.

5) For purposes of implementing the provisions of this Article the Minister shall by directive define the term "for commercial use."

53. *Withholding of Income Tax on Payments*

1) Origanization having legal personality, ', government agencies, private nonprofit institutions, and non-governmental organizations ("NGOs") shall withhold income tax on payments which by Regulations to be issued by the Council of Ministers are subject to withholding Tax.

2) The amount withheld shall be two per cent (2%) Of the gross amount of the payment.

3) Within ten days from the last day of each month, the withholding agent shall transfer to the government the amount required to be withheld on payments made during the month. The withholding agent's aggregate monthly transfer shall be accompanied by a statement lising separately each specified person to whom payments were made; the person's TIN; the monthly total of payments made to that person; and the amount of income tax withheld results in government with respect to that person.

4) If the amount of income tax withheld on payment to specified person results in underpayment of income tax actually due for the year, as determined at the time of declaration of income tax, the taxpayer is required to pay the difference with the declaration. If the amount of income tax withheld results in overpayment of income tax actually due for the year, the Tax Authority shall refund the taxpayer within the time and in the manner prescribed under Article 76.

፭· በዚህ አንቀጽ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብሩን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ተቀንሶ ገቢ መደረግ ያለበትን ግብር በሙሉ ወይም በከፊል ቀንሶ ገቢ ያላደረገ እንደሆነ ግብሩን ሙሉ በሙሉ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ይገደዳል።

፶፬· <u>የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ለባለመብቱ በሚከፈልበት ጊዜ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት</u>

፩· ማናቸውም በሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለባለመብቱ የሚከፍል ሰው፣ በሠንጠረዥ "መ" መሠረት የሚፈለገውን ግብር ከተከፋዩ ሂሣብ ላይ ቀንሶ ማስቀረት አለበት።

፪· ከፋዩ ያለበት ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ፣ ከፋዩ ከተከፋዩ ገቢ ላይ ቀንሶ ማስቀረት ካለበት ሌላ ማናቸውም ግዴታ ቀዳሚነት ይኖረዋል።

፫· ከፋዩ ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት ፲፭ ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። ስለሆነም በዚህ ዓይነት ተቀንሶ የቀረው ግብር ገቢ በሚደረግበት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያገኙትን ግብር ከፋዮች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፬· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው መግለጫ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚወስነው ቅርፅና አኳኋን የሚቀርብ ሆኖ፣ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፤

ሀ) የእያንዳንዱን ግብር ከፋይ ስም፣ አድራሻ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ለ) በሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር የሚከፈልበትን ክፍያ መጠን።

ሐ) ከክፍያው ላይ ተቀንሶ የቀረውን ግብር መጠን፣

፭· ለግብር ከፋዩ ክፍያ በሚፈፀምበት ጊዜ፣ ከፋዩ ለእያንዳንዱ ግብር ከፋይ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን ግብር ተቀንሶ ቀሪ መደረጉን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። ይህም የምስክር ወረቀት በንዑስ አንቀጽ (፬) የተዘረዘረውን መረጃ፣ ግብር ከፋዩ ተቀንሶ ቀሪ በተደረገው የግብር መጠን ላይ ቅሬታውን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን፣ እና ቅሬታውን ማቅረብ የሚችልበትን አኳኋን የሚገልፅ መሆን አለበት።

፮· ግብር ተቀንሶ ቀሪ መደረጉን የሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት በሠንጠረዥ "መ" መሠረት ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተቀንሶ ለቀረው ግብር ማስረጃ ይሆናል።

፶፭· <u>የመታወቂያ ወረቀት ስለመስጠት</u>

የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ለተሰጣቸው ሰዎች የመታወቂያ ወረቀት ይሰጣል።

፶፮· <u>የተፈፀመውን ክፍያ እና ግብር ተቀንሶ ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥ ሰነድ</u>

፩ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው በእያንዳንዱ የግብር ዘመን፣

ሀ) የተፈፀሙ ክፍያዎችን፣ እና

ለ) ከእነዚህ ክፍያዎች ተቀንሶ የቀረውን ግብር፣

የሚያሳዩ የሂሳብ ሰነዶችን የመያዝ እና የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ምርመራ እንዲያደርግባቸው የማቅረብ ግዴታ አለበት።

፪· ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን የሂሳብ ሰነዶች አግባብነት ካላቸው የግብር ዘመን መጨረሻ አንስቶ ለ፭ የግብር ዓመታት ማቆየት አለበት።

፫· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ሰነዶች ኮፒ እርሱ በሚሰጠው ቅፅ እና ሁኔታ እንዲሁም በሚወስነው የጊዜ ልዩነት እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።

፶፯· <u>በታክሱ ዘመኑ ውስጥ የሚፈለገውን ግብር ስለማስተካከል እና ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ስላለበት የመካስ ግዴታ</u>

፩· ተቀንሶ ቀሪ የተደረገው ግብር የመጨረሻ የግብር ክፍያ ከሆነበት ሁኔታ በስተቀር፣ ተቀንሶ ቀሪ የተደረገ ግብር ክፍያ (በአንቀጽ ፶፫ ወይም በአንቀጽ ፶፬ መሠረት በየጊዜው የተከፈለ ግብር ወይም በአንቀጽ ፶፪ መሠረት በገቢ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ ግብር) ግብር ከፋዩ በዚያው የታክስ ዘመን ውስጥ ሊከፍል የሚገባው ግብር በሚሰላበት ጊዜ የሚካተት ይሆናል።



5) If a withholding agent fails to withhold or under withholds he shall be made to pay the full amount of the tax to the Tax Authority.

54. *Withholding of Schedule "D" Income Tax on Payments*

1) The payer of any payment subject to tax under Schedule "D" shall withhold from the payment the amount of tax required by Schedule "D".

2) The obligation of the payer to withhold tax has priority over all other obligations to withhold amounts from payments to a payee (the taxpayer).

3) A payer shall pay the witheld tax to the Tax Authority within fifteen (15) days of the end of each calendar month, and each payment shall be accompanied by a statement with respect to each taxpayer who received payments during the month.

4) The statement referred to in Sub-Article (3) shall be in the form and furnished in the manner prscribed by the Tax Authority, and shall contain the following information :

(a) the name, address, and TIN of each taxpayer;

(b) the amount of payments subject to tax under Schedule D;

(c) the amount of the tax withheld from the payments.

5) At the time of making a payment to a taxpayer, the payer shall furnish each taxpayer a tax withholding certificate (in the form prescribed by the Tax Authority) showing the date of the payment and stating the information listed in Sub-Article (4); the taxpayer's right to contest the amount of tax withheld; and the manner of doing so.

6) The tax-witholding certificiate is proof of the amount of tax withheld on payments subject to tax under Schedule D.

55. *Issuance of Identification Card*

The Tax Authority shall issue identification cards to Withholding Agents.

56. *Record of Payments and Tax Withheld*

1) A withholding agent shall maintain, and make available for inspection by the Tax Authority, records showing, in relation to each fiscal year:

(a) payments made to a payee, and

(b) tax withheld from those payments.

2) The withholding agent shall keep the records referred to in Sub-Article (1) for five (5) fiscal years after the end of the fiscal year to which the records relate.

3) The Tax Authority may require a withholding agent to furnish a copy of the records to be maintained under Sub-Article (1) in the manner, form and at the intrvals prescibed by the Tax Authority.

57. *Adjustment To Tax Due For Year And Withholding Agent's Indemnity*

1) Except for tax withheld with respect to final taxes, withheld tax (or tax paid currently under Article 53 or Article 54 or collected on import under Article 52 is included in ascertaining a taxpayer's tax due for the tax year.

፪· ግብሩ ተቀንሶ ገቢ የተደረገበት ሰው ተቀንሶ ገቢ የተደረገው ግብር እንዲከፈለው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ያስቀረ እና ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ያደረገ ሰው ገቢ የተደረገውን ግብር ለተቀነሰበት ሰው እንደ ከፈለ ይቆጠራል።

ክፍል ሦስት
የግብር ሂሳብ አያያዝ መርሆዎች

፶፰· የሂሳብ አያያዝ ዘዴ

፩· በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ግብር ከፋዩ ያገኛል ተብሎ የታሰበውን ወይም ያገኘውን ገቢ ለማረጋገጥ ከዘመኑ በኋላ የሚሰበሰበው ወይም የሚከፈለው ሂሳብ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በዘመኑ እንደተሰበሰበ ወይም እንደተከፈለ ተቆጥሮ እንደአግባብነቱ በገቢነት እንዲያዝ ወይም በወጪ እንዲቀነስ ይደረጋል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫)የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተለየ የሂሳብ አያያዝ ሥራ ላይ እንዲውል ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ግብር ከፋይ ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ ወይም በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መያዝ አለበት።

፫· ለግብር አከፋፈል ሲባል ኩባንያ ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መሠረት መያዝ አለበት።

፬· ማንኛውም ሰው የሂሳብ አያያዝ ዘዴውን ለመለወጥ እንዲፈቀድለት የግብር አስገቢውን ባለሥልጣን በፅሑፍ መጠየቅ ይችላል። የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ተለዋጩ ዘዴ የግብር ከፋዩን ሂሳብ በትክክል የሚያሳይ ነው ብሎ ሲያምንበት ለውጡን መቀበሉን በፅሑፍ ያስታውቃል።

፭· የግብር ከፋዩ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ እንዲለወጥ ሲፈቀድ የገቢ ርዕሶች ሳይመዘገቡ እንዳይቀሩ ወይም በድጋሚ እንዳይመዘገቡ ለማድረግ የግብር ከፋዩ የገቢ ርዕሶች፣ ተቀናሽ ወይም የታክስ ማካካሻ ሂሳቦች ላይ ለውጡ ከተደረገበት የግብር ዘመን ቀጥሎ ባለው ዓመት ውስጥ ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይገባል።

፶፱· በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ

፩· ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዘውን ግብር ከፋይ ገቢ ለማስላት ግብር ከፋዩ የተቀበለውን ወይም በስሙ የተያዘለትን የገንዘብ መጠን በሂሳቡ ውስጥ ማካተት አለበት።

፪· ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ወጪ አደረገ የሚባለው ግብር ከፋዩ በራሱ የሚፈፅመው ክፍያ ሲሆን ነው።

፷· በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ

፩· ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ፣ ገቢውን በሚያሠላበት ጊዜ በስሙ በተሰብሳቢነት የተያዘውን የገንዘብ መጠን በሂሳቡ ውስጥ ማካተት አለበት።

፪· ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ የተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ወጪ አደረገ የሚባለው በስሙ በተከፋይነት የተያዘ ሲሆን ነው።

፫· በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አንድ ሂሳብ በግብር ከፋዩ ተሰብሳቢ ነው የሚባለው የመክፈያው ጊዜ የተላለፈ ወይም ክፍያው የሚፈፀመው በተወሰኑ ክፍያዎች ተከፋፍሎ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ሂሳቡን ለመቀበል መብት ባገኘበት ጊዜ ነው።

፬· በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አንድ ሂሳብ ተከፋይ ሂሳብ ነው ተብሎ የሚያዘው ለክፍያው ምክንያት የሆነው ግዴታ በትክክል የታወቀ ሲሆን ነው። ይሁን እንጂ ግዴታው የታወቀ ቢሆንም ለዚህ ሂሳብ መሠረት የሆነው የኤኮኖሚ ተግባር ከመከናወኑ በፊት እንደተከፋይ ሂሳብ አይያዝም።

፭· ለንዑስ አንቀጽ (፬) አፈፃፀም የኤኮኖሚ ተግባር ተከናወነ የሚባለው፦



2) A withholding agent who has withheld under this Proclamation and remitted the amount withheld to the Tax Authority is treated as having paid the withheld amount to the payee for the purposes of a claim by the taxpayer for payment of the amount withheld.

SECTION III
*Tax Accounting Principles*

58. *Method of Accounting*

1) Subject to this Proclamation, for the purposes of ascertaining a person's income accruing or derived during a tax period, the timing inclusions and deductions shall be made according to generally accepted accounting principles.

2) Without prejudice to Sub-Articles (1) and (3), and unless the Tax Office prescribes otherwise in particular case, a taxpayer shall account for tax purposes on a cash or accural basis.

3) A company shall account for tax purposes on an accrual basis.

4) A person may apply, in writing, for a change in that person's method of accounting and the Tax office may, by notice in writing, approve the application but only if satisfied that the change is necessary to clearly reflect that person's income.

5) If the person's method of accounting is changed, adjustments to items of income, deduction, or credit shall be made in the tax period following the change, so that an item is not omitted or taken in account more than once.

59. *Cash–Basis Accounting*

1) A person who is accounting for tax purposes on a cash basis shall acoount for amounts to be included in calculating that person's income when they are received by, or made available to that person.

2) An outgoing or expense is incurred by a person who is accounting, for tax purposes, on a cash basis when it is paid by that person.

60. *Accrual–Basis Accounting*

1) A person who is accounting for tax purposes on an accrual basis shall account for amounts to be included in ascertaining that person's income when they are receivable by that person.

2) An outgoing or expense is incurred by a person who is accounting for tax purposes on an accrual basis when it is payable by the person.

3) Subject to this Proclamation, an amount is receivable by a person when that person becomes entitled to receive it, even if the time for discharge of the entitlement is postponed or the entitlement is payable by installments.

4) Subject to this Proclamation, an amount is treated as payable by a person when all the events that determine liability have occurred and the amount of the liability can be determined with reasonable accuracy, but not before economic performance with respect to that amount occurs.

5) For the purposes of Sub-Article (4), economic performance occurs:

ሀ) አገልግሎቶችን እና ንብረቶችን በተመለከተ አገልግሎቱ በተሰጠ ወይም ንብረቱ በተገኘ ጊዜ ነው።

ለ) በንብረት መጠቀምን በተመለከተ ንብረቱ በጥቅም ላይ በዋለበት ጊዜ ነው፣

ሐ) በማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችለውን ሙሉ ክፍያ ግብር ከፋዩ በፈፀመበት ጊዜ ነው።

፷፩. <u>አስቀድሞ ስለተደረጉ ክፍያዎች</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለመሬት ሊዝ የተፈፀመ ክፍያን ጨምሮ ማናቸውም ከአሥራ ሁለት ወራት በላይ ለሚቆይ አገልግሎት ወይም ማናቸውም ሌላ ጥቅም የተደረገ ወጪ ተቀናሽ ተፈፃሚ የሚሆነው፣ አገልግሎቱ ወይም ጥቅሙ ሥራ ላይ በሚውልበት የግብር ዘመን ተከፋፍሎ ነው።

፷፪. <u>መብትን ስለመጠየቅ</u>

፩. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ገንዘቡ ለመቀበል የሕግ መብት ያለው ወይም ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለፅ የይገባኛል ጥያቄ እስካቀረበ ድረስ ጠያቂው ገንዘቡን የመቀበል መብት ወይም የመክፈል የሕግ ግዴታ የሌለበት ቢሆንም እንዲህ ያለውን ሂሳብ እንደገቢ ወይም እንደወጪ መያዝ አለበት።

፪. በንዑስ አንቀጽ (፩) የተነገረው ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ገንዘቡን የተቀበለው ሰው መልሶ የተካ ወይም ወጪ የተደረገ ሂሳብ እንዲመለስ የተደረገ እንደሆነ ገንዘቡ በተተካ ወይም ወጪው በተመለሰበት የግብር ዘመን ውስጥ የተገኘው ገቢ በዚሁ መሠረት መስተካከል አለበት።

፫. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ገንዘብ ለመቀበል የሕግ መብት ያለው ወይም ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ ያለበት መሆኑን በመግለፅ ጥያቄ እስካቀረበ ድረስ ጠያቂው ገንዘቡን የመቀበል መብት ወይም የመክፈል የሕግ ግዴታ የሌለበት ቢሆንም እንዲህ ያለውን ሂሳብ እንደተሰብሳቢ ወይም እንደተከፋይ ሂሳብ መያዝ አለበት።

፬. በንዑስ አንቀጽ (፫) የተነገረው ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ጠያቂው ገንዘቡን ልቀበል ይገባል ወይም ክፍያ የመፈፀም ግዴታ አለብኝ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ ያነሳ እንደሆነ ጥያቄውን ባነሳበት የግብር ዘመን ውስጥ ያገኘው ገቢ ተገቢ በሆነ አኳኋን እ፣ ስተካከል ይደረጋል።

፷፫. <u>ለረዥም ጊዜ ስለሚቆዩ ውሎች</u>

፩. ለግብር አከፋፈል ሲባል ሂሳቡን በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ላይ በተመሠረተ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለረዥም ጊዜ ከሚቆይ የንግድ ሥራ ውል ጋር በተያያዘ አንድ ሂሳብ በገቢ ውስጥ መቼ እንደሚካተት ወይም ተቀናሽ እንደሚደረግ የሚወሰነው በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ከውሉ ውስጥ የተጠናቀቀውን በመቶኛ በማስላት ይሆናል።

፪. ከረዥም ጊዜ ውል ውስጥ የተጠናቀቀው በመቶኛ የሚወሰነው የውሉን ጠቅላላ ዋጋ እና ከግብር ዘመኑ ማለቂያ ጊዜ በፊት የተደረገውን ወጪ፣ የተደረጉ ማስተካከያዎችን እና የዋጋ ውጣ ውረድን ጨምሮ ከተገመተው ጠቅላላ የውሉ ዋጋ ከሆነው ጋር በማነፃፀር ይሆናል።

፫. የንግድ ሥራ የረዥም ጊዜ ውል በሚጠናቀቅበት የግብር ዘመን ውስጥ የንግድ ሥራውን የሚያካሂደው ሰው ለረዥም ጊዜ ከሚቆዩት ውሎች ጋር በተያያዘ፣

ሀ) የከሰረ፣ ወይም

ለ) ያልተካካሰ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሸጋገር ኪሣራ ያለው እንደሆነ፣

ሐ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኪሣራው ወደ አለፉት የግብር ዓመታት እንዲዘዋወር፣ እና

መ) ለረዥም ጊዜ ከሚቆይ ውል ጋር በተያያዘ በአንድ የግብር ዘመን ከገቢ ላይ ከሚያዘው ወጪ እስካልበለጠ ድረስ ከገቢው ላይ እንዲካካስ ያደርጋል።



(a) with respect to the acquisition of services or property, at the time the services or properties are provided;

(b) with respect to the use of property, at the time the property is used; or

(c) in any other case, at the time that person makes payment in full satisfaction of the liability.

61. *Prepayments*

Without prejudice to Article 21 of this Proclamation, a deduction for an outgoing or expense incurred on a service or other benefit which extends beyond twelve months including cost of lease of land, shall be allowed proportionately over the tax periods to which the service or other benefit relates.

62. *Claim of Right*

1) A taxpayer who is accounting for tax purposes on a cash basis shall treat an amount as received and an outgoing or expense as paid, even though that person is not legally entitled to receive the amount or liable to make the payment, if that person claims to be legally entitled to receive, or legally obliged to pay the amount.

2) Where Sub-Article (1) applies and that person later refunds the amount received or recovers the outgoing or expense paid, an appropriate adjustment shall be made to that person's income of the tax period during which the refund or recovery occurs.

3) A person who is accounting for tax purposes on an accrual basis shall treat an amount as receivable and an outgoing or expense as payable even though that person is not legally entitled to receive the amount or liable to make the payment, if that person claims to be legally entitled to receive, or to be legally obliged to pay the amount.

4) Where Sub-Article (3) applies and that person later ceases to claim the right to receive the amount or to claim an obligation to pay the outgoing or expense, an appropriate adjustment shall be made to that person's income of the tax period during which that person ceases to make the claim.

63. Long Term Contracts

1) In the case of a person accounting for tax purposes on an accrual basis, the timing of inclusions in and deductions from income relating to a long-term contract of a business of that person shall be accounted for on the basis of the percentage of the contract completed during any tax period.

2) The percentage of completion is determined by comparing the total costs allocated to the contract and incurred before the end of the tax period with the estimated total contract costs including any variations or fluctuation.

3) Where during the tax period in which a long-term contract of a business is completed the person carrying on the business:

(a) incurs a loss; or

(b) has an unrelieved loss available for carrying forward under Article 28(1);

which is attributable to the long-term contract, the Tax Authority may allow the loss to be:

(c) carried back to preceding tax periods, and

(d) applied against an amount of income of a tax period not exceeding the amount by which inclusions in the income of the business relating to the long-term contract for that period exceed deductions therefrom.

፬· አንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ በንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያጋጥመው ኪሣራ ከንግድ ሥራው የረዥም ጊዜ ውሎች ጋር እንዲያያዝ ማድረግ የሚቻለው በግብር ዘመኑ ከንግድ ሥራው የረዥም ጊዜ ውሎች የተገኘውን ገቢ ለማስላት የተፈቀደው ወጪ ገቢውን ለመወሰን መሠረት ከተደረጉ ሂሳቦች የበለጠ እንደሆነ ነው።

፭· በዚህ አንቀጽ ውስጥ "የንግድ ሥራ የረዥም ጊዜ ውል" ማለት ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ፲፪ ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዘመን ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት፣ የመትከል ወይም የግንባታ ሥራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው።

ክፍል አራት

ገቢን ስለማስታወቅ እና ግብርን ስለመወሰን

፷፬· የግብር ዓመት

፩· በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልተወሰነ በስተቀር፣ ግብር የሚወሰንበት ጊዜ ("የግብር ዓመት") ማለት የበጀት ዓመት ሲሆን፣ ይህም ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

፪· የግብር ከፋዮች የግብር ዓመት፤

ሀ) ግለሰቦችን እና የሽርክና ማኅበሮችን በሚመለከት የበጀት ዓመቱ፣

ለ) ድርጅቶችን በሚመለከት፣ የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት ነው።

፫· ማናቸውም ድርጅት በግብር አስገቢው ባለሥልጣን በቅድሚያ በፅሑፍ ካልተፈቀደለት እና ከፈቃዱ ጋር በተያያዘ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የዘረዘራቸውን ሁኔታዎች ካላሟላ በስተቀር የሂሳብ ዓመቱን መለወጥ አይችልም።

፬· የሂሳብ ዓመቱን እንዲለውጥ የተፈቀደለት ድርጅት ከፈቃዱ ጋር በተያያዘ ከተዘረዘሩት ግዴታዎች አንዱን ያላሟላ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የፅሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለድርጅቱ የተሰጠውን ፈቃድ መሠረዝ ይችላል።

፭· የግብር ከፋዩ የሂሳብ ዓመት በንዑስ አንቀጽ (፫) ወይም (፬) መሠረት የተለወጠ እንደሆነ፣ ለውጡ ከመደረጉ በፊት ባለው ሙሉ የግብር ዓመት እና አዲሱ የግብር ዓመት በሚጀምርበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ "የመሸጋገሪያ ዓመት" በመባል የሚታወቅ እና በተለየ ሁኔታ የሚታይ ይሆናል።

፷፭· የምስክር ወረቀት እና የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢን ስለመወሰን

፩· ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚሰጠው ግብር ተቀናሽ መደረጉን የሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት፣ ተቀጣሪው ካገኘው የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ ላይ በምስክር ወረቀቱ የተመለከተው ግብር ተቀናሽ ለመደረጉ ማረጋገጫ ነው።

፪· ተቀጣሪው ካገኘው የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ ላይ ተቀንሶ የቀረውና በአንቀጽ ፶፩ መሠረት ከቀጣሪው ከሚቀርብ መግለጫ ጋር ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የተደረገው ሂሳብ፣ ገንዘቡ ገቢ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የሚፀና በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተወሰነ ግብር እንደሆነ ተደርጐ ይወሰዳል። ሆኖም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ መኖሩን የደረሰበት እንደሆነ ማሻሻያ ለማድረግ ይችላል።

፫· አንድ ተቀጣሪ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ ብቻ የሆነ እንደሆነ ገቢውን የማስታወቅ ግዴታ የለበትም።

፬· ከዚህ በላይ የተነገረው ቢኖርም ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ ተቀጥሮ ገቢ የሚያገኝ ወይም የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው ዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ አገር መንግሥታት ኤምባሲዎች ሚሲዮኖችና በማናቸውም የኮንስለር ተቋሞች የሚሠራ የሠንጠረዥ "ሀ" ገቢ የሚያገኝ ተቀጣሪ በአንቀጽ ፶፩(፫) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ራሱ አስታውቆ ግብሩን መክፈል አለበት።

፭· ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ ተቀጥሮ ገቢ የሚያገኝ ሠራተኛን ቀጥሮ የሚያሠራ ሰው ሠራተኛው ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ የሚሠራ መሆኑን ከደረሰበት እና ገቢው በሌላው ቀጣሪ ያልተጣመረ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብለት ገቢውን አጣምሮ ግብሩን ይወስናል።



4) A loss incurred by a person in carrying on a business during a tax period is attributable to a long-term contract of the business to the extent that deductions allowed in ascertaining the income from the business relating to the long-term contract for that period exceed inclusions in ascertaining that income.

5) In this Article, "long-term contract" of a business of a person means a contract for manufacture, installation, or construction, or, in relation to each, the performance of related services, which is not completed within the tax period in which work under the contract commenced, other than a contract estimated to be completed within twelve (12) months of the date on which the work under the contract commenced.

SECTION IV

Declaration and Assessment

64. *Tax Year*

1) Unless otherwise provided, the period for tax assessment ("tax year") shall be the fiscal year, that is, the one-year period from 1st Hamle to 30th Sene.

2) The tax year of a person is:

(a) in the case of an individual or an association of individuals, the fiscal year;

(b) in the case of a body, the accounting year of the body.

3) A body shall not change its accounting year unless it obtains prior approval, in writing, from the Tax Authority and complies with any condition that may be attached to the approval.

4) The Tax Authority may, by notice in writing, revoke an approval granted to a company under Sub-Article (3) if the body fails to comply with any of the conditions attached to the approval.

5) Where the tax year of a person changes as a result of Sub-Article (3) or (4), the period between the last full tax year prior to the change and the date on which the new tax year commences shall be treated as a separate tax year, to be known as the "transitional year."

65. *Certificate and Assessment of Schedule A Income*

1) The tax-withholding certificate issued by an employer to an employee shall be proof that tax in the amount stated was withheld on the employee's Schedule "A" income of the amount stated.

2) The amount of tax withheld on an employee's Schedule A income, paid to the Tax Authority and accompanied by the employer's statement (as required by Article 51) shall be the amount assessed by the Tax Authority effective on the date the tax is paid, and subject to later amendment if the Tax Authority determines that an error or omission has been made.

3) In the case of an employee whose taxable income for a tax year consists exclusively of Schedule "A" income, no declaration of income is required.

4) Notwithstanding the preceding, an employee working for more than one employer or an employee of international organization having diplomatic immunity or working in embassies, missions and other consular establishments of a foreign government shall himself declare and pay taxes on his schedule "A" income with the time prescribed under Article 51(3).

5) If an employer finds out that his employee has more than one employment income and if he ascertains that the other employer(s) have not aggregated said income, he shall aggregate and withhold the tax thereon.

፷፮· የሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ገቢን ስለማስታወቅ እና ግብር ስለመወሰን

፩· ማንኛውም የሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ገቢ የሚያገኝ ግብር ከፋይ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚያወጣው ቅጽ መሠረት፣

ሀ) የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ፣

ለ) የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ፣

ገቢውን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርበው ሂሣብ ዓይነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል ።

፫· በገቢ ማስታወቂያው መሠረት ከተሠላው ግብር ላይ በግብር ዓመቱ ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፪ እና ፶፫ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገው እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት እንዲካካስ የተደረገው በውጭ አገር የተከፈለ ታክስ ከተቀነሰ በኋላ ግብር ከፋዩ በልዩነት የሚፈለግበትን ግብር ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ።

፬· ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ከተሰላው ግብር የበለጠ ከፍሎ የተገኘ እንደሆነ ፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በአንቀጽ ፷፯ በተደነገገው መሠረት የገቢውን ማስታወቂያ ትክክለኛነት ባረጋገጠ በ፺ (ዘጠና) ቀናት ውስጥ በብልጫ የተከፈለውን ለግብር ከፋዩ መመለስ አለበት ።

፭· በገቢ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው እና በዘመኑ መከፈል ያለበት ግብር ፣ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተወሰነ ግብር ሆኖ ይቆጠራል ። ሆኖም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ ያለ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ውሣኔውን በዚያው መጠን በማሻሻል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ይሰጣል ።

፷፯· የሠንጠረዥ "መ" ገቢን ስለማስታወቅና ግብርን ስለመወሰን

፩· የመጨረሻ ታክስ ሆኖ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ በሚደረገው ግብር የማይሸፈን የሠንጠረዥ "መ" ገቢ ያገኘ ማንኛቸውም ግብር ከፋይ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚያወጣው ቅጽ መሠረት ገቢውን ማስታወቅ አለበት ። ግብር ከፋዩ የዚህ ዓይነቱን የገቢ ማስታወቂያ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሚያቀርበው የኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ከተጠናቀቀ ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ነው ።

፪· በገቢ ማስታወቂያው መሠረት ከተሠላው ግብር ላይ በግብር ዓመቱ ውስጥ በአንቀጽ ፯ መሠረት እንዲካካስ የተደረገው በውጭ አገር የተከፈለ የሠንጠረዥ "መ" ታክስ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪውን ሂሳብ ግብር ከፋዩ ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት ።

፫· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ መኖሩን ካላረጋገጠ በስተቀር በገቢ ማስታወቂያው ላይ የተመለከተው በዓመቱ መከፈል የሚገባው ግብር ፣ በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተወሰነ ግብር ሆኖ ይቆጠራል።

፷፰· የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ገቢ በቁርጥ ስለመወሰን

፩· የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን የግብር ግዴታ ለመወሰን የቁርጥ ግብር አወሳሰን ዘዴ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

፪· የቁርጥ ግብር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ውስጥ በተመለከተው በንግድ ሥራው ዓይነት ፣ በንግዱ ሥራ ስፋት ፣ የንግዱ ሥራ በሚገኝበት ቦታ ያሉትን ልዩነቶች የሚያንፀባርቅ የቁርጥ ግብር አወሳሰን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ የሚወሰን የግብር መጠን ነው ። የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚፈቅደው መሠረት ግብሩን በየጊዜው ለመክፈል ካልጠየቀና ካልተፈቀደለት በስተቀር ግብር ከፋዩ የቁርጥ ግብሩን በየዓመቱ ከሐምሌ ፩ ቀን እስከ ሐምሌ ፴ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት ።

66. Declaration and Assessment of Schedule B and C Income

1) Every taxpayer who has Schedule B or Schedule C income shall prepare a declaration of his income in a form prescribed by the Tax Authority. Taxpayers shall submit the tax declaration to the Tax Authority at the time of submitting the balance sheet, and the profit and loss account for that tax year within the time prescribed below:
   (a) Category A taxpayers within 4 months from the end of the taxpayers tax year.
   (b) Category B taxpayers within 2 months from the taxpayers tax year.

2) The type of records to be submitted to the Tax Authority in accordance with Sub-Article (1) above shall be determined by Regulatons to be issued by the Council of Ministers.

3) The tax calculated in accordance with the tax declaration, reduced by the tax with heldin accordance with Articles 52 and 53 of this Proclamation and the amounts provided by Article 7 (foreign tax credit) of this Proclamation during the tax year, shall be transferred by the taxpayer to the Tax Authority simultaneously with the tax declaration.

4) Any excess payments over the tax calculated according to Sub-Article (3) of this Article shall be refunded by the Tax Authority to the taxpayer within ninety (90) days of becoming satisfied on the tax declaration.

5) The amount of tax due for the year, as stated in the declaration, shall be the amount assessed by the Tax Authority although the Tax Authority may determine that an error or omission has been made and therefore may issue an amended assessment.

67. *Declaration and Assessment of Schedule D Income*

1) Every taxpayer who has Schedule D income, not subject to withholding at source constituting a final tax, shall prepare a declaration of that income in a form prescribed by the Tax Authority. Taxpayers shall submit this declaration to the Tax Authority within two (2) months from the end of the Ethiopian Fiscal Year.

2) The tax calculated in accordance with the declaration, after the amounts provided by Article 7 (foreign tax credit) paid during the year with respect to the Schedule D income subject to declaration having been reduced, shall be transferred by the taxpayer to the Tax Authority simultaneously with the declaration.

3) The amount of tax due for the year, as stated in the declaration, shall be the amount assessed by the tax Authority unless the Tax Authority determines that an error or omission has been made.

68. *Standard Assessment for Category C Taxpayers*

1) A standard assessment method shall be used to determine the income tax liability of Category C taxpayers.

2) The standard assessment shall be a fixed amount of tax determined in accordance with a Council of Ministers Regulations establishing a schedule of standard assessment amounts that reflect variations in the type of business, business size, and business location. The taxpayer shall pay the tax determined in accordance with standard assessment on the 7th day of July to the 6th day of August every year, unless, the taxpayer requested and is allowed to make installment payments in accordance with Council of Ministers Regulations.

፫· የቁርጥ ግብር መጠን በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ እና ለማሻሻያው መሠረት የሚሆኑ ጉዳዮች ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ ። ሚኒስትሩ የተሻሻለውን የቁርጥ ግብር መጠን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያሠራጫል ።

፷፱· ግብርን በግምት ስለመወሰን

፩· ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብና ሠነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሠነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ፣ ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን ይችላል ።

፪· ግብር በግምት የሚወሰንበት አኳኋን በገቢዎች ሚኒስትር በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል ።

፸· ገቢን ማጣመር

ግብር ከፋዩ በአንድ ሠንጠረዥ ሥር ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከተለያየ የገቢ ምንጭ የሚያገኝ ሲሆን ግብሩ የሚወሰነው ገቢውን በማጠቃለል ይሆናል ።

፸፩· ይርጋ

፩· ግብር ከፋዩ በዚህ አዋጅ በተመለከተው ጊዜ ውስጥና አኳኋን የገቢ ማስታወቂያውን ያቀረበ ከሆነ ፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የቀረበውን ማስታወቂያ አስተ ካክሎ ግብሩን መወሰን የሚችለው በ፭ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው ። ይህም የ፭ ዓመት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የገቢ ማስታወቂያው መቅረብ ካለበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ይሆናል ።

፪· ግብር ከፋዩ በዚህ አዋጅ በተመለከተው አኳኋን የገቢ ማስታወቂያውን ያቀረበ ሆኖ ፣ ማስታወቂያው የቀረበው ገቢን ለማስታወቂያ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ የሆነ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በ፭ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቀረበውን ማስታወቂያ አስተካክሎ ግብሩን መወሰን ይችላል ። ይህም የ፭ ዓመት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የገቢ ማስታወቂያውን ከተቀበለበት ቀን አንስቶ ነው ።

፫· ግብር ከፋዩ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የተጭበረበረ የገቢ ማስታወቂያ ያቀረበ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በማናቸውም ሌላ ሕግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ግብሩን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል ።

ክፍል አምስት

የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ

፸፪· የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ይዘት

እያንዳንዱ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የሚከተሉትን አሟልቶ መያዝ አለበት፤

፩· ጠቅላላ ገቢንና በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀናሽ የሚሆኑትን ወጪዎች ፤

፪· ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ፤

፫· ተፈፃሚነት የሚኖረውን የማስከፈያ ልክ ወይም መቶኛ ፤

፬· የተከፈለውንና ቀሪውን ግብር ፤

፭· ማናቸውንም መቀጫ ወይም ወለድ ፤

፮· የግብር ከፋዩን ስም ፣ አድራሻ ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

፯· የግብሩን አወሳሰን ዘዴ እና ግብር ከፋዩ ስላለው መብት አጭር ማብራሪያ ።

፸፫· የግብር ውሣኔ ማስታወቂያዎች ስለሚደርሱበት ሁኔታ

፩· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለግብር ከፋዩ የሚሰጣቸው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያዎች ወይም ሌሎች ማስታወቂያዎች በሚከተለው ሁኔታ ለግብር ከፋዩ በጽሑፍ ይደርሳሉ።

(ሀ) ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነ ሰው በአደራ ፖስታ ፣ ወይም በቀጥታ ለግብር ከፋዩ በእጁ በመስጠት ወይም እሱ የሌለ እንደሆነ ፣ ከቤተሰቦቹ ውስጥ ለማንኛውም አካለ መጠን ለደረሰ ወይም በመኖሪያው ወይም የሙያ ወይም የንግድ ሥራ በሚሠራበት ሥፍራ ቀጥሮ ለሚያሰራው ማንኛውም ሰው በመስጠት ፣ ሆኖም ማስታወቂያውን የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ይኸው ማስታወቂያ በግብር ከፋዩ መኖሪያ ቤት በር ላይ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ክፊል በሆነ ወይም በንግድ ሥራ አመቺ ሥፍራ በመለጠፍ ፤

ለ) ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሆነ ድርጅት በአደራ ፖስታ አማካኝነት በተመዘገበው የድርጅቱ አድራሻ በመላክ ወይም በድርጅቱ የንግድ ሥራ ቦታ ለሚገኘው ማንኛውም የሥራ መሪ ወይም ተቀጣሪ በመስጠት ፤

3) The period during which the standard assessment amount will be used and the basis for the revised amount shall be determined by a directive to be issued by the Minister. The Minister shall distribute the revised standard assessment to the tax Authorities.

69. *Assessment by Estimation*

1) If no records and books of accounts are maintained by the taxpayer, or if, for any reason, the records and books of accounts are unacceptable to the Tax Authority, or if the taxpayer fails to declare his or its income within the time prescribed by this Proclamation, the Tax Authority may assess the tax by estimation.

2) The manner of assessing tax by estimation shall be determined by directives to be issued by the Minister of Revenue.

70. *Aggregation*

A taxpayer who derives income from different sources subject to the same schedule shall be assessed on the aggregate of such income.

71. *Limitations*

1) If a taxpayer has submitted a declaration of income within the time limit and manner as prescribed in this Proclamation, the Tax Authority has five (5) years to amend the assessment. The five-year assessment period runs from the due date of the declaration.

2) If a taxpayer has submitted a declaration in the manner required by this Proclamation, but after the due date for making a declaration, the Tax Authority has five (5) years to amend the assessment. The five years assessment period runs from the date the declaration was received by the Tax Authority.

3) In case where the taxpayer has not declared his income or has submitted a fraudulent declaration, not time limit provided in any other law shall bar the assessment of the tax by the Tax Authority.

SECTION V

*Assessment Notification*

72. *Contents of Assessment Notification*

Every assessment notification shall contain the following elements:

1) gross income and deductions applicable under this Proclamation;
2) taxable income;
3) rates applicable or percentage;
4) taxes paid and due;
5) any penalty or interest;
6) the taxpayer's name, address, and TIN; and
7) a brief explanation of the assessment and a statement of the taxpayer's rights.

73. *Service of Tax Notices*

1) Income tax assessment notices or other notices issued by the Tax Authority to any taxpayer shall be communicated in writing as follows:

(a) In the case of a resident individual, by registered letter or by delivery to the taxpayer in person, or if he is absent, to any adult member of his family or any person employed by him at his residence, or place of business or, professional practice, provided that, if, no person can be found to accept such service, then, the same may be effected by affixing the notice to the door or other available part of the said residence or place of business.

(b) in the case of a resident body, by registered letter to the registered address of the body or by delivery to any director or employee of the body at any of its places of business.

ሐ) ተቀማጭነታቸው በኢትዮጵያ ላልሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ላለው ወኪል ወይም ወኪሎች በእጅ በመስጠት ወይም የማይገኙ ከሆነ ወኪሉ በሚሠራበት የንግድ ሥራ ቦታ ወይም በሌላ አመቺ በሆነ ሥፍራ በመኖሪያ ቤቱ ላይ በመለጠፍ ፣

ከእነዚህ እርምጃዎች አንዱም በማንኛውም ምክንያት ካልተሳካ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ማንኛውም ጋዜጣ ላይ በማሳተም ሊፈፀም ይችላል ፣ ለማሳተሚያ የወጣው ወጪ በግብር ከፋዩ ላይ ይታሰባል።

፪· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለግብር ከፋዩ አግባብ ባለው መንገድ የሰጠው ማንኛውም የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ይሆናል ፤

ሀ) ግብር ከፋዩ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ (፴) ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ግብር ካልከፈለ ወይም ለግብር ይግባኝ ጉባዔ ይግባኝ ካላቀረበ፣ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የግብር ይግባኝ ጉባዔ የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ያልቀረበበት ከሆነ፣ ወይም

(ሐ) የይግባኝ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠ ።

፫· በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የመጨረሻና ተፈፃሚ በሚሆነው የግብር ውሣኔ መሠረት የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ ግብር ከፋይ ጥፋተኛ ነው ።

## ክፍል ስድስት
## ክፍያ

፸፬· ግብር በሕግ በተወሰነው ጊዜ መከፈል ያለበት ስለመሆኑ

ማናቸውም በተወሰነ ቀን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ያለበት ግብር (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የተያዘ ወይም የተሰበሰበ ታክስ ጭምር) በዚሁ በተወሰነው ቀን ገቢ መደረግ አለበት ። በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ግብርን ያለመክፈል ወለድ እና ገቢው ለዘገየበት መቀጫ የመክፈል ግዴታን ያስከትላል ።

፸፭· ወለድ

፩· ማንኛቸውም ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ ፤ ግብር መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከተከፈለበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው የግብር መጠን ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት ።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ ፳፭ ፐርሰንት (ሃያ አምስት በመቶ) ታክሎበት ይሆናል።

፫· ወለዱ የሚሰበሰበው ወለድ የሚከፈልበት ግብር በሚሰበሰብበት ዓይነት ነው ።

፸፮· ማካካሻ እና ተመላሽ ሂሳብ

፩· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ የተደረገው ወይም በየጊዜው የተከፈለው ግብር ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የተከፈለ ግብር ፣ ግብር ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ግብር በላይ መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ፣

ሀ) ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ ታክስ ግብር ከፋዩ ለሚፈለግበት ፦

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚከፈሉ ሌሎች ግብሮች

፪· በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለሚቀረው ግብር፣

፫· በዚህ አዋጅ ወይም በሌሎች የግብርና የቀረጥ ሕጎች መሠረት ግብር ከፋዩ ለሚፈለግበት ሌላ ማናቸውም የገንዘብ መጠን ፣ እንዲካካስ ማድረግ ፣

ለ) የሂሳቡን ትክክለኛነት ባረጋገጠ በዘጠና ቀናት ጊዜ ውስጥ ተራፊውን ሂሳብ ለግብር ከፋዩ መመለስ ፣ አለበት።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ግብር ከፋዩ ተመላሹን ሂሳብ ያላገኘ እንደሆነ ባለፈው ሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ልክ ላይ ፳፭ ፐርሰንት (ሃያ አምስት በመቶ) ታክሎበት ወለድ ይከፈለዋል ።

(c) in the case of non-resident persons, to their agent or agents in Ethiopia, or by affixing to the door or other available part of the residence or place of business of such agent if he could not be served in person;

Provided that, if in any case none of these measures are effective, service may be discharged by the publication in any newspaper in which Court notice may be advertised. The cost of such publication shall be charged to the taxpayer.

2) Any assessment of income tax duly served on the taxpayer shall become final when:

(a) the taxpayer fails to pay the tax due or to lodge his or its appeal with the Tax Appeal Commission within thirty (30) days from the date of receipt of an assessment notice or from the date of decision of the review committee,

(b) the time for appealing the decision of the Tax Appeal Commission has expired; or

(c) the Court of Appeal renders its final decision.

3) A taxpayer who does not pay the final assessment as provided under Sub-Article (2) of this Article is in default.

## SECTION VI
## Payment

74. *Tax Payable when Due*

Any tax (including whithheld or collected tax) that is to be paid to the Tax Authority by a stated date shall be payable on that date. Failure to make a timely payment shall result in the imposition of interest and the late payment penalty.

75. *Interest*

1) If any amount of tax is not paid by the due date, the taxpayer is obliged to pay interest on such amount for the period from the date the tax is due to the date it is paid.

2) The interest rate under Sub-article (1) of this Article is set at 25% (twenty five percent) over and above the highest commercial lending interest rate that prevailed during the preceding quarter.

3) Interest shall be collected in the same manner as the tax to which it relates.

76. *Credit and Refund*

1) Where the Tax Authority is satisfied that tax has been paid by a person, whether by withholding, installments, or otherwise, in excess of the person's tax libality to which the payment or payments relate, the Tax Authority shall:

(a) credit the overpaid tax against any liability of that person in respect of:

(i) other taxes under this Proclamation;

(ii) withholding of tax under this Proclamation;

(iii) any other amount due to the Tax Authority under this Proclamation; or any other tax law; and

(b) refund the remainder to that person within 90 days of becoming satisfied.

2) The Tax payer shall be entitled to an interest set at the highest commercial lending interest rate increased by 25% (twenty five percent) that prevailed during the preceding quarter if he/it has not received the refund within the time prescribed under Sub-Article (1) (b) of this Article.

፫· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተነገረው ሳይወሰን ግብር ከፋዩ በብልጫ የከፈለው ግብር እንዲመለስለት በዚህ አንቀጽ መሠረት ለመጠየቅ ይችላል ። በብልጫ የተከፈለ ግብር እንዲመለስ የሚቀርብ ጥያቄ ከዚህ ቡታች ከተዘረዘሩት ዘግይቶ ከተፈፀመው ጀምሮ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን በጽሑፍ መቅረብ አለበት፣

ሀ) የተመላሽ ጥያቄ ከሚቀርብበት ግብር ጋር በተያያዘ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለግብር ከፋዩ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን፣

ለ) ግብሩ ወይም ወለዱ ከተከፈለበት ቀን።

፬· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በቀረበ የተመላሽ ጥያቄ ላይ ውሣኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፵፭ ቀናት ውስጥ የተመላሽ ጥያቄ ላቀረበው ግብር ከፋይ የተሰጠውን ውሣኔ የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽሑፍ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት ።

፭· በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በተሰጠ ውሣኔ ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ውሣኔው የግብር ውሣኔ እንደሆነ ተቆጥሮ በይግባኝ ሥርዓት መሠረት በውሣኔው ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ።

## ክፍል ሰባት
## የግብር አሰባሰብ አፈፃፀም

### ፸፯· የግብር ከፋዩን ሀብት ስለመያዝ

፩· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ግብር የሚፈለግበት ሰው በአንቀጽ ፸፫(፫) በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የዚህን ግብር ከፋይ ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ግብር እና ንብረቱን ለመያዝ ለተደረገው ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ማድረግ ይችላል። የመንግሥት ሠራተኞችን ጨምሮ የማንኛውንም ሠራተኛ ደመወዝ ለሠራተኛው ደመወዝ የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ኃላፊ ማስታወቂያ በመስጠት እንዲያዝ ማድረግ ይቻላል።

፪· ለዚህ ክፍል አፈፃፀም "መያዝ" በማናቸውም መንገድ መያዝን እንዲሁም የግብር ከፋዩ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ግብር መሰብሰብን ይጨምራል ። በንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፮) በተነገረው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዙ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ፀንቶ ያለ ግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው ። የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብር ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ የፖሊስ ሠራዊት አባል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል ። ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከ፲ ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል ። ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል ።

፫· ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዙ ምክንያት የሆነውን የግብር ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፣ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከግብር ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የግብር ዕዳ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የግብር ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል ።

፬· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ባልተከፈለ የግብር ዕዳ ምክንያት በመቀጠር የሚገኝን ገቢ ወይም ሌላ ንብረት መያዝ የሚቻለው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሀብቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለግብር ከፋዩ በጽሑፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል ። በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሀብቱ ከመያዙ ከ፴ ቀን በፊት ለግብር ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል ።

3) Without limiting the generality of Sub-Article(1) of this Article, a person may apply for a refund under this Article. A refund application shall be made to the Tax Authority in writing within three (3) years of the later of:

(a) the date on which the Tax Authority has served the notice of assessment to which the refund application relates, or

(b) the date on which the tax or interest was paid.

4) The Tax Authority shall, within forty-five (45) days of making a decision on a refund application under Sub-Article 2, serve on the person applying for the refund a notice in writing of the decision.

5) A person dissatisfied with a decision referred to in Sub-Article 4 may challenge the decision only through the appeal procedure as though the decision were that of an assessment.

## SECTION VII
## *Collection Enforcement*

### 77. Seizure of Property to Collect Tax

1) Subject to Sub-Article (4) of this Article, if any person liable to pay any tax imposed by this Proclamation is in default under Article 73(3), it shall be lawful for the Tax Authority to collect such tax 'and such further amount as shall be sufficient to cover the expenses of the seizure) by seizing any property belonging to such person. Seizure may be made on the accrued salary or wages of any employee, including a government employee, by serving a notice of seizure on the officer who has the duty of paying the salary or wages.

2) For purposes of this Section; the team "Sezure" includes seizure by any means, as well as, collection from a person who owes money or property to the taxpayer. Except as provided in Sub-Articles (3) and (6), a seizure shall extend only to property possessed and obligations existing at the time the seizure is made. The Tax Authority may request a police officer to be present during seizure. Where the Authority seizes any property as provided hereinabove, it shall have the right to sell the seized goods at public auction or in any other manner approved by the Authority within not less than 10 days after the seizure, except that when the goods seized are perishable the Authority can sell the goods after any reasonable period having regard to the nature of the goods.

3) Whenever any property on which seizure had been made is not sufficient to satisfy the claim for which seizure is made, the Tax Authority may, thereafter and as may be necessary, proceed to seize other property, liable to seizure, of the person against whom the claim exists until the amount due, together with all expenses, is fully paid.

4) Seizure may be made under Sub-Article (1) of this Article on employee's remuneration or other property of any person with respect or any unpaid tax only after the Tax Authority has notified such person in writing of its intention to make such seizure. The notice shall be delivered not less than thirty (30) days before the day of the seizure.

፭· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የ፴ ቀን የጊዜ ገደብ እና በንዑስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው የ፴ ቀን የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ግብሩ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ከቀረበና ግብር ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ግብር የመሰብሰቡ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል።

፮· ለግብር ከፋዩ የሚከፈለውን ደመወዝ የመያዝ አፈፃፀም ውጤት ደመወዙ እንዲያዝ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የግብሩ ዕዳ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ወይም የግብሩ ዕዳ በይርጋ ምክንያት ሊጠየቅ የማይችል እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል።

፯· ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ገቢዎች እና ንብረቶች ከመያዝ ነፃ ናቸው።

ሀ) በሠንጠረዥ "ሀ" ከግብር ነፃ ከተደረገው የገቢ መጠን ሳያልፍ ሠራተኛ የሚያገኘው ደመወዝ ወይም ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ሌላ ገቢ፣

ለ) በማናቸውም የኢትዮጵያ ሕግ እንዳይከበሩ የተደረጉ ገቢዎች ወይም ንብረቶች፣

## ፸፰· የንብረት መያዝ ውጤት

፩· በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በአንቀጽ ፴ በተመለከተው መሠረት በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በግብር ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለግብር ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቀው የያዘውን ሀብት የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈፀም ኃላፊነት አለበት።

፪· ማናቸውም ሰው የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሣይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል። ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የግብር ዕዳ መጠን (በግብሩ ዕዳ ላይ የሚታሰበውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ) ሊያልፍ አይችልም።

፫ በንዑስ አንቀጽ ፪ ከተመለከተው የግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን ፶ ፐርሰንት (ሃምሣ በመቶ) በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል።

፬· በዚህ አንቀጽ መሠረት በይዞታው ሥር ያለው ንብረት ያስረከበ ወይም በግብር ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን በተጠየቀው መሠረት ገቢ ያደረገ ማናቸውም ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የግብር ግዴታውን ባልተወጣው ግብር ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል።

## ፸፱· የሒሣብ መዝገብ ስለማቅረብ

ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት።

## ፹· በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ

፩· ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንሥቶ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ ባለሥልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

5) If the Tax Authority makes a finding that the collection of the tax is in jeopardy, a demand for immediate payment of such tax may be made by the Tax Authority and, on failure or refusal to pay the tax, collection thereof by seizure shall be lawful without regard to the 30-days period provided in Sub-Article (1) and the days provided in sub-Article (4).

6) The effect of a seizure on employee remuneration payable to a taxpayer shall be continuous from the date such seizure is first made until the liability out of which such seizure arose is satisfied or becomes unenforceable by reason of lapse of time.

7) The following shall be exempt from seizure:
   (a) such amount of employee remineration or other periodic income payable to an individual as does not exceed the exempt amount according to Schedule A; and
   (b) all other income and property that are not liable to attachment or lien under Ethiopian law.

## 78. *Enforcement of Seizure*

1. Any person in possession of (or obligated with respect to) property subject to seizure on which a seizure has been made shall, unless such property is, at the time of such demand, subject to an attachment or execution under any judicial process or is encumbered by law with the preferred right of other creditors as stipulated under Article 30, on the demand of the Tax authority surrender such property (or discharge such obligation)
2. Any person who fails or refuses to surrender any property subject to seizure, on demand of the Tax Authority, shall be personally liable to the government in a sum equal to the value of the property not so surrendered, but not exceeding the amount of taxes for the collection of which seizure has been made (together with costs and interest on such sum).
3. In addition to the personal liability imposed by Sub-Article (2), if the failure or refusal to surrender is without reasonable cause, such person shall be liable for an additional charge equal to fifty percent (50%) of the amount recoverable under Sub-Article (2).
4. Any person in possession of property who surrenders or makes payment in accordance with this Article shall be discharged from any obligation or liability to the delinquent taxpayer or to any other person arising from such surrender or payment.

## 79. *Production of Books*

If a seizure has been made or is about to be made on any property, any person having custody or control of any books or records containing evidence or statements relating to the property subject to seizure shall, on demand of the Tax Authority, exhibit such books or records to the Tax Authority.

## 80. *Preferential claim to Assets*

1. From the date on which tax becomes due and payable under this Proclamation, subject to the prior secured claims of creditors, the Authority has a preferential claim over all other claims upon the assets of the person liable to pay the tax until the tax is paid.

፪· ማንኛውም ሰው ግብር የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለውን ግብር እና ግብሩን ለማስከፈል የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የግብሩ ዕዳ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የጽሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን በመግለጽ ለግብር ከፋዩ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

፫· በንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለጸው ማስጠንቀቂያ የደረሰው ግብር ከፋይ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ፴ ቀን ውስጥ ግብሩን ያልከፈለ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለመዝጋቢው ባለሥልጣን የግብር ከፋዩ ሀብት ባልተከፈለው የግብር ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል።

፬· በንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ መዝጋቢው ባለሥልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዣ ሰነድ ይመዘግባል፣ ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ግብር ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል።

፹፩· <u>የግብር አወሳሰንን ሊያደናቅፍ የሚችል ሁኔታ መኖር</u>

የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የሚያሳምን በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ትዕዛዙን የሚደግፍ መግለጫ በማያያዝ የግብር ከፋዩ የባንክ ሂሣብ እንዲታገድ እና ስለግብር ከፋዩ የፋይናንስ እንቅስቃሴ መረጃ እንዲሰጠው የአስተዳደር ትዕዛዝ ሊሰጥ እና ግብሩን ወዲያውኑ መወሰን ይችላል። ይሁን እንጂ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከዚህ በላይ የተመለከተውን አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ካስተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት አሥር ቀናት ውስጥ ፍ/ቤት ትዕዛዙን እንዲያጸድቅለት ማድረግ አለበት። የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ሥልጣን መጠቀም የሚችለው የግብሩን አወሳሰን ግልጽ ለማድረግ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት ብቻ ነው።

፹፪· <u>ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በቀረ ግብር ላይ ስለሚኖር የይገባኛል ቅድሚያ</u>

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ ባለበት ሰው ተቀንሶ የተያዘ ግብር፣

ሀ) የተያዘው ግብር አስገቢውን ባለሥልጣን በመወከል ይሆናል፣

ለ) ግብሩን ቀንሶ የያዘው ሰው ላለበት ዕዳ ወይም ማናቸውም ሌላ ተጠያቂነት እንዲከበር ማድረግ አይቻልም።

ሐ) ግብሩን ቀንሶ የያዘው ሰው የከሰረ ወይም ሂሣቡ በመጣራት ላይ በሚሆንበት ጊዜ ተቀንሶ የቀረው ግብር በመጣራት ላይ ያለው፣ በዕዳ ምክንያት የሚተላለፈው ወይም የከሰረው ድርጅት ሀብት ክፍል ሆኖ አይቆጠርም። በመሆኑም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ ሂሣብ ላይ የሀብት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት የይገባኛል ቅድሚያ መብት ይኖረዋል።

፪· በዚህ አዋጅ መሠረት ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረው ግብር፣

ሀ) ከክፍያው ላይ በመጀመሪያ የሚቀነስ ይሆናል።

ለ) ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ወይም በማናቸውም ሕግ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ መቀነስ ካለበት ሌላ ሂሳብ በፊት ቅድሚያ ይኖረዋል።

፹፫· <u>ግብር ከፋዩ ስላለው ጥበቃ</u>

በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው፣ የሚጠበቀው፣ እና የሚመዘገበው በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ብቻ ይሆናል። ማናቸውም ሌላ የመንግሥት አካል በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘውን ንብረት ማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሠረት በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም። በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ግብር ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል።

2) Where a person is in default of paying tax, the Authority may, by notice in writing, inform that person of the Authority's intention to apply to the Registering Authority to register a security interest in any asset situated in Ethiopia which is owned by that person, to cover any unpaid tax in default, together with any expense incurred in recovery proceedings.

3) If the person on whom a notice has been served under Sub-Article (2) fails to pay the amount specified in the notice within 30 days after the date of service of the notice, the Authority may, by notice in writing, direct the Registering Authority that the asset, to the extent of the defaulter's interest therein, shall be the subject of security for the total amount of unpaid tax.

4) Where the Authority has served a notice on the Registering Authority under Sub-Article (3), the Registering Authority shall, without fee, register the notice of security as if the notice were an instrument of mortgage over or charge on such asset, as the case may be, and such registration shall, subject to any prior mortgage or charge, operate while it subsists in all respects as a legal mortgage over or charge on the land or building to secure the amount due.

81. *Jeopardy Assessment*

In exceptional cases where the Tax Authority has reasonable grounds to believe that the collection of tax is in jeopardy, and where a state of urgency exists, the Tax Authority may issue an administrative order to the Bank with a statement of justification supplementing its order to block the accounts of the taxpayer and secure information thereon, and may make an immediate assessment of tax for the current period; provided, however; that the Tax Authority shall obtain court authorization within ten (10) days from the date of issuance of its administrative order and further that such powers may only be used to elucidate information relevant to the assessment.

82. *Priority of claim on Tax Withheld*

1) Tax withheld by a withholding agent under this Proclamation:

(a) is held by the withholding agent in trust for the Tax Authority;

(b) is not subject to attachment in respect of a debt or liability of the withholding agent; and

(c) in the event of liquidation or bankruptcy of the withholding agent, does not form part of the estate in liquidation, assignment, or bankruptcy and the Tax Authority has a first claim before any distribution of property is made.

2) An amount that a withholding agent is required under this Proclamation to withhold from a payment is:

(a) a first charge on that payment; and

(b) withheld prior to any other deduction which the withholding agent may be required to make by virtue of an order of any court or any other law.

83. *Taxpayer Safeguards*

Any property seized under this Section shall be seized, held, and accounted for only by the Tax Authority. No other agency of the government may require the property seized under this section to be transferred or given over to it for any cause whatsoever. If any property seized under this Section is sold, any portion of the proceeds in excess of the taxpayer's liabilities under this section shall be returned promptly to the owner of the property.

## ክፍል ስምንት
## ሽልማቶች እና አስተዳደራዊ መቀጫዎች

**፹፬· ለተረጋገጠ መረጃ ስለሚሰጥ ሽልማት**

፩· ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በሚደብቅ፣ አሳንሶ በሚያስታውቅ፣ በሚያጭበረብር ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሳይከፍል በሚቀር ግብር ከፋይ ላይ በተጨበጭ መረጃ በመደገፍ ሪፖርት የሚያቀርብ ሰው፣ የተደበቀውን ግብር እስከ ሃያ በመቶ (፳ ፐርሰንት) ድረስ ግብሩ ሲሰበሰብ እንዲያገኝ ይደረጋል።

፪· ይሁን እንጂ መረጃ አቅራቢው፣
ሀ) የግብር አለመከፈሉ ድርጊት ተካፋይ ከሆነ፣ ወይም
ለ) ይህን ማድረግ የሥራው አንድ አካል ከሆነ፣
የዚህ ሽልማት ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም።

፫· ዝርዝሩ የግብር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**፹፭· ለከፍተኛ የሥራ ውጤት ስለሚሰጥ ሽልማት**

፩· የግብሩ ባለሥልጣን እርአያነት ባለው ሁኔታ የግብር መክፈል ግዴታቸውን ለሚወጡ ግብር ከፋዮች እና ከፍተኛ የሥራ ብቃት ለሚያሳዩ የግብር ባለሥልጣኑ ሠራተኞች ሽልማት ይሰጣል።

፪· ዝርዝሩ የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**፹፮· ገቢን ባለማስታወቅ ወይም ዘግይቶ በማስታወቅ የሚከፈል መቀጫ**

ማንኛውም ግብር ከፋይ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ የሚከተለውን መቀጫ ይከፍላል፤
ሀ) ገቢውን ሳያስታውቅ ለዘገየበት ለመጀመሪያው ፴ ቀን ወይም የዚህ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር ፩ ሺህ፣
ለ) ገቢውን ሳያስታውቅ ለዘገየበት ለተጨማሪው ፴ ቀን ወይም የዚሁ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር ፪ ሺህ፣
ሐ) ከዚህ በላይ ላለው ገቢውን ሳያስታውቅ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ፴ ቀን ብር ፩ ሺህ አምስት መቶ።

**፹፯· ግብርን አሳንሶ በማስታወቅ የሚከፈል መቀጫ**

፩· ማናቸውም ግብር ከፋይ በገቢ ማስታወቂያው ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር አሳንሶ ያስታወቀ እንደሆነ ያሳነሰውን ግብር መጠን አሥር በመቶ (፲ ፐርሰንት) ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እንደተመለከተው የተቀነሰው ገቢ ከፍተኛ የሆነ እንደሆነ አሳንሶ ያስታወቀውን ግብር ሃምሳ በመቶ (፶ፐርሰንት) መቀጫ ይከፍላል።

፪· ግብር ከፋዩ አሳንሶ ያስታወቀው ግብር ከፍተኛ ነው የሚባለው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ከ፦ ስተኛው የበለጠ እንደሆነ ነው፤
ሀ) በገቢ ማስታወቂያ መታየት ካለበት ግብር ፳፭ ፐርሰንት (ከሃያ አምስት በመቶ)፣

፫· ግብር ከፋዩ ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙን የሚመረምረው የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ወይም ፍርድ ቤት የመጨረሻውን ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ የመቀጫው ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

**፹፰· አዘግይቶ በመክፈል የሚጣል መቀጫ**

ማናቸውም ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልከፈለ እንደሆነ የሚከተለው መቀጫ ይጣልበታል፣
ሀ) ግብሩ ሊከፈል ከሚገባው ቀን ለአንድ ቀን ከዘገየ ያልተከፈለውን ግብር ፭ ፐርሰንት (አምስት በመቶ)፣
ለ) ከዚህ በኋላ ላለው ለእያንዳንዱ ወር የመጀመሪያ ቀን ሳይከፈል የቀረውን ግብር ሁለት በመቶ (፪ ፐርሰንት)፣

**፹፱· ተገቢን የሂሣብ መዝገብ ባለመያዝ የሚጣል መቀጫ**

፩· ማናቸውም ግብር ከፋይ ለአንድ የተወሰነ የግብር ዘመን መያዝ የሚገባውን ተገቢ የሂሣብ ሰነድ፣ የሂሣብ መዝገብ እና መግለጫ ያልያዘ እንደሆነ የተወሰነበትን ግብር ፳ ፐርሰንት መቀጫ ይከፍላል፤

፪· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ ተገቢውን የሂሣብ መዝገብ፣ ሰነድ እና ሌሎችንም መረጃዎች ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሳይዝ የቀረ መሆኑን ሲደርስበት፣

## SECTION VIII
## *Rewards and Administrative Penalties*

84. *Reward for Verifiable Information*

1) Where a person provides a verifiable and objective information of tax evasion through concealment, under reporting, fraud or any other improper means, the informer shall be granted upto twenty percent (20) of the amount of tax evaded at the time of collection of the said tax.

2) The informer shall not be entitled to such a reward where:
(a) he/she has participated in the tax evasion; or
(b) where such reporting is part of his/her employment duty.

3) Details shall be provided by the directives of the Tax Authority

85. *Reward for Outstanding Performance*

1) The Tax Authority shall reward tax payers and tax officers for outstanding performance and discharge of duties.

2) Details shall be provided by the directives of the Minister of Revenue.

86. *Penalty for Late Filing or Non-Filing*

A taxpayer who fails to file a timely tax declaration is liable for a penalty equal to:
(a) 1,000 Birr for the first thirty (30) days (or part thereof) the declaration remains unfiled);
(b) 2,000 Birr for the next thirty (30) days (or part thereof) the declaration remains unfiled);
(c) 1,500 Birr for each thirty (30) days (or part thereof)thereafter that the declaration remains unfiled.

87. *Penalty for Understatement of Tax*

1) If the amount of tax shown on a declaration understates the amount of tax required to be shown, the taxpayer is liable for a penalty in the amount of 10% (ten per cent) of the understatement or 50% (fifty per cent) if the understatement is considered substaintial in accordance with Sub-Article (2) of this Article).

2) The understatement is considered substantial if it exceeds the smaller of the following two amounts:
(a) twenty-five percent (25%) of the tax required to be shown on the return; or
(b) 20,000 Birr.

3) The penalty shall continue to apply until, the Appeal Commission or a Court, as the case may be, shall have rendered its final decision.

88. *Penalty for Late Payment*

A taxpayer who fails to pay tax liability on the due date is subject to:
(a) a penalty of 5% (five percent) of the amount of unpaid tax on the first day after the due date has passed; and
(b) an additional 2 % (two percent) of the amount of the tax that remains unpaid on the first day of each month thereafter.

89. *Penalty for Failure to Keep Proper Records*

1) The taxpayer shall be liable for a penalty of 20% of the tax assessed if he failed to keep proper books of account, records, and other documents regarding a certain tax year.

2) If the Tax Authority finds that a taxpayer has failed for two consecutive tax years, to keep proper books of account, records, and other documents:

ሀ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ ሲልክለት ፈቃድ ሰጪው መ/ቤት የግብር ከፋዩን የንግድ ሥራ ፈቃድ ወዲያውኑ ያግዳል።

ለ) ግብር ከፋዩ ተገቢውን የሂሣብ መዝገብ፣ ሰነድ እና ሌሎችንም መረጃዎች በሦስተኛው ዓመትም ያላቀረበ እንደሆነ፣ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ ሲደርሰው ፈቃድ ሰጪው መ/ቤት የግብር ከፋዩን የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሠርዛል።

ሐ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ መዝገብ የመያዝ ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑን ሲደርስበት ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሠረዝ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚልከው ማስታወቂያ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጠ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ሆኖ ይቆጠራል። ስለሆነም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ ግዴታውን ያልተወጣ ለመሆኑ የመጨረሻ ማረጋገጫ ከማግኘቱ በፊት ማስታወቂያውን መላክ የለበትም።

፺· ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ባለማድረግ የሚጣል መቀጫ

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ቀንሶ ገቢ ያላደረገውን የግብር መጠን ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት። ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት የከፈለውን ሂሣብ ከግብር ከፋዩ መልሶ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

፪· ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ማንኛውም ግብር ከፋይ ያለበት ኃላፊነት ይኖርበታል። በመሆኑም ገቢ እንዲያደርግ የተጠየቀውን የግብር መጠን የመቃወም ወይም ቀደም ሲል የከፈለው ታክስ እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው።

፫· በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ያላደረገ ሰው በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ተገቢውን ግብር ቀንሶ ገቢ ሳያደርግ ለፈፀመው ክፍያ ብር ፩ ሺ መቀጫ ይከፍላል።

፬· ከዚህ በላይ ከተደነገገው መቀጫ በተጨማሪ የሚከተሉት ግለሰቦች ከዚህ በታች የተወሰነውን መቀጫ እንዲከፍሉ ይደረጋል፤

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተመለከተው ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ያለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ ያለበት ሥራ አስኪያጅ፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተመለከተው ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ያለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ የነበረበት እና ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረጉን ሥርዓት የመከታተል ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሆኖ ክትትሉን ወይም ቁጥጥሩን በተገቢው መንገድ ባለማከናወኑ ግብሩ ተቀንሶ ገቢ ላለመደረጉ ምክንያት የሆነ የሂሣብ ኃላፊ ወይም ማንኛውም ሌላ ኃላፊ ብር ፩ ሺ መቀጫ ይከፍላሉ።

፺፩· የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ባለመጠቀም የሚጣል መቀጫ

፩· ግብር ከፋዩ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ እንደሆነ ግብር ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው ከተከፋዩ ሂሣብ ላይ ፴ ፐርሰንት (ሠላሳ በመቶ) ቀንሶ ገቢ ያደርጋል።

፪· ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ለሚገባው ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ ግብር ከፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው በተጨማሪ ብር ፭ ሺ (አምስት ሺ ብር) ወይም ሊከፈለው የሚገባውን ሂሣብ ከሁለቱ አነስተኛውን በመቀጫ መልክ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን እንዲከፍል ይደረጋል።

፺፪· መቀጫን ስለመሰብሰብ እና በመቀጫ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

አስተዳደራዊ መቀጫ ከግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሚሰጥ ማስታወቂያ እና የክፍያ ጥያቄ ወዲያውኑ መከፈል አለበት። ስለሆነም የመቀጫ አወሳሰን እና አሰባሰብ ግብር በሚወሰንበት እና በሚሰበሰብበት አፈፃፀም ይመራል። በዚህ አዋጅ ውስጥ "የተወሰነ ግብር" በሚል የተጠቀሰ አስተዳደራዊ መቀጫን ይጨምራል።

(a) the licensing authority shall forthwith suspend the taxpayer's license on notification by the Tax Authority;

(b) if in a subsequent year, the Tax Authority again finds that the taxpayer has failed to keep proper books, records, and documents, the licensing authority shall revoke the taxpayer's license on notification by the Tax Authority;

(c) A finding by the Tax Authority that the taxpayer's failure justifies notification of the licensing authority for purposes of suspension or revocation of the taxpayer's license shall for all purposes of this Proclamation be treated as an ssessment and notification may not be sent to the licensing authority until the Tax Authority's finding is final.

90. *Penalty for Failure to Withhold Tax*

1) A withholding agent who fails to withhold tax in accordance with this Proclamation is personally liable to pay to the Tax Authority the amount of tax which has not been withheld, but the withholding agent is entitled to recover this amount from the payee.

2) The tax withholding liability imposed by this Proclamation shall be treated as a tax liability for purposes of any Article providing taxpayers with the right to contest the amount of tax due or to recover tax paid.

3) In addition to any amount for which a withholding agent is liable under Sub-Article (1), an agent who fails to withhold tax in accordance with this Proclamation shall be liable for a penalty of 1,000 Birr for each instance of failure to withhold the proper amount.

4) A penalty of Birr 1,000 is imposed on the following individuals:

(a) a manager who knew or should have known of the failure described in Sub-Article (1);

(b) a chief accountant or another senior officer who is responsible for supervision or control of withholding procedures and who knew or should have known of the failure described in Sub-Article (1), or whose improper supervision failed to prevent it.

91. *Penalty for Failure to Meet TIN Requirements*

Taxpayers failing to meet the requirements for TIN are subject to the following penalties:

1) a withholding agent who makes a payment to a person who has not supplied a TIN is required to withhold thirty percent (30%) of the amount of the payment.

2) a taxpayer who has not supplied the TIN to the withholding agent, in addition to what is stipulated under Sub-Article (1) of this Article is liable to pay a fine of 5,000 Birr or the amount of the payment, whichever is less.

92. Collection of and Appeal Against Penalties

Administrative penalities shall be paid on notice and demand by the Tax Authority and shall be assessed and collected in the same manner as taxes. Any references, in this Proclamation, to "tax imposed" shall be deemed to include administrative penalties imposed.

፺፫· ግብር ከፋዩን ከመቀጫ ነፃ ስለማድረግ

የገቢ ማስታወቂያው ከመመርመሩ በፊት ግብር ከፋዩ በራሱ ተነሳሽነት ወደተሳሳተ የግብር ውሣኔ እና አፈፃፀም ሊያመሩ የሚችሉ ስህተቶችን ያረመ እንደሆነ፣ ከግብር እና ከወለድ በስተቀር፣ በዚህ አዋጅ የተጣለውን መቀጫ ከመክፈል ነፃ ይደረጋል።

ክፍል ዘጠኝ
የወንጀል ጥፋቶች

፺፬· በግብር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ-ሥርዓት

በግብር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው ፣ የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይሆናል ።

፺፭· በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ላይ ስለሚፈፀም ጥፋት

ማንኛውም ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ይዞ የተገኘ እንደሆነ በያዘው በእያንዳንዱ ተጨማሪ መለያ ቁጥር ልክ ከብር ፳ሺህ (ሃያ ሺ ብር) በማያንስና ከብር ፶ ሺህ (ሃምሣ ሺህ ብር) በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በእያንዳንዱ ተጨማሪ መለያ ቁጥር ልክ በአምስት ዓመት እሥራት ይቀጣል ።

፺፮· ሕግን በመጣስ ግብር ስላለመክፈል

ማንኛውም ግብር ከፋይ ሕግን በመጣስ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ግብር ያልከፈለ እንደሆነ ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል ። ስለሆነም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፮ መሠረት ገቢውን አሳንሶ በማስታወቁ ምክንያት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ፭ ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል ።

፺፯· የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ

፩· ማናቸውም ግብር ከፋይ ፦
   ሀ) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ አንድን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ፣ ወይም
   ለ) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፣
   የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል።

፪· የሐሰት መግለጫው የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያ የሆነ እንደሆነ ፣
   ሀ) የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ግብር ከብር ፩ ሺህ በማይበልጥ፣ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ግብር ከፋዩ ከብር ፳ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል ።
   ለ) አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ግብር ከብር ፩ሺህ የሚበልጥ ከሆነ ከብር ፳ሺህ በማያንስ እና ከብር ፻ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፫· የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ፣
   ሀ) የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ግብር ከብር ፩ሺህ በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ግብር ከፋዩ ከብር ፶ ሺህ በማያንስ እና ከብር ፻ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ፣ እሥራት፣
   ለ) አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ግብር ከብር ፩ ሺህ የሚበልጥ ከሆነ ከብር ፸፭ ሺህ በማያንስ እና ከብር ፪፻ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፲ ዓመት በማያንስ እና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

93. *Exoneration of Taxpayer from Liability*

In the event that errors that led to incorrect determination and execution of tax obligations are corrected independently before commencement of a tax examination, the taxpayer shall be released from liability, with the exception of paying the tax and interest.

SECTION IX
Criminal Offences

94. *Procedure in Tax Offence Cases*

A tax offence is a violation of the criminal law of Ethiopia and shall be charged, prosecuted, and appealed in accordance with the Ethiopian criminal procedure law.

95. *TIN Violations*

If a person subject to tax is convicted of obtaining more than one TIN, that person shall be liable to pay a fine of not less than 20,000 Birr and not more than 50,000 Birr and to imprisonment of five (5) years per additional TIN obtained.

96. *Tax Evasion*

A taxpayer who evades the declaration or payment of tax commits an offense and, in addition to the penalty for the understatement of income referred to in Article 86, may be prosecuted and, on conviction, be subject to imprisonment for a term of not less than five (5) years.

97. *Making False or Misleading Statements*

1) A tax payer who:
   (a) makes a statement, to an officer of the Tax Authority, that is false or misleading in a material particular; or
   (b) omits from a statement made to an officer of the Tax Authority any matter or thing without which the statement is misleading in a material particular;

   commits an offence and is liable on conviction.
2) Where the statement or omission is made without reasonable excuse,
   (a) and if the inaccuracy of the statement undetected may result in the underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, the tax payer shall be liable to a fine of not less than 10,000 Birr and not more than 20,000 Birr, and imprisonment for a term of not less than one (1) year and not more than three (3) years, and
   (b) if the underpayment of tax is in an amount exceeding Birr 1,000, he shall be liable to a fine of not less than twenty thousand Birr and not more than 100,000 Birr and imprisonment for a term of not less than three (3) years and not more than five (5) years.
3) Where the statement or omission is made knowingly or recklessly,
   (a) and if the inaccuracy of the statement undetected may result in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, to a fineo f not less than 50,000 Birr and not more than 100,000 Birr, or imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (10) years; and
   (b) if the underpayment of tax is in an amount exceeding Birr 1,000, to a fine of not less than 75,000 Birr and not more than 200,000 Birr, or imprisonment for a term of not less than ten (10) years and notmore than fifteen (15) years.

፺፰· የግብር አስገቢውን ባለሥልጣን ሥራ ስለማሰናከል

፩· ማንኛውም ሰው፡—

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ ያለን የግብር አስገቢ ባለሥልጣን ሠራተኛ ተግባር ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ ፣ ወይም

ለ) የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ ፣ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ፣ ሲፈረድበት ከብር ፲ሺህ በማያንስ እና ከብር ፻ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና በሁለት ዓመት እሥራት ይቀጣል ።

፪· የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የግብር አስገቢውን ባለሥልጣን ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ፤

ሀ) የግብር ከፋዩን ገቢ አስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሠነዶችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት ፣

ለ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት ፣

ሐ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደ ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ።

፺፱· በግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም በግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተቀጠረ ማንኛውም ሰው ፡—

ሀ) በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ ፣ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ወይም

ለ) ከግብር በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም ፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ ፣ በግብር ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ ወይም በምሥጢር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ ፣ ወይም

ሐ) በዚህ አዋጅ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ከተሰጠው ሥልጣን በላይ የሠራ ወይም በተሰጠው ሥልጣን ያለአግባብ የተጠቀመ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፶ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፲ ዓመት በማያንስ ከ፳ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል ።

፻· ሳይፈቀድ ግብር ስለመሰብሰብ

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ሳይፈቀድለት ግብር ወይም እንደ ግብር የሚታይ ሌላ ክፍያ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ወንጀል የፈፀመ ሆኖ ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፶ሺህ በማያንስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ፭ ዓመት በማያንስ ከ፲ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል ።

፻፩· መርዳት ወይም ማበረታታት

ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሳሳ፣ ወይም በምስጢር የተባበረ እንደሆነ እንደዋናኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈፅማል። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈፀመ ሰው፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ዕርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል።

፻፪· በድርጅቶች የሚፈፀም ጥፋት

፩· በንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው በድርጅቱ የተፈፀመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ፣ በዚህ አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆንበታል ።

98. *Obstruction of Tax Administration*

1) A person who,

(a) obstructs or attempts to obstruct an officer of the Tax Authority in the performance of duties under this Proclamation, or

(b) otherwise impedes or attempts to impede the administration of the Proclamation,

commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 10,000 Birr and not more than 100,000 Birr, and imprisonment for a term of two (2) years.

2) The following and similar other actions are considered to constitute obstruction:

(a) refusal to satisfy a request of the Tax Authority for inspection of documents, reports, or other information related to a taxpayer's income-producing activities;

(b) non-compliance with a Tax Authority request to report for an interview;

(c) interference with a tax officer's right to enter the taxpayer's business premises.

99. *Offences by Tax Authority Employee*

Any person employed for carrying out the provisions of this Proclamaton who:

(a) directly or indirectly, asks for or receives in connection with any of the officer's duties, a payment or reward, whether pecuniary or otherwise, or promise or security for that payment or reward, not being a payment or reward to wich the officer is lawfully entitled to receive, or

(b) enters into or acquiesces in an agreement to do or to abstain from doing permit, conceal, or connive at any act or thing whereby the tax revenue is or may be defrauded, or which is contrary to the provisions of this Proclamation or to the proper execution of the officer's duty;

(c) exeeds the authority conferred upon the Tax Authority or misuses such authority;

commits an offence and is liable, on conviction, to a fine of not more than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than ten (10) years and not more than twenty (20) years.

100. *Unauthorized Tax Collection*

Any person who is not authorized to collect tax under this Proclamation collects or attempts to collect tax (or an amount the person describes as tax) commits an offence and is liable, on conviction, to a fine of not less than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (10) years.

101. *Aiding or Abetting*

A person who aids, abets, incites,or conspires with another personto commit a violation againstthis Proclamation also commits an offence under this proclamation and shall be subject to prosecution, and shall on conviction be liable to a fine and imprisonment not in excess of the amount of fine or period of imprisonment provided for the offence aided or a betted.

102. *Offences by Entities*

1) Subject to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, where an entity commits an offence, the manager of that entity at the time of the Commission of the offence is treated as having committed the same offence and is liable to a fine and imprisonment under this Proclamation.

፪· በንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ወይም አዋጁ እንደግብር የሚቆጥረውን ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈፀመበት ጊዜ ወይም ጥፋቱ ከተፈፀመበት ጊዜ· አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላው ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ለሚፈልገው ግብር እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ።

፫· በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገጉት፦

ሀ) ጥፋቱ የተፈፀመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ ፣

ለ) አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈፀም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን ፣ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ ፣

ተፈፃሚ አይሆኑበትም።

፬· ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት ለተሰጠው ሰው ግብሩን ቀንሶ በማስቀረቱ ምክንያት ዕቃ ለማቅረብ ወይም አገልግሎት ለመስጠት እምቢተኝነት ያሳየ ማናቸውም ሰው ከብር ፭ሺህ በማያንስ እና ከብር ፲ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣትና ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል ።

፭· ለንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) አፈፃፀም "ሥራ አስኪያጅ" ማለት፤

ሀ) የሽርክና ማኅበርን በሚመለከት የሽርክናው ማኅበር አባል ወይም የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ከሁለቱ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ፣

ለ) ድርጅትን በሚመለከት የኩባንያው የሥራ መሪ ፣ ሥራ አሥኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ፣

ሐ) የሰዎችን ኅብረት በሚመለከት የኅብረቱ ሥራ አሥኪያጅ ወይም በዚሁ ኃላፊነት እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ ፣ ነው።

፻፫· የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ አትሞ ስለማውጣት

፩· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺፫ – ፻፩ የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈፀም የተፈረደባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር ፣

ሀ) የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ ፣

ለ) ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር ፣

ሐ) ጥፋቱ የተፈጸመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመኖች ፣

መ) ሳይከፈል የቀረውን ግብር መጠን ፣

ሠ) በተጨማሪ እንዲከፈል የተወሰነበት ግብር ካለ ይህንኑ።

## ክፍል አሥር
## የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት

፻፬· የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በግብር ባለሥልጣኑ ኃላፊ አቅራቢነት እንደአግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስትር ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለሥልጣን ይሰየማሉ ።

፻፭· ኮሚቴው ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

፩· ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ሆኖ፣

ሀ) በግብር ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ ፣ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሣኔ ለመስጠት ፣

ለ) ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውም የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች መሰብሰብ ።

2) Subject to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, where an entity commits an offence by failing to pay an amount of tax, including an amount treated by this Proclamation as though it were tax, every person who is the manager of that entity at that time, or was a manager within six (6) months prior to the date of commission shall jointly and severally, be liable with that entity and that other person to the Tax Authority for the amount.

3) Sub-Articles (1) and (2) do not apply where:
   (a) the offence is committed without such person's knowledge or consent; and
   (b) such person has exercised the degree of care, diligence and skill that a reasonably prudent person would have exercised in comparable circumstances to prevent the commission of the offence.

4) Any person who refuses to supply goods or render services to a withholding agent, by reason of him withholding an amount of tax from the payment to that person, shall personally be liable to a fine of not less than Birr 5,000 and not exceeding Birr 10,000 and to imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years.

5) In Sub-Articles (1) and (2), "manager" means,
   (a) in the case of a partnership, a partner or manager of the partnership or a person purporting to act in either of those capacities;
   (b) in the case of a body, a director, manager, or officer of the company or a person purporting to act in any of those capacities; and
   (c) in the case of an association of persons, a manager or a person purporting to act in that capacity.

103. Publication of Names

1) The Authority shall from time to time publish by notice in daily Gazettes a list of persons who have been convicted of offences under Articles 93 to 101.

2) Every list published in terms of Sub-Article (1) shall specify:
   (a) the name and address, of the enterprise or of the person;
   (b) such particulars of the offence as the Authority may think fit:
   (c) the tax period or tax periods in which the offence occurred;
   (d) the amount or estimated amount of the tax evaded; and
   (e) the amount, if any, of the additional tax imposed.

## SECTION X
## Appeal Procedure

104. Review Committee

Members of the Review Committee shall be appointed by the Minister of Revenue or the competent authority of the regional government, as appropriate, upon the recommendation of the head of the Tax Authority.

105. Powers And Duties of Review Committee

1) The Review Committee shall be accountable to the head of the Tax Authority and shall have the following duties:
   (a) to examine and decide on all applications submitted by tax payers for compromise of penalty, interest, and waiver of tax liability;
   (b) to gather any written evidence or information relevant to the matter submitted;

ሐ) በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከግብሩ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት ፣

መ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሰጠው የግብር ውሣኔ ትክክለኛ ፣ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን ይኖረዋል ።

፪· የአቤቱታ አጣሪው ከግብር ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ግብር ከፋዩ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ፲ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው ።

፫· የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ የኮሚቴውን የውሣኔ ሀሳብ ሊያፀድቅ ወይም በውሣኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለፅ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል ።

፩፻፮· <u>መቀጫን ስለማንሳት</u>

የአበቱታ አጣሪ ኮሚቴ የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በግብር ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ማድረግ ይችላል ።

፩፻፯· <u>የግብር ውሣኔን በመቃወም ይግባኝ ስለማቅረብ መብት</u>

፩· በማንኛውም ግብር አወሳሰን ቅር የተሰኘ ማንኛውም ግብር ከፋይ፣ ከዚህ ስታች ባለው ንዑስ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ካሟላ ለግብር ይግባኝ ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "የይግባኝ ጉባዔ" ተብሎ ለሚጠቀሰው) ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

፪· ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያላሟላ ይግባኝ፣ በይግባኝ ጉባዔ ተቀባይነት አይኖረውም፣

ሀ) ግብር ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የግብር መጠን አምሳ በመቶ (፶ ፐርሰንት) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ካላስያዘ፣

ለ) የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ በደረሰው ወይም በአቤቱታ ኮሚቴ ውሣኔ በተሰጠ በ፴ ቀን ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ።

፩፻፰· <u>ይግባኝ የቀረበበትን ቀን</u>

ይግባኙ የቀረበበት ቀን ነው የሚባለው፡–

ሀ) በቀጥታ ለይግባኝ ጉባዔው የቀረበ ሲሆን ይግባኙ በመዝገብ ቤት የተመዘገበበት ቀን ይሆናል፣ ወይም

ለ) በሪኮማንዴ የተላከ ሲሆን፣ በፖስታ ቤት የተመዘገበበት ቀን ይሆናል፣

፩፻፱· <u>የይግባኝ ማመልከቻ ይዘት</u>

የይግባኙ ማመልከቻ በሁለት ቅጂ ተዘጋጅቶ የሚከተሉትን የያዘ ይሆናል።

ሀ) ግልጽ በሆነ ሁኔታ የይግባኙን ፍሬ ነገር፣ የይግባኙን ምክንያቶች፣

ለ) የግብር ከፋዩን ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ሐ) ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር በአባሪነት ሊቀርቡ የሚገባቸውን አግባብ ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች፣ እንዲሁም ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መያዣ የተከፈለበት ደረሰኝ ፎቶ ኮፒ።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) ውስጥ ከሀ–ሐ ከተዘረዘሩት መኻል አንዱ ቢጐድል የይግባኝ ጉባኤው ይግባኝ ባይ፣ የተባለውን ጉድለት እንዲያሟላ ይጠይቀዋል። ይግባኝ ባይ፣ በአምስት ቀኖች ውስጥ የተባለውን ጉድለት ያላስተካከለ እንደሆነ፣ የቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ ወዲያውኑ ውድቅ ይሆናል።

፩፻፲· <u>የይግባኝ ሰነዶችን ስለመስጠት</u>

፩· ይግባኙ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመሰማቱ አስቀድሞ፣

ሀ) የይግባኙ ማመልከቻ ግልባጭ በይግባኝ ጉባዔው አማካይነት ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን እንዲደርሰው ይደረጋል፣

ለ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን መልሱን ለይግባኝ ጉባዔው ሲያቀርብ ግልባጩን ለይግባኝ ባዩ ይሰጣል።

፪· አቤቱታው ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ የማስረዳት ኃላፊነት የይግባኝ ባይ ይሆናል።



(c) to summon any person, who directly or indirectly has dealt with the assessment, to appear before it for questioning him about the case under its investigation; and

(d) to review determination made by the Tax Authority for accuracy, completeness, and compliance with this Proclamation.

2) The Committee shall only review applications submitted to it within 10 days of receipt of tax assessment notification.

3) The Head of the Tax Authority may approve the recommendations or remand the case, with his observations, to the committee for further review.

106. Waiver of Penalty

The Review Committee may waive administrative penalties in accordance with the directives issued by the Minister of Revenue.

107. Right of Appeal against Assessment of Income

1) Any taxpayer who objects to an assessement may appeal to the Tax Appeal Commission (hereinafter referred to as the "Appeal Commission") upon the fulfillment of the requirements hereunder.

2) No appeal shall be accepted by the Appeal Commission, unless:

(a) a deposit of thirty-five percent (50%) of the desputed amount is made to the Tax Authority; and

(b) the appeal is lodged with the Appeal Commission within thirty (30) days following the day of receipt of the Assessment Notice or from the date of decision of the Review Committee.

108. *Date of Lodging Appeal*

The date on which an appeal is submitted shall be the date of:

(a) its registration by the archives of the Appeal Commission if it is delivered other than by registered mail; or

(b) registration by the post office if sent by registered mail.

109. *Contents of Memorandum of Appeal*

1) The memorandum of appeal shall be sumbitted in diplicate and shall include:

(a) a statement of the specific subject matter of the appeal and the reason for the appeal:

(b) the taxpayer's name, address, and TIN, and

(c) as attachements, any relevant supporting documents and a photocopy of the receipt for the appeal deposit.

2) Where any one of the first three conditions under Sub-Article (1) is missing, the Appeal Committee shall require the appellant to correct the deficiency within five (5) days, failing of: which the appeal shall be rejected.

110. *Service of Documents*

1) Prior to the first hearing of any appeal:

(a) a copy of the memorandum of appeal shall be served on the Tax Authority by the Appeal Commission; and

(b) the Tax Authority shall submit its reply to the Appeal Commission while at the same time giving a copy thereof to the appeallant.

2) The appellant shall have the burden of proof with a view of establishing his or its claim.

**፩፻፲፩· የይግባኝ ጉባዔ ውሣኔ**

፩· የይግባኝ ጉባዔው የቀረበውን ይግባኝ ከመረመረ በኋላ የይግባኝ ባዩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ውሣኔው የተሰጠበትን ቀን፣ በጉባዔው ስብሰባ የተገኙትን አባላት ዝርዝር የሊቀመንበሩን ስም ፣ አግባብ ኖሯቸው የተወሰዱት አንቀጾች የሚገኙበትን ሕግ የሚያብራራ ውሣኔ በጽሑፍ መስጠት አለበት።

፪· የይግባኝ ሰሚ ጉባዔውን ውሣኔ የያዘው መግለጫ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፤

ሀ) የተደረሰበትን ድምዳሜ (የይግባኝ ባዩ አቤቱታ ድጋፍ ያለው መሆን ያለመሆኑን ፣ ተቀባይነት ያገኘው በሙሉ ወይም በከፊል መሆኑን ፣ ተቀባይነት ይግባኙ ከመመሪያ ጋር ወደ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን የተመለሰ መሆኑን ፣ ይግባኝ ባዩ ሊከፈል የሚገባውን የግብር መጠን (ካለ) እና ይግባኝ ባዩ የሚጠየቅባቸውን ሌሎች ጉዳዮች ዝርዝር)፤

ለ) የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችና በይግባኙ ውስጥ የተጠቀሱትን ሕጎች ትርጉም፣ ይግባኙ በተሰማበት ወቅት በሙሉ በተነሱት አግባብ ባላቸው በእያንዳንዱ ጭብጥ ላይ የተሰጠውን እልባት፣ ውሣኔውን በሚመለከት ረገድ የተሰጠ የሃሳብ ልዩነት ካለ፤

ሐ) የይግባኝ ባዩን ይግባኝ የማቅረብ መብቶች።

፫· ውሣኔው የተገኙት የጉባዔው አባላት ፊርማና የጉባዔው ማኅተም ያርፍበታል።

፬· የይግባኝ ጉባዔ፣

ሀ) ይግባኝ ባይ በሁለት የቀጠሮ ጊዜዎች ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ይግባኙን ካቀረበ በኋላ የመልስ መልስ ሳያቀርብ ሲቀር፣

ለ) የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የይግባኙ ማመልከቻ ከደረሰው በኋላ በሁለት የቀጠሮ ጊዜዎች ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ለይግባኙ መልስ ሳይሰጥ ሲቀር፣

ተከራካሪው ወገን በሌለበት ውሣኔ ይሰጣል።

**፩፻፲፪· የይግባኝ ጉባዔን ውሣኔ በመቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ፤**

፩· የይግባኝ ጉባዔ የሰጠው ውሣኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የይግባኝ ጉባኤው ውሣኔ በተሰጠ በ፴ ቀን ውስጥ ጉዳዩን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ ስለሕጉ ስህተት ፍርድ ሊጠይቅ ይችላል።

፪· ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር ብቻ ተመልክቶ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩን ወደ ጉባዔው ይመልሳል።

፫· ሥልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት በሕግ ጥያቄ ላይ በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ውሣኔው በተሰጠ በ፴ ቀን ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት ይችላል። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሊያይ የሚችለው የመጀመሪያው ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚያየውን የሕግ ጉዳይ ብቻ ነው።

፬· ግብር ከፋዩ በግብር ይግባኝ ጉባዔ የተወሰነበትን ሙሉ ግብር ካልከፈለ በስተቀር የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን መቀበል የለበትም።

**፩፻፲፫· የይግባኝ ጉባዔ መቋቋም**

፩· የሚከተሉት የግብር ይግባኝ ጉባዔዎች እንዳስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ

ሀ) በፌዴራል ደረጃ የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባዔ፤

ለ) በእያንዳንዱ የክልል ዋና ከተማ፣ የክልል የግብር ይግባኝ ጉባዔ፣

ሐ) በእያንዳንዱ የዞን ዋና ከተማ፣ የዞን የግብር ይግባኝ ጉባዔና፣

መ) በእያንዳንዱ የወረዳ አስተዳደር ከተማ፣ የወረዳ የግብር ይግባኝ ጉባዔ።

111. *Decision of Appeal Commission*

1) After reviewing the case, the Appeal Commission shall issue a written decision setting out the TIN of the appellant and the date of decision, the names of the panel members and the panel's chair person, and a statement of the decision.

2) The statement of the Commissions decision shall include:

(a) the holding (whether the appellant's claim is justified and accepted partly or wholly, whether the claim is remanded with instructions to the Tax Authority; and the amount the appellant is required to pay, if any, and other necessary detailes of appeallant's liabilities);

(b) the factual findings, citation to the aplicable law, legal interpretation, a conclusion on each relevant issue presented; and any dissenting opinion.

(c) a summary of the appellant's appeal rights.

3) The decision shall be signed by the panel members present, and the Seal of the Appeal Commission shall be affixed thereon.

4) The Appeal Commission may decide ex-parte where:

(a) any appellant fails to give counter reply when neccssary, or to appear before it on two occasions, after lodging appeal;or

(b) the Tax Authority, after receiving the memorandum of appeal, fails to give reply or to appear before it on two occasions.

112. Appeal from Decision of Appeal Commission

1) Any party dissatisfied with the decision of the Appeal Commission may appeal to the competent court of appeal on the ground that it is erroneous on any matter of law within 30 days from the date of receipt of the written decision of the Appeal Commission.

2) The court of appeal shall hear and determine any question of law arising on appeal and shall, after reaching its decision thereon, return the case to the Commission.

3) An appeal to the next court of appeal from the decision of the lower court of appeal may be made by either party, within thirty (30) days of the decision of the lower court of appeal.

4) A taxpayer's appeal shall not be accepted by the court unless at the time the appeal is lodged, the taxpayer has paid the tax liability determined by the Appeal Commission.

113. *Establishement of Appeal Commission*

1) The following Tax Appeal Commissions shall be established:

(a) Federal Appeal Commission, at the Federal level;

(b) Regional Appeal Commission, in each Regional Government town;

(c) Zonal Appeal Commission, in each Zonal town; and ,

(d) Woreda Appeal Commission, in each Woreda Administrative town.

፪· በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ የክልሉ መንግሥት ከላይ በተጠቀሱት ማንኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኙት አካባቢዎች የተለየ የይግባኝ ጉባዔ ማቋቋም አስፈላጊ አለመሆኑን ሲረዳ እነዚህ ቦታዎች በአቅራቢያው በተቋቋመ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ያደርጋል።

፫· የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባዔ ተጠሪነቱ ለፍትሕ ሚኒስትር፣ የከተማ መስተዳድሮች ይግባኝ ጉባዔዎች ተጠሪነት ለየመስተዳድሩ ሥራ አስፈጻሚ፣ የክልል፣ የዞን እና የወረዳ የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች ተጠሪነት በየደረጃው ላሉ ሥራ አስፈጻሚ አካላት ይሆናል።

፩፻፲፬· <u>የይግባኝ ጉባዔ አባሉችን ስለመሰየም</u>

፩· በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አባላት በሕዝብ ዘንድ ባላቸው ታዋቂነትና ታማኝነት፣ ባላቸው ጠቅላላ እና ልዩ ዕውቀት እንዲሁም ከግብር ጋር በተገናኘ ጥፋት ካልፈፀሙ ሰዎች መካከል ተመርጠው ይሰየማሉ።

፪· እንደ አግባብነቱ የፍትሕ ሚኒስትር ወይም የከተማ መስተዳድር እና የክልል ሥራ አስፈጻሚ አካላት የግብር ይግባኝ ሰሚ አባላት የሚመረጡበትን መመዘኛ እና ስብጥር የሚወስን መመሪያ ያወጣሉ።

፫· ይህንን መመሪያ በመከተል የግብር ይግባኝ ጉባዔ አባላት የሚሆኑት እንደአግባብነቱ በፍትሕ ሚኒስትሩ ወይም አግባብ ባለው የከተማ መስተዳድር፣ የክልል፣ የዞን ወይም የወረዳ ሥራ አስፈጻሚ አካል ተመርጠው ይሾማሉ።

፬· የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ፕሬዚዳንት ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፩፻፲፫ (፫) ከተዘረዘሩት መካከል አግባብ ባለው አካል ይሾማል።

፭· በእያንዳንዱ የይግባኝ ጉባዔ ከአንድ የበለጡ ጉባዔዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። በዚህ ዓይነቱም ሁኔታ እያንዳንዱ ጉባዔ አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን የራሱን ሊቀ መንበር ከአባሉቹ መካከል ይመርጣል።

፮· የማንኛውም የይግባኝ ጉባዔ አባል የአገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመታት ጊዜ ይሆናል። በይግባኝ ጉባዔ ወይም በእያንዳንዱ ጉባዔ በሊቀመንበርነት እንዲያገለግል የተመረጠ ሰው የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ወይም በምትክነት የተመረጠ ሲሆን የተካው ሰው የቀረው የሥራ ጊዜ ይሆናል።

፯· የግብር ይግባኝ ጉባዔ ሊቀመንበር እና የቀሩትም ሌሎች አባሎች እንደአግባብነቱ ሚኒስትሩ ወይም የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ አካል በየጊዜው በሚወስነው መሠረት በጉባዔው ላይ እየተገኙ ለሠሩበት ጊዜ አበል ይከፈላቸዋል።

፩፻፲፭· <u>የይግባኝ ጉባዔ እና ሊቀመንበሩ ስለሚኖራቸው ተግባርና ሥልጣን፤</u>

፩· የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ፡

ሀ) በማስረጃ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችንና ሕግን መሠረት በማድረግ ይግባኝ የተመሠረተበትን የግብር ውሣኔ የማፅናት፣ የመቀነስ ወይም የመሠረዝ ሥልጣንና ለጉዳዩ የመጨረሻ ውጤት ለማስገኘት ትክክልና አስፈላጊ መስሉ የታየውን ማናቸውንም ተጨማሪ ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል።

ለ) የግብር አስገቢውን ባለሥልጣን ወይም ግብር ከፋዩን እንደነገሩ ሁኔታ ተጨማሪ ፍሬ ነገሮች ካሉ እነዚህኑ እንዲያቀርቡ መመሪያ ይሰጣል፣ እንዲሁም፣

ሐ) እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት፣ ግብር ከፋዩንም ሆነ ግብር አስገቢውን ባለሥልጣን፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ ሰው፣ ማኀበር፣ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት ግብር ከፋዩ ላቀረበው አቤቱታ አግባብ ያላቸውን ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ያዛል።

2) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1), if the Regional Government finds it unnecessry to have a separate Appeal Commission at any of the above mentioned levels, it shall make an arrangement in such a way that such areas may be covered by the Appeal Commission established in the neighboring locality.

3) The Federal Appeal Commission shall be accountable to the Minister of Justice; City administration, appeal commissions to the executive organs of city administration, region, zone, woreda, as the case may be.

114. *Appointment of Members*

1) Members of Appeal Commission at every level shall be appointed from among persons having good reputation, acceptability, integrity, general and professional knowledge, and from among persons who have not committed any offense in connection with tax and tax administration.

2) The Minister of Justice or executive organs of city administrations and regions, as the case may be, shall issue directives setting out the criteria to be applied in the selection, appointment and composition of members of Appeal Commissions.

3) On the basis of said directive members of the appeal commissions and panels shall be selected and appointed by the Minister of Justice or the appropriate city administration, regional, zonal or woreda executive organ, as the case may be.

4) The Appeal Commission's President shall be appointed by appropriate entities listed under Article 113(3)above.

5) Each Appeal Commission may have more than one (1) panel. In such cases each panel shall have five (5) members and shall elect one (1) members to serve as Chair person.

6) The person term of office of an Appeal Commission member shall be two (2) years. A member appointed to chair an Appeal Commission or a panel shall serve in that capacity for two (2) years or the remaining period of ıthat other member's term if he is a substtute.

7) The Chairperson and other members of the Commission shall be entitled to receive such attendance fees for sitting on panels as shall be fixed from time to time by the Minister or the Executive body of the Region, as appropriate.

115. *Powers and Duties of Appeal Commission and of its Chairperson*

1) The Appeal Commission shall have the authority:

(a) to confirm, reduce, or annul any assessment appealed against on the basis of established factual grounds and the law, and make such further consequential order thereon as may seem just and necessary for the final disposition of the matter;

(b) to instruct the Tax Authority or the taxpayer to submit new facts, if any; and

(c) to order the Tax Authority or the taxpayer or any other person or governmental department or agency, as the case may be, to produce supporting evidence relevant to the taxpayer's allegation.

፪· እያንዳንዱ የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ሊቀመንበር፣
ሀ) የይግባኙን ፍሬ ነገር የያዘውን ጽሑፍ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ ያደርግለታል፤
ለ) የጉባዔውን አጀንዳ ያዘጋጃል፤
ሐ) የይግባኝ ክርክሩ በሚሰማበት ወቅት ሊቀመንበሩ ጉባዔው ላይ ይቀመጣል፤ እንዲሁም ሥነ ሥርዓቱን ይመራል፤
መ) በቃለ ጉባዔ የተያዙ ወይም በውሣኔ ውስጥ የተመዘገቡ የቃል ወይም የፅሑፍ ክርክሮች ሁሉ በሚገባ መመዝገባቸውንና ሕግ በሚያዘው ፎርም ዓይነት መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፤
ሠ) በሊቀ መንበርነት የሚመራው ጉባዔ ስላከናወናቸው ተግባሮች ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል።

፩፻፲፮· የማስረዳት ኃላፊነት

የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሰጠው ውሣኔ ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳትኃላፊነቱየተወሰነውን ግብር ወይም የባለሥልጣኑን ውሣኔ የሚቃወመው ሰው ይሆናል።

፩፻፲፯ ደንብና መመሪያ የሚውጣት ሥልጣን

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ደንብ የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቶታል።
፪· የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

ክፍል አሥራ አንድ
የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩፻፲፰· የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩· ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ወቅት መከፈል ያለባቸውና በመከፈል ላይ ያሉ የግብር ክፍያዎች ወይም ከማናቸውም ንግድ ሥራ፣ የሞያ ሥራ፣ የቮኬሽን ሥራና ከማናቸውም ሌሎች ሥራዎች የተገኘን ገቢ ወይም በገቢነት የተመዘገበን በሚመለከት በዚህ አዋጅ የተሻሩ ሕጐች ሁሉ ተፈፃሚነት አላቸው።
፪· በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የይግባኝ ሰሚ ጉባዔዎች እስከሚቋቋሙ ድረስ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያሉት የይግባኝ ሰሚ ኮሚሲዮኖች ሁሉ ሥራቸውን እንደተለመደው በማካሄ[illegible] ይቀጥላሉ።

፩፻፲፱· የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕ[illegible]ች

፩· ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፶፫ ከነማሻሻያዎቹ ፣
፪· ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ግብር ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፰/፲፱፻፹፬፣
፫· የፌዴራል የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔን ለማቋቋም የወጣው ፲፱፻፺፫ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፫ ፲፱፻፺፫፣ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
፬· ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ሕጐች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

፩፻፳· አዋጁ የሚፀናበት ቀን፣

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ የፀና በመሆን እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚነት አለው።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም
ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2) An Appeal Commission's Chairperson shall:
(a) make preliminary examination of memoranda of appeal;
(b) prepare the agenda for the panel;
(c) preside over and guide the proceedings;
(d) ensure that the arguments are properly recorded in the minutes and that the decision conforms to the prescribed form; and
(e) submit an annual report about the accomplishment (performance) of the commission he presides over.

116. *Burden of Proof*

The burden of proving that an assessment is excessive or that a decision of the Authority is wrong lies on the person objecting to the assessment or decision.

117. *Power to Issue Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers shall issue regulations for the proper implementation of this Proclamation.
2) The Minister of Finance and Economic Development shall issue directives for thecarrying out of any power delegated to him under this Proclamation.

*SECTION XI*
*Transitional Provisions*

118. *Transitional Provisions*

1) All repealed laws hereunder, shall continue to apply to all liabilities that are already due and payable upon the coming into force of this Proclamation or are accrued in respect of income from trade, business, profession, vocations or any other activity taxable thereunder.
2) All existing Tax Appeal Commissions shall continue to function until such time as new Tax Appeal Commission has been established in accordance with the provisions of this Proclamation.

119. *Repealed and Inapplicable Laws*

1) The Income Tax Proclamation No. 173 of 1961 and all amendments thereto are hereby repealed.
2) Payment of Tax on Gains from Capital Proclamation No. 108/1994 is hereby repealed.
3) Federal Tax Appeal Tribunal Establishement Proclamation No. 233/2001.
4) All laws which are inconsistent with this Proclamation shall not apply on matters covered under this Proclamation.

120. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 4th day of July 2002, and shall apply to all income paid, received or earned from Hamle 1/1994 E.C. onward.

Done at Addis Ababa, this 4th day of July, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA